እምነታችን

The Westminster Confession of Faith

ተርጓሚና አሳታሚ
ቄስ ኃይሉ መኮንን

ኦርቶዶክስ ፕረስቢቴሪያን ቤተ ክርስቲያን
የመንፈሳዊ ትምህርት ሥነ ጽሑፍ አገልግሎት

አሳታሚው በጽሑፍ ከሚሰጠው ፈቃድ ውጪ ይህን መጽሐፍ
መገልበጥና ማባዛት የተከለከለ ነው።

Committe on Foreign Missions
The Orthodox Presbyterian Church
607 N. Easton Road, Bldg. E, Box P
Willow Grove, PA 19090-0920
USA

መግቢያ

ይህ «እምነታችን» ተብሎ የተሰየመው ጽሑፍ Westminster Confession of Faith[1] ከሚለው የእምነት መግለጫ የተተረጎመ ነው። ይህ የትምህርት መጽሐፍ በመጀመሪያ የተጻፈው በእንግሊዝ አገር እ. ኤ. አ. 1643 ዓ. ም. ሲሆን፤ የፕረስቢቴሪያን ቤተ ክርስቲያን የእምነት መመሪያ ሆኖ ለብዙ ዓመት አገልግሏል። አሁንም የወንጌል አማኝ የሆኑት የፕረስቢቴሪያን አብያተ ክርስቲያናት የእምነታቸው መመሪያ አድርገው ይጠቀሙበታል። ይህ መጽሐፍ አማርኛ አንበብው መረዳት ለሚችሉ ሁሉ ብዙ በረከት እንዲያመጣ ጸሎታችንና ምኞታችን ነው።

እምነታችን ከተሰኘው ጽሑፍ ቀጥሎ በጥያቄና በመልስ የተዘጋጀ ካተኪዝም ቀርቧል። ይህ ካተኪዝምም እንዲሁ በዌስት ሚንስተር ጉባኤ 1643 ዓ. ም. ተዘጋጀ። ያዘጋጁትም ሊቃውንት The Shorter Catechism ብለው ሰይመውታል። የአማርኛው ትርጉም ታርሞ የተዘጋጀው በአልበርት ሲ. እስትሮንግ፤ በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር 1963 ዓ. ም. ሲሆን፤ አሁን ደግሞ እኔ በዚህ መልክ አያይዤ አቅርቤዋለሁ። ካንዳንድ የቃላት ማስተካከል በሰተቀር ዋና ትርጉሙ ያው የበፊቱ ነው።

ቄስ ኃይሉ መኮንን
ጥቅምት 24 ቀን 14 ቀን 1983 ዓ. ም.
ዋሽንግተን ዲ. ሲ.

USA
24 October 1990

---

[1]ዌስትሚኒስተር የተባለው በለንደን የሚገኝ ቤተ ክርስቲያን ነው፤ ስሙም ዌስትሚኒስተር ቻፕል ይባላል። ጽሑፉን ያዘጋጀው ጉባኤ የተሰበሰበው በዚህ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለነበር የጽሑፉ ስም ዌስትሚኒስተር ተባለ።

ለሁለተኛው እትም መግቢያ

የመጀመሪያው እትም በተወሰነ ቁጥር ስለተባዛ በቶሎ ተበትኖ አለቀ። ብዙዎች ስላላገኙትና እንዲሁም በሌሎችም ቦታዎች በጣም ተፈላጊነት ስላገኘ፣ ይህን ሁለተኛ እትም ሳዘጋጅ ለጌታ ምስጋና እያቀረብሁ ነው።

ይህ ጽሑፍ በድጋሚ ሊዘጋጅና ሊታተም የቻለው ኦርቶዶክስ ፕሮስቢቴሪያን ቤተ ክርስቲያን የአማርኛ የመንፈሳዊ ሥነጽሑፍ አገልግሎት ስለጀመረች ነው። በእግዚአብሔር ድጋፍና በቤተ ክርስቲያኒቱ አገልግሎት፣ ከዚህ በኋላም በረካታ የመንፈሳዊ ትምህርት ያዘሉ ጽሑፎችን ለማሳተም ዓላማ አለን።

በመጀመሪያው እትም ላይ የነበሩት ብዙ የፊደላትና የቃላት ስሕተቶች በተቻለ መጠን በዚህ በሁለተኛው እትም ላይ ታርመዋል።

ባለፉት ዓመታት ውስጥ እግዚአብሔር የክርስቲያኖችን ቁጥር አበርክቷል። በዚያውም መጠን ደግሞ ሰይጣን ብዙ ሐሰተኛ ትምህርቶችን በክርስቲያኖች መካከል በመዝራት ለማሰናከል እየጣረ ነው። ይህ ጽሑፍ ምእመናን በእምነታቸው የተመሠረቱ እንዲሆኑ ይረዳቸዋል። ትምህርቱ በጣም ጥልቅ ከመሆኑ የተነሣ፣ ለአዲስ አማኞች የበሰሉ ክርስቲያኖች በማብራራት ሊረዱቸው ያስፈልጋል።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ምእመናንን ለማስተማር በሚያደርጉት ጥረት ይህ ጽሑፍ ጠቃሚ መሣሪያ ነው። በዚህ መጽሐፍ በሰፈሩት በአንዳንዶቹ ነጥቦች ሙሉ በሙሉ ሁላችንም እንደማንስማማባቸው ግልጽ ነው፤ ግን ቢያንስ ከመቶው በዘጠና አምስቱ ስለምንስማማባቸው፤ የማንስማማባቸው ነጥቦች የመጽሐፉን ጠቃሚነት ሊቀንሱት አይገባም። ስለዚህ ምእመናን ቃሉን በማወቅ እንዲጠነክሩ፥ ክርስቶስም በልባቸው በእነምት እንዲኖር፥ ሥርና መሠረታቸውም በፍቅር እንዲጸና፤ ይህ ጽሑፍ ተዘጋጀቶ ቀርቧል። ክብር ለአምላካቸንንና ለአዳኛችን ይሁን፤ አሜን!!

ቄስ ኃይሉ መኮንን
ጥር 15 ቀን 1989 ዓ. ም.
ቨርጂንያ፣ አሜሪካ
January 1997
USA

ምዕራፍ አንድ
መጽሐፍ ቅዱስ

1. ሰው በተፈጥሮ ያገኘው ሕሊና፥ የተፈጥሮ ነገሮች የሚያስተላልፉት መልእክትና እንዲሁም በታሪክ ውስጥ የሚፈጸሙት ድርጊቶች ባንድነት የእግዚአብሔርን ኃይል፤ የእግዚአብሔርን ጥበብና የእግዚአብሔርን በጎነት እንዲሁም መለኮታዊ ሕልውናን ምን ጊዜም ቢሆን ግልጽ አድርገው ያውጃሉ። ስለዚህ እግዚአብሔርን ላለማወቅ ከንቱ ምክንያት የሚፈጥሩትን መልስ ያሳጧቸዋል[1]። ይሁን እንጂ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ነገሮች ለደኅንነት አሰፈላጊ የሆነውን የእግዚአብሔርን እውቀትና ፈቃድ ሊገልጹ ብቁ አይደሉም[2]። ስለዚህ እግዚአብሔር በልዩ ልዩ ዘመናት፥ በልዩ ልዩ መንገዶች ራሱን ሊገልጽና ፈቃዱን ለቤተ ክርስቲያን ሊያውጅ በጎ ፈቃዱ ሆነ[3]። በኋላም እውነት በተሻለ መንገድ አዲጠበቅና እንዲተላለፍ፤ ቤተ ክርስቲያንም በበለጠ ተመሥርታና ጸንታ የሥጋን ማታላል፥ የሰይጣንና የዓለምን ማወናበድ መቋቋም እንድትችል የገለጻላትን በሙሉ በጽሑፍ አስቀመጠ[4]፤ ይህም መጽሐፍ ቅዱስ ነው[5]። ከዚህም የተነሣ መጽሐፍ ቅዱስ ከመጻፉ በፊት ፈቃዱን ያሳውቅባቸው የነበሩት መንገዶች አሁን ስላቆሙ ዓላማውንና ሐሳቡን በሙሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጠቅልሎታል[6]። ይህም ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስ እጅግ አሰፈላጊ መሆኑን ያስረዳል።

1. ሮሜ 2፡14፥15፤ 1፡19፥20፤ መዝ. 19፡1–4፤ እንዲሁም ሮሜ 1፡32ና 2፡1።
2. ዮሐ. 17፡3፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡21፤ 2፡13፥14።
3. ዕብ. 1፡1፥2።
4. ሉቃ. 1፡3፥4፤ ሮሜ 15፡4፤ ማቴ. 4፡4፥7፥10፤ ኢሳ. 8፡20።
5. 2ኛ ጢሞ. 3፡15፤ 2ኛ ጴጥ. 1፡19።
6. ዮሐ. 20፡31፤ 1ኛ ቆሮ. 10፡12፤ 14፡37፤ 1ኛ ዮሐ. 5፡13፤ ዕብ. 1፡1፥2፤ 2፡2–4።

2. መጽሐፍ ቅዱስ የሚከተሉት መጻሕፍት አሉት።

<u>የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት</u>

ኦሪት ዘፍጥረት
ኦሪት ዘጸአት
ኦሪት ዘሌዋውያን
ኦሪት ዘኍልቁ
ኦሪት ዘዳግም
መጽሐፈ ኢያሱ
መጽሐፈ መሳፍንት
መጽሐፈ ሩት

1ኛ ሳሙኤል
2ኛ ሳሙኤል
1ኛ ነገሥት
2ኛ ነገሥት
1ኛ ዜና መዋዕል
2ኛ ዜና መዋዕል
መጽሐፍ ዕዝራ
መጽሐፈ ነህምያ
መጽሐፈ አስቴር
መጽሐፈ ኢዮብ
መዝሙረ ዳዊት
መጽሐፈ ምሳሌ
መጽሐፈ መክብብ
መኃልየ መኃልይ
ትንቢተ ኢሳይያስ
ትንቢተ ኤርምያስ
ሰቆቃወ ኤርምያስ
ትንቢተ ሕዝቅኤል
ትንቢተ ዳንኤል
ትንቢተ ሆሴዕ
ትንቢተ አሞጽ
ትንቢተ ሚክያስ
ትንቢተ ኢዩኤል
ትንቢተ አብድዩ
ትንቢተ ዮናስ
ትንቢተ ናሆም
ትንቢተ ዕንባቆም
ትንቢተ ሶፎንያ
ትንቢተ ሐጌ
ትንቢተ ዘካርያስ
ትንቢተ ሚልክያስ

የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት

የማቴዎስ ወንጌል
የማርቆስ ወንጌል
የሉቃስ ወንጌል
የዮሐንስ ወንጌል
የሐዋርያት ሥራ
ወደ ሮሜ ሰዎች
1ኛ ቆሮንቶስ
2ኛ ቆሮንቶስ
ወደ ገላትያ ሰዎች
ወደ ኤፌሶን ሰዎች
ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች
ወደ ቆላስያስ ሰዎች
1ኛ ተሰሎንቄ
2ኛ ተሰሎንቄ
1ኛ ጢሞቴዎስ
2ኛ ጢሞቴዎስ
ወደ ቲቶ
ወደ ፊልሞና
ወደ ዕብራውያን
1ኛ ጴጥሮስ
2ኛ ጴጥሮስ
1ኛ ዮሐንስ
2ኛ ዮሐንስ
3ኛ ዮሐንስ
የያዕቆብ መልእክት
የይሁዳ መልእክት
የዮሐንስ ራእይ

እነዚህ ሁሉ የእምነትና የሕይወት መመሪያ ይሆኑ ዘንድ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የተጻፉ ናቸው[7]።

7. ሉቃ. 16፡29፥31፤ 24፡27፤ 2ኛ ጢሞ. 3፡15፥16፤ ዮሐ. 5፡46፥47።

3. አዋልድ መጽሐፍት በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፉ ስላይደሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍት ክፍል ውስጥ አይገቡም። ስለዚህ በእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምንም ሥልጣን የላቸውም። ተራ የሰዎች ጽሑፎች ከሚኖሯቸው ሥልጣን የተለየ ሥልጣን ተሰጥቷቸውም በሥራ ላይ ሊውሉ አይገባም[8]።

8. ራእ. 22፡18፥19፤ 2ኛ ጴጥ. 1፡21።

4. ልናምነውና ልንታዘዘው የሚገባን የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን የተመረኮዘው በማንም ሰው ወይም በቤተክርስቲያን ምስክርነት ላይ አይደለም፤ ነገር ግን እውነት በሆነውና በደራሲው በእግዚአብሔር ላይ ነው። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ብቻ በመሆኑ ሊታመን ይገባዋል[9]።

9. 2ኛ ጴጥ. 16፡29፥31፤ 24፡27፥44፤ 2ኛ ጢሞ. 3፡15፥16፤ ዮሐ. 5፡46፥47።

5. በቤተ ክርስቲያን ምስክርነት የተነሣ መጽሐፍ ቅዱስን እንድናከብር ልንገፋፋ አንችላለን[10]። የመልእክቱ መለኮታዊነት፥ የትምህርቱ ስምረት፥ ያጻጻፉ ግርማ፥ ልዩ ልዩ የሆኑት ክፍሎች ባንድነት መስማማት፥ ለእግዚአብሔር ክብር ለመስጠት ያለው ዓላማ፥ ሰው ሊድንበት የሚችልበትን መንገድ ማሳየቱ፥ ሌሎችም ተወዳዳሪ የሌላቸው የአጻጻፍ ውበቶቹና ሙሉነቱ በአንድነት መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ለመሆኑ ያለጥርጥር ያረጋግጣሉ። ይህም ሆኖ ሳለ ግን መጽሐፍ ቅዱስ ስህተት የሌለበት ፍጹም የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ልናምን የምንችለው ከቃሉ ጋር በመተባበር በልባችን ውስጥ ከሚመሰክረው ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሥራ የተነሣ ነው[11]።

10. 1ኛ ጢሞ. 3፡15

11. 1ኛ ቆሮ. 2፡9፥10፤ ዕብ. 4፡12፤ ዮሐ. 10፡35፤ ኢሳ. 55፡11፤ በተጨማሪም ሮሜ 11፡36፤ መዝ. 19፡7–11፤ እንዲሁም 2ኛ ጢሞ. 3፡15፤ 1ኛ ቆሮ. 2፡4፥5፤ 1ኛ ተሰ. 1፡5፤ 1ኛ ዮሐ. 2፡20፥27፤ እንደገናም ኢሳ. 59፡21

6. ስለ እግዚአብሔር ክብርና ስለሰው ደኅንነት፥ ስለ እምነትና ስለ ኑሮ የእግዚአብሔር ሐሳብ አንድም በግልጽ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ ይገኛል፤ ወይም ትከለኛ በሆነና አስፈላጊ በሆነ የማብራሪያ አስተሳሰብ ከተጻፈው ይደረስበታል። አዲስ የመንፈስ ቅዱስ መገለጥም ሆነ ሲወርድ ሲዋረድ በመጣ የሰዎች ትምህርት አንዳችም ነገር በቃሉ መጨመር አይቻልም[12]። ነገር ግን ከቃሉ ደኅንነት የሚሰጠውን እውቀት ለመቀበል መንፈስ ቅዱስ ለልቦና

ብርሃን እንደሚሰጥ አስፈላጊ መሆኑን እናምናለን[13]። በአምልኮተ እግዚአብሔር ሥርዓትና በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በኩል ቃሉ ሰግልጽ የማይጠቁማቸው በሰዎች ተግባርና በጎብረተሰቡ ያሉ አዳንድ ሁኔታዎች አሉ፤ እነሱም በተፈጥሮ ብርሃን፥ ጭምት በሆነ ክርስቲያናዊ የሐሳብ ሚዛን፥ ምንጊዜም ልንከተላቸው በሚገባን አጠቃላይ የቃሉ ሐሳብ ሊመሩ ይገባል[14]።

12. 2 ጢሞ. 3፡15–17፤ ገላ. 1፡8፥9፤ 2ኛ ተሰ. 2፡2
13. ዮሐ. 6፡45፤ 1ኛ ቆሮ. 2፡12፥14፥15፤ ኤፌ. 1፡18፤ 2ኛ ቆሮ. 4፡6
14. 1ኛ ቆሮ. 11፡13፥14፤ 14፡26፥40

7. በመጽሐፍ ቅዱስ የሰፈሩት ነገሮች ሁሉ በራሳቸው እኩል ግልጽነት የላቸውም። እንዲሁም ለሁሉም እኩል ግልጽ አይሆኑም[15]። ነገር ግን ለደኅንነት ሊደያበቁ፥ ሊታመኑና ሊጠበቁ የሚገባቸው በግልጽ ስለተጻፉና ባንድ ወይም በሌላ ቦታ ተብራርተው ስለሚገኙ የተማሩት ብቻ ሳይሆኑ ያልተማሩትም መጠነኛ ጥረት በማድረግ ሊገነዘቧቸው ይችላሉ[16]።

15. 2ኛ ጴጥ. 3፡16
16. መዝ. 119፡105፥130፤ ዘዳ. 29፡29፤ 30፡10–14፤ የሐዋ. 17፡11

8. መጽሐፍ ቅዱስ በቀጥታ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት ስለተጻፈና በእግዚአብሔርም ጥበቃና እንክብካቤ ከስህተት ስለተጠበቀ እውነተኛነቱ የማይጠረጠር ነው[17]። በሃይማኖትም ከርክር ሁሉ ቤተ ክርስቲያን የመጨረሻ የአቤቱታዋ ማሰሪያ ታደርገዋለች[18]። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስን ለማወቅ መብት ያላቸው የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ በእግዚአብሔር ፍርሃት መጽሐፍ ቅዱስን እንዲያነቡና እንዲመረምሩ ስለታዘዙ[19]፤ መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያ የተጻፈባቸው ቋንቋዎችም አሁን ለእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ ስለማይታወቁ መጽሐፍ ቅዱስ የመጣላቸው ሕዝቦች ሁሉ[20] የእግዚአብሔር ቃል በሙላት በሁሉም እንዲገኝ እግዚአብሔርንም በሚገባ እንዲያመልኩትና[21] መጽሐፍ በሚሰጠው ትእግሥትና መጽናናት ተስፋ እንዲያደርጉ፥ መጽሐፍ ቅዱስ በቋንቋቸው ሊተረጎምላቸው ይገባል[22]። ብሉይ ኪዳን በመጀመሪያ የተጻፈው የጥንት የእግዚአብሔር ሕዝብ ቋንቋ በነበረው በዕብራይስጥ ሲሆን አዲስ ኪዳን ደግሞ በዘመኑ የነበሩ የአብዛኛዎቹ ሕዝቦች ቋንቋ በነበረው በግሪክ ቋንቋ ተጻፈ።

17. ማቴ. 5፡18፤ መዝ. 119፡89
18. ኢሳ. 8፡20፤ ማቴ. 15፡3፥6፤ የሐዋ. 15፡15፤ ሉቃስ 16፡31
19. ዮሐ. 5፡39፤ የሐዋ. 17፡11፤ ራእ. 1፡3፤ 2ኛ ጢሞ. 3፡14፥15
20. ማቴ. 28፡19፥20፤ 1ኛ ቆሮ. 14፡6፤ ማር. 15፡34

21. ቆላ. 3፡16፤ ዘጸ. 20፡4-6፤ ማቴ. 15፡7-9
22. ሮሜ 15፡4

9. መጽሐፍ ቅዱስን ያለስህተት የሚተረጉም ራሱ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው። ስለዚህ የአንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ትርጉም አሻሚ ሆኖ ሲገኝ፥ ገለጥ ብሎ የተነገረበት ቦታ ለአሻሚው ክፍል አብራሪ ሆኖ መቅረብ አለበት[23]። የአንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ትርጉምም ብዙ ሳይሆን አንድ ብቻ ነው።

23. የሐዋ. 15፡15፤ ዮሐ. 5፡46፤ 2ኛ ጴጥ. 1፡20፥21

10. የሃይማኖት ከርከር ሁሉ የበላይ መፍቻ መጽሐፍ ቅዱስ ሊሆን ይገባል። የአብያተ ክርስቲያናት ቃለ ጉባኤ፥ የጥንት ሊቃውንት አስተያየቶች፥ የሰዎች ትምህርቶችና የግል አስተያየቶች በሙሉ በመጽሐፍ ቅዱስ መመዘን ይገባችዋል። መጽሐፍ ቅዱስ በሚሰጠውም ውሳኔ ልንረጋ ይገባናል[24]።

24. ማቴ. 22፡29፥31፤ የሐዋ. 28፡25፤ 1ኛ ዮሐ. 4፡1-6

ምዕራፍ ሁለት
ትምህረተ ሥላሴ

1. እውነተኛና ሕያው የሆነ[1] አንድ አምላክ ብቻ አለ[2]። እሱም በባሕርዩ ውስን ያልሆነና ፍጹም ብጹዕ የሆነ[3]፥ ንጹህ መንፈስ[4]፥ የማይታይ[5]፥ ሥጋ የሌለው፥ የማይከፋፈል[6]፥ ከሰዎች ባሕርይ የተለየ[7]፥ የማይለወጥ[8]፥ ታላቅ[9]፥ ዘላለማዊ[10]፥ በሰው አእምሮ ተጠቅልሎ የማይወሰን[11]፥ ኃያል[12]፥ በጥበብ የተሞላ[13]፥ ፍጹም ቅድስናን የተጎናጸፈ[14]፥ ፍጹም ነጻነት ያለው[15]፥ በሁሉ ነገር ፍጹም ሙሉነትን የተቀዳጀ[16]፥ ሁሉን ነገር ለራሱ ክብር[17] በማይለወጠውና ጻድቅ በሆነው ምክሩ የሚሠራ[18]፥ ፍጹም አፍቃሪ[19]፥ ቸር፥ መሐሪ፥ ታጋሽ፥ በመልካምነትና በእውነተኛነት የበለጸገ፥ በደልን፥ ኃጢአትንና መተላለፍን የሚምር[20]፥ አጥብቀው ለሚፈልጉት ዋጋቸውን የሚሰጥ[21]፥ በፍርዱ ፍጹም ጻድቅና አስፈሪ[22]፥ ኃጢአትን የሚጠላ[23]፥ በደለኛውን እንዲሁ ንጹህ ነህ የማይል ነው[24]።

1. ዘዳ. 6፡4፤ 1ኛ ቆሮ. 8፡4፤ ገላ. 3፡20
2. 1ኛ ተሰ. 1፡9፤ ኤር. 10፡10
3. ኢዮ. 11፡7፥8፥9፤ 26፡14፤ መዝ. 139፡6
4. ዮሐ. 4፡24

5. 1ኛ ጢሞ. 1፡17፤ ዮሐ. 1፡18
6. ዘጸ. 4፡15፥16፤ ዮሐ. 4፡24፤ ሉቃ. 24፡39
7. የሐዋ. 14፡11፥15
8. ያዕ. 1፡17፤ ሚል. 3፡6
9. 1ኛ ነገ. 8፡27፤ ኤር. 23፡23፥24
10. መዝ. 90፡2፤ 1ኛ ጢሞ. 1፡17
11. መዝ. 145፡3፤ ሮሜ 11፡34
12. ዘፍ. 16፡27
13. ሮሜ 16፡27
14. ኢሳ. 6፡3፤ ራእ. 4፡8
15. መዝ. 115፡3፤ ኢሳ. 14፡24
16. ኢሳ. 45፡5፥6፤ ዘጸ. 3፡14
17. ኤፌ. 1፡11
18. ምሳ. 16፡4፤ ሮሜ 11፡36፤ ራእ. 4፡11
19. 1ኛ ዮሐ. 4፡8፥16፤ ዮሐ. 3፡16
20. ዘጸ. 34፡6፥7
21. ዕብ. 11፡6
22. ነህ. 9፡32፥33፤ ዕብ. 10፡28-31
23. ሮሜ 1፡18፤ መዝ. 5፡5፥6፤ 11፡5
24. ዘጸ. 34፡7፤ ነህ. 1፡2፥3፥6

2. እግዚአብሔር ሙሉ ሕይወት[25]፥ ክብር[26]፥ መልካምነት[27]፥ ብፁዕነት[28] በራሱና ከራሱ አለው። በራሱና ለራሱ ፍጹም የተሟላ ስለሆነ ፍጥረቶቹ ለምንም አያስፈልጉትም[29]። የራሱን ክብር በፍጥረቶቹ ውስጥ፥ በፍጥረቶቹ ላይ፥ በፍጥረቶቹ በኩል ይገልጻል እንጂ የሌለውን ክብር ፍጥረቶቹ አይጨምሩለትም[30]። እሱ ብቻ የሕይወት ምንጭ ነው፤ ሁሉ ነገር ከርሱ፥ በርሱ፥ ለእርሱ ነው[31]። በሁሉም ላይ ባለሙሉ ሥልጣን ነው። የፈለገውን ሁሉ በነርሱ በኩል፥ ለነርሱ፥ በነርሱ ላይ ያደርጋል[32]። በፊቱ ሁሉ ነገር የተከፈተና የተገለጠ ነው[33]፤ እውቀቱም ወሰን የሌለው፥ ስህተት የሌለው፥ በፍጥረቶቹ የማይደገፍ[34] ስለሆነ ሁልጊዜ እርገጠኛ የሆነ ነው[35]። በምክሩ ሁሉ፥ በሥራው ሁሉ፥ በትእዛዙ ሁሉ ፍጹም ቅዱስ ነው[36]። ከመላእክትና ከሰዎች ከሌሎችም ፍጥረታት ሁሉ ስግደት ቢሆን አገልግሎት ወይም መታዘዝ በፈለገው ጊዜ መጠየቅ ይችላል[37]።

25. ኤር. 10፡10፤ ዮሐ. 5፡26
26. የሐዋ. 7፡2
27. መዝ. 119፡68
28. 1ኛ ጢሞ. 6፡15፤ ሮሜ 9፡5
29. የሐዋ. 17፡24፥25
30. ሉቃ. 17፡10

31. ሮሜ 11፡36
32. ራእ. 4፡11፤ ዳንኤል 4፡25÷35፤ 1ኛ ጢሞ. 6፡15
33. ዕብ. 4፡13
34. ሮሜ 11፡33÷34፤ መዝ. 147፡5
35. የሐዋ. 15፡18፤ ሕዝ. 11፡5
36. መዝ. 145፡17፤ ሮሜ 7፡12
37. ራእ. 5፡12–14

3. እግዚአብሔር በአምላክነት፥ በባሕርይ፥ በኃይል፥ በዘላለማዊነት አንድ ሲሆን፤ በአካል ግን ሦስት ነው። ሦስቱ አካላትም አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ ናቸው[38]። አብ ከማንም የማይወጣና የማይሰርጽ፥ ወልድ ከዘላለም ከአብ የተወለደ[39]፥ መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ከዘላለም የሚሠርጽ ነው[40]።

38. ማቴ. 3፡16÷17፤ 28፡19፤ 2ኛ ቆሮ. 13፡14፤ ኤፌ. 2፡18
39. ዮሐ. 1፡14÷18፤ ዕብ. 1፡2÷3፤ ቆላ. 1፡15
40. ዮሐ. 15፡26፤ ገላ. 4፡6

ምዕራፍ ሦስት
የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ

1. እግዚአብሔር ከዘለዓለም ጀምሮ ፍጹም ጥበብ በሞላበትና ቅዱስ በሆነው ፈቃዱ፤ በነጻነትና በማይለወጥ ውሳኔ እንዲሆን ያሰበውን ሁሉ አስቀድሞ ወሰነ[1]። ይህንንም ሲወስን እግዚአብሔር ራሱ የኃጢአት መንሥኤ ባለመሆን[2] እንዲሁም የፍጡሮቹን ፈቃድ ባለመጣስ ነው። የፈቃዱ ፈጻሚ መሣሪያዎች ነጻነታቸው ወይም መሣሪያነታቸው የተጠበቀ ይሆናል እንጂ አይሻርም[3]።

1. መዝ. 33፡11፤ ኤፌ. 1፡11፤ ዕብ. 6:17
2. መዝ. 5፡4፤ ያዕ. 1፡13÷14፤ 1ኛ ዮሐ. 1፡5፤ ዕብ. 1፡13
3. የሐዋ. 2፡23፤ ማቴ. 17፡12፤ የሐዋ. 4፡27÷28፤ ዮሐ. 19፡11፤ ምሳ. 16፡33

2. እግዚአብሔር እንዲፈጸሙ የወሰናቸውን ነገሮች ሁሉ አስቀድሞ ቢያውቅም[4]፤ እንዲፈጸሙ የወሰናቸውን ነገሮች ያቀደው ወደፊት የሚፈጸሙትን ነገሮች አስቀድሞ ስላወቃቸው አይደለም። ወይም ምን ቢፈጸም ምንን እንድሚያስከትል አስቀድሞ ስላወቀ አይደለም[5]።

4. 1ኛ ሳሙ. 23፡11÷12፤ ማቴ. 11፡21÷23
5. ሮሜ 9፡11÷13÷16÷18

3. ለክብሩ መገለጫ አንዳንድ ሰዎችና መላእክት[6] ለዘለዓለም ሕይወት በእግዚአብሔር አስቀድመው ሲወሰኑ፤ ሌሎች ደግሞ ለዘለዓለም ሞት አስቀድመው በእግዚአብሔር ተወስነዋል[7]።

6. 1ኛ ጢሞ. 5፡21፤ ይሁ. 6፤ ማቴ. 25፡31+41
7. ኤፌ. 1፡5+6፤ 9፡22+23፤ ምሳ. 16፡4

4. እነዚህ መላእክትና ሰዎች እንዲህ አስቀድመው በነፍሰ ወከፍና በማይሻር ውሳኔ ስለታቀዱ፥ ቁጥራቸው አይጨምርም ወይም አይቀንስም[8]።

8. ዮሐ. 13፡18፤ 2ኛ ጢሞ. 2፡19፤ ዮሐ. 10፡14-16+27+28፤ ዮሐ. 17፡2+6+9-12

5. ከሰዎች መካከል ለሕይወት የተመደቡት እግዚአብሔር ዓለም ከመፈጠሩ በፊት በዘለዓለማዊና በማይለወጠው ዓላማው፤ በማይመረመረው ምክሩና በበጎ ፈቃዱ፥ በክርስቶስ ለዘለዓለም ክብር ስለመረጣቸው ነው[9]። ይህም በነጻ ጸጋውና ፍቅሩ ብቻ እንጂ፥ እንደሚያምኑ ወይም መልካም ሥራ እንደሚሠሩና እንደሚጸኑ በማወቁና ወይም ከፍጡሮቹ በሚገኝ ምክንያት በመማረኩ አይደለም[10]። ይህም ሁሉ ለጸጋው ክብር ነው[11]።

9. ኤፌ. 1፡4+9+11፤ ሮሜ 8፡28-30፤ 2ኛ ጢሞ. 1፡9፤ 1ኛ ተሰ. 5፡9
10. ሮሜ 9፡11+13+15+16፤ ኤፌ. 2፡8+9፤ 1፡5+9+11
11. ኤፌ. 1፡6+12

6. እግዚአብሔር የተመረጡትን ለክብር እንደወሰነ ሁሉ እንዲሁም ደግሞ ውሳኔው የሚከናወንበትን መንገድም በራሱ ፈቃድ አብሮ ውስኗል[12]። ስለዚህ የተመረጡት በአዳም ወድቀው በክርስቶስ ይድናሉ[13]። በክርስቶስ ወደ እምነት በመንፈሱ ይጠራሉ፥ ይጸድቃሉ፥ ልጅነትን ይቀበላሉ፥ ይቀደሳሉ[14]፥ በሱ ኃይል ለደኅንነት በእምነት ይጠበቃሉ[15]። ከተመረጡትም በሰተቀር ሌሎች በክርስቶስ ወደ እምነት አይጠሩም፥ አይጸድቁም፥ ልጅነትን አይቀበሉም፥ አይቀደሱም፥ አይድኑም[16]።

12. 1ኛ ጴጥ. 1፡2፤ ኤፌ. 2፡10፤ 2ኛ ተሰ. 2፡13
13. 1ኛ ተሰ. 5፡9+10፤ ቲቶ 2፡14
14. ሮሜ 8፡30፤ ኤፌ. 1፡5፤ 2ኛ ተሰ. 2፡13
15. 1ኛ ጴጥ. 1፡5
16. ዮሐ. 10፡14+15+26፤ 6፡64፤ ሮሜ 8፡28-39፤ ዮሐ. 8፡47፤ 17፡9፤ 1ኛ ዮሐ. 2፡19

7. የቀሩት ሰዎች እግዚአብሔር በማይመረመረው ምክሩና ፈቃዱ ምሕረትን ለመስጠትም ለመንፈግም እንደመልካም ፈቃዱ ስለሚያደርግ፤ በፍጡሮቹ ላይ ላለው ለኃይሉ ክብር ይሆን ዘንድ፤ ሳይመርጥ አልፎአቸዋል። እነሱንም በኃጢአታቸው ምክንያት ለገናናው ፍርዱ ክብር ይሆን ዘንድ፤ ለውርደትና ለቁጣ መሰናቸዋል[17]።

17. ማቴ. 11፡25፥26፤ ሮሜ 9፡17፥18፥21፥22፤ ይሁ. 4፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡8፤ 2ኛ ጢሞ. 2፡19፥20

8. ይህ የእግዚአብሔር ከፍተኛ የውሳኔ ምሥጢር ትምህርት በጥሩ ዘዴና ጥንቃቄ ሊያገ ይገባዋል[18]። ይህም ሰዎች በቃሉ የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ በትጋት በመከተልና በመታዘዝ በጥሪያቸው ጽኑነት ለዘለዓለም የተመረጡ መሆናቸውን እንዲያረጋግጡ ነው[19]። በዚህ ሁኔታ ይህ ትምህርት ለምስጋና፥ ለአክብሮት፥ እግዚአብሔርን ለማድነቅ ምክንያት እየሆነ ከልባቸው ወንጌልን ለሚታዘዙ ሁሉ ለትሕትና፥ ለትጋት፥ ለትልቅ መጽናናት ይሆንላቸዋል[21]።

18. ሮሜ 9፡20፤ 11፡33፤ ዘዳ. 29፡29
19. 2ኛ ጴጥ. 1፡10፤ 1ኛ ተሰ. 1፡4፥5
20. ኤፌ. 1፡6፤ ሮሜ 11፡33
21. ሮሜ 11፡5፥6፥20፤ 8፡33፤ ሉቃስ 10፡20፤ 2ኛ ጴጥ. 1፡10

ምዕራፍ አራት
እግዚአብሔር ዓለምን እንደፈጠረ

1. አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ[1] ዘላለማዊ የኃይሉን ክብር፥ የኃይሉን ጥበብ፥ የኃይሉን መልካምነት[2] ለመግለጽ የሚያታዩትንና የማይታዩትን፥ በስድስት ቀን በመጀመሪያ ለመፍጠር መልካም ፈቃዱ ሆነ። የፈጠረውም ሁሉ መልካም ነበር[3]።

1. ሮሜ 11፡36፤ 1ኛ ቆሮ. 8፡6፤ ዕብ. 1፡2፤ ዮሐ. 1፡1፥3፤ ዘፍ. 1፡2፤ ኢዮ. 33፡4
2. ሮሜ 1፡20፤ ኤር. 10፡12፤ መዝ. 104፡24፤ 33፡5
3. ዘፍ. 1፡1–31፤ መዝ. 33፡6፤ ዕብ. 11፡3፤ ቆላ. 1፡16፤ የሐዋ. 17፡24፤ ዘጸ. 20፡11

2. እግዚአብሔር ሌሎችን ፍጥረቶች ሁሉ ከፈጠረ በኋላ ሰውን ሴትና ወንድ አድርጎ[4] ፈጠረ። አእምሮና የማትሞት ነፍስንም ሰጣቸው[5]። በተጨማሪም እውቀትን፥ ጽድቅን፥ እውነተኛ ቅድስናን ሰጥቶ በራሱ መልክ[6] ፈጠራቸው። ሕጉን በልቦናቸው ጻፈላቸው[7]። የሰጣቸውን ሕግ ለመፈጸም የሚያስችል ኃይል ሰጣቸው[8]። አብሮም ሕጉን ለመጠበቅ ወይም ለመተላለፍ የመምረጥ ችሎታ ሰጥቶ ፈጠራቸው[9]። በልቦናቸውም ከተጻፈው ሕግ በተጨማሪ መልካምንና ክፉን የምታስታውቀውን ዛፍ እንዳይበሉ የሚል ትእዛዝ ተቀበሉ[10]። ይህንም ትእዛዝ እስከጠበቁ ድረስ ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ዝምድናቸው በመደሰት በፍጥረት ሁሉ ላይ ሥልጣን ነበራቸው[11]።

4. ዘፍ. 1፡27
5. ዘፍ. 2፡7፤ መክ. 12፡7፤ ሉቃ. 23፡43፤ ማቴ. 10፡28
6. ዘፍ. 1፡26፤ ቆላ. 3፡10፤ ኤፌ. 4፡24
7. ሮሜ 2፡14፥15
8. ዘፍ. 2፡17፤ መክ. 7፡29
9. ዘፍ. 3፡6፥17
10. ዘፍ. 2፡17፤ 2፡15-3፡24
11. ዘፍ. 1፡28፤ 1፡29፥30፤ መዝ. 8፡6-8

ምዕራፍ አምስት
መግቦተ እግዚአብሔር

1. ሁሉን ነገር የፈጠረው ታላቁ እግዚአብሔር ፍጥረቶቹን ሁሉ፥ ድርጊቶቹን ሁሉ፥ ነገሮችን ሁሉ[1] ከታላቁ እስከ ታናሹ[2] በጥበበኛውና በቅዱሱ አስተዳደሩ[3]፥ በማይሳሳተው የቀደመው እውቀቱ[4]፥ በነጻና በማይለወጠው የፈቃዱ ምክር[5]፥ ለጥበቡ፥ ለኃይሉ፥ ለፍርዱ፥ ለመልካምነቱ፥ ለምሕረቱ[6] ክብር ይሆን ዘንድ ሁሉን ነገር ይደግፋል፥ ይመራል፥ በየፈርጁ ያስቀምጣል፥ ያስተዳድራል[7]።

1. ነህ. 9፡6፤ መዝ. 145፡14-16፤ ዕብ. 1፡3
2. ዳን. 4፡34፥35፤ መዝ. 135፡6፤ የሐዋ. 17፡25-28፤ ኢዮ. 38፡1-41፡34
3. ማቴ. 10፡29-31፤ ማቴ. 6፡26-32
4. ምሳ. 15፡3፤ 2ኛ ዜና 16፡9፤ መዝ. 104፡24፤ 145፡17
5. የሐዋ. 15፡18፤ ኢሳ. 42፡9፤ ሕዝ. 11፡5
6. ኤፌ. 1፡11፤ መዝ. 33፡10፥11
7. ኢሳ. 63፡14፤ ኤፌ. 3፡10፤ ሮሜ 9፡17፤ ዘፍ. 45፡7፤ 145፡7

2. እግዚአብሔር በቀደመው እውቀቱና ዕቅዱ የነገሮች ሁሉ መነሻ ነው። ሁሉንም ነገሮች ባለመለወጥ እንዲሁም ያለስህተት[8] እንዲፈጸሙ ያደርጋል። ይሁን እንጂ ይህን ሁሉ ሲያደርግ አፈጻጸሙ በተፈጥሮ ሕግ መሠረት ነው፤ ያም አስፈላጊ በሆነ መንገድ ወይም ምርጫን በተከተለ መንገድ ወይም አንዱን የሌላው ውጤት በማድረግ ይሆናል[9]።

8. የሐዋ. 2፡23፤ ኢሳ. 14፡24፥27
9. ዘፍጥ. 8፡22፤ ኤር. 31፡35፤ ኢሳ. 10፡6፥7፤ ዘጸ. 21፡13፤ ዘዳ. 19፡5፤ 1ኛ ነገ. 22፡28–34

3. እግዚአብሔር በተራ አስተዳደሩ በፍጥረቶቹ አማከይነት ይሠራል[10]። ነገር ግን ያለፍጡሮቹ መተባበር[11] ወይም ከፍጡሮቹ ፈቃድ ውጭ በሆነ መንገድ[12] ወይም የፍጡሮቹን ፈቃድ በመቃወም[13] እንደወደደ ለመሥራት ነጻ ነው።

10. የሐዋ. 27፡24፥31፤ ኢሳ. 55፡10፥11
11. ሆሴ. 1፡7፤ ማቴ. 4፡4፤ ኢዮ. 34፡20
12. ሮሜ 4፡19–21
13. 2ኛ ነገ. 6፡6፤ ዳን. 3፡27

4. የእግዚአብሔር ታላቅ ኃይሉ፥ የማይመረመረው ጥበቡና፥ ወሰን የሌለው መልካምነቱ በአስተዳደሩ ሁሉ ይገለጻል። በመጀመሪያም ሰው በኃጢአት በወደቀ ጊዜ ተገልጾአል፤ በሌሎችም የሰዎችና የመላእክት ኃጢአት ተገልጾአል[14]። ይህም እንዲሁ ባዶ ፈቃድ መስጠት ብቻ አይደለም[15]፤ ነገር ግን ጥበቡንና ኃይሉን በመግለጽ[16] ድርጊቶችን ሁሉ በብዙ ዓይነት መንገድ እየተቆጣጠረ ለራሱ ቅዱስ ዓላማ[17] ያውላቸዋል። ይህን ሁሉ ሲያደርግም ኃጢአተኛነት ከፍጡሩ ብቻ ይመነጫል እንጂ ከእግዚአብሔር አይመነጭም። እርሱም ፍጹም ቅዱስና ጻድቅ ስለሆነ የኃጢአት መነሻ ወይም የኃጢአት ደጋፊ አይደለም[18]።

14. ኢሳ. 45፡7፤ ሮሜ 11፡32–34፤ 2ኛ ሳሙ. 16፡10፤ የሐዋ. 2፡23፥28፤ 2ኛ ሳሙ. 24፡1፤ 1ኛ ዜና 21፡1፤ 1ኛ ነገ. 22፡22፥23፤ 10፡4፥13፥14።
15. ዮሐ. 12፡40፤ 2ኛ ተሰ. 2፡11
16. መዝ. 76፡10፤ 2ኛ ነገ. 19፡28
17. ዘፍ. 50፡20፤ ኢሳ. 10፡6፥7፥10–15
18. ያዕ. 1፡13፥14፥17፤ 1ኛ ዮሐ. 2፡16፤ መዝ. 50፡21

5. ፍጹም ጠቢብ፥ ጻድቅና ቸር የሆነው እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ ለተወሰነ ወቅት የራሱን ልጆች በብዙ ፈተናዎችና በራሳቸው የልቦና

ርኩሰት ውስጥ ይተዋቸዋል። ይህም ለቀድሞው ኃጢአታቸው ሊቀጣቸው፥ ወይም ተደብቆ ያለው የልባቸው ርኩሰትና አታላይነት ምን ያህል ጠንካራ መሆኑን እንዲገነዘቡና ትሑት እንዲሆኑ[19]፥ እንዲሁም በሱ ላይ በቅርብና ቶሎ ቶሎ እንዲደገፉ፥ ለወደፊትም በኃጢአት ከመውደቅ እንዲጠበቁ፥ እንዲህ ለመሳሰሉትና ሌሎች ትክክልና ቅዱስ ምክንያቶች ይህን ያደርጋል[20]።

19. 2ኛ ዜና 32፡25፥26፥31፤ ዘዳ. 8፡2፥3፥5፤ ሉቃ. 22፡31፥32፤ 2ኛ ሳሙ. 24፡1፥25
20. 2ኛ ቆሮ. 12፡7፥8፥9፤ መዝ. 73፡1–28፤ 77፡1–12፤ ማር. 14፡66፡–72፤ ዮሐ. 21፡15–19

6. ነገር ግን እግዚአብሔር በጻድቅ ፈራጅነቱ ላለፈው ኃጢአታቸው የሚያሳውራቸውና የሚያደነድናቸው[21] ከፋዎችና በእግዚአብሔር የማይታመኑ ሰዎች፤ አእምሮአቸው ብርሃን እንዳይበራሰት፥ በልቦናቸውም እንዳይታደሱ[22] ከነሱ ጸጋውን መንፈግ ብቻ ሳይሆን፥ አንዳንድ ጊዜ ያሏቸውንም ስጦታዎች በመውሰድ[23] በራሳቸው ርኩሰት ቀስቃሽነት ለኃጢአት እንዲጋለጡ ያደርጋል[24]። ከዚህም ጋር ለራሳቸው ምኞት፥ ለዓለም ፈተናና ለሰይጣን ኃይል[25] አሳልፎ ይሰጣቸዋል። እንግዲህ በዚህ ሁኔታ እግዚአብሔር የተመረጡትን ልቦና የሚያለሰልስባቸውን መንገዶች፥ ለእነዚህኛዎቹ ግን በገዛ ራሳቸው አሠራር ለልቦናቸው ማደንደኛ መሣሪያ አድርጎ ይጠቀምባቸዋል[26]።

21. ሮሜ 1፡24፥26፥28፤ 11፡7፥8
22። ዘዳ. 29፡4፤ ማር. 4፡11፥12
23. ማቴ. 13፡12፤ 25፡29፤ የሐዋ. 13፡10፥11
24. ዘፍ. 4፡8፤ 2ኛ ነገ. 8፡12፥13፥ ማቴ. 26፡14–16
25. መዝ. 109፡6፤ ሉቃ. 22፡3፤ 2ኛ ተሰ. 2፡10–12
26. ዘጸ. 8፡15፥32፤ 2ኛ ቆሮ. 2፡15፥16፤ ኢሳ. 8፡14፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡7፥8፤ ዘጸ. 7፡3፤ ኢሳ. 6፡9፥10፤ የሐዋ. 28፡26፥27

7. የእግዚአብሔር ጠቅላላ አስተዳደር ለፍጡሮቹ ሁሉ እንደሚደርስ እንዲሁም ልዩ በሆነ አሠራር የራሱን ቤተ ክርስቲያን ይንከባከባል፤ ሁሉንም ነገሮች ለመልካም እንዲሆኑ ያደርግል[27]።

27. 1ኛ ጢሞ. 4፡10፤ አሞ. 9፡8፤ ማቴ. 16፡18፤ ሮሜ 8፡28፤ ኢሳ. 43፡4፥5፥14

ምዕራፍ ስድስት
ሰው በኃጢአት መውደቁና ቅጣቱ

1. የመጀመሪያ ወላጆቻችን በሰይጣን ተንኮለኛ ፈተናና አታላይነት የተከለከለውን ፍሬ በመብላት ኃጢአት ሠሩ[1]። እግዚአብሔር በጥበበኛውና በቅዱስ ዓላማው ይህን ኃጢአታቸውን ለከብሩ ያውለው ዘንድ ስላቀደ ፈቀደው[2]።

1. ዘፍ. 3፡13፤ 2ኛ ቆሮ. 11፡3
2. ምዕራፍ አምስት አንቀጽ አራትን ይመልከቱ

2. በዚህ ኃጢአት ምክንያት የነበራቸው መሠረታዊ ጽድቅ ተገፈፈ፥ ከእግዚአብሔርም ጋር የነበራቸው ዝምድና ተቋረጠ[3]፥ በኃጢአት ሞቱ[4]፥ በነፍሳቸውና በሥጋቸው በሙሉ በኃጢአት የረከሱ ሆኑ[5]።

3. ዘፍ. 3፡6-8፤ ሮሜ 3፡23
4. ዘፍ. 2፡17፤ ኤፌ. 2፡1-3፤ ሮሜ 5፡12
5. ዘፍ. 6፡5፤ ኤር. 17፡9፤ ቲቶ 1፡15፤ ሮሜ 3፡10-19

3. እነሱም የሰው ሁሉ ስርና መሠረት ስለሆኑ የኃጢአታቸው ፍርድ ከነሱ በተፈጥሮ መንገድ ተወልደው[6] በመጡት ሰዎች ሁሉ ላይ ተቆጠረ[7]። ይህም ፍርድ የኃጢአት ሞትና የባሕርይ በኃጢአት መበከል ነው።

6. የሐዋ. 17፡26፤ ሮሜ 5፡12፥15-19፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡21፥22፥49
7. መዝ. 51፡5፤ ዮሐ. 3፡6፤ ዘፍ. 5፡3፤ ኢዮ. 15፡14

4. ልናመልጥ ከማንችልበት፥ ርኩስና ለመንፈሳዊ ነገር ሙት ከሆነው፥ እንዲሁም በጠቅላላ መጥፎ ሥራ ለመሥራት ካዘነበለውና[9] የመልካም ነገር ሁሉ ተቃራኒ ከሆነው ባሕርያችን፤ የኃጢአት ድርጊቶች ሁሉ ምን ጊዜም ባለማቋረጥ ይፈልቃሉ[10]።

8. ሮሜ 5፡6፤ 7፡18፤ ቆላ. 1፡21
9. ዘፍ. 8፡21፤ ዘፍ. 6፡5፤ ሮሜ 3፡10-12
10. ማቴ. 15፡19፤ ያዕ. 1፡14፥15፤ ኤፌ. 2፡2፥3

5. ይህ የረከሰው ሕይወት በዚህ ሕይወት፤ ዳግም በተወለዱት ዘንድም ይኖራል[11]። ምንም እንኳ በክርስቶስ ምሕረት ቢሰጠውና

ቢገደልም፥ ራሱ የረከሰው ሕይወትም ሆነ ድርጊቶቹ በርግጥና በእውነት ኃጢአት ናቸው[12]።

11. ምሳ. 20፡9፤ መክ. 7፡20፤ ሮሜ 7፡14፥17፥18፥21–23፤ 1ኛ ዮሐ. 1፡8፥10
12. ሮሜ 7፡7፥8፥25፤ ገላ. 5፡17

6. የባሕርይ ወይም የድርጊት ኃጢአት ሁሉ ጻድቅ የሆነውን የእግዚአብሔርን ሕግ የሚተላለፍና የሚቃረን ስለሆነ[13]፥ በራሱ በኃጢአተኛው ላይ በደለኛነትን ያስከትላል[14]። ተላለፊውም ለእግዚአብሔር ቁጣና[15] ለሕጉ ርግማን[16] የተመደበ ይሆናል። ያም ከመንፈሳዊ[17]፥ ከጊዜያዊና[18] ከዘላለማዊ[19] ሥቃይ ጋር ለሞት ተገዥ መሆን ማለት ነው[20]።

13. 1ኛ ዮሐ. 3፡4
14. ሮሜ 2፡15፤ 3፡9፥10
15. ኤፌ. 2፡3
16. ገላ. 3፡10
17. ሮሜ 6፡23
18. ኤፌ. 4፡18
19. ሮሜ 8፡20፤ ሰቆ. 3፡39
20. ማቴ 25፡41፤ 2ኛ ተሰ. 1፡9

ምዕራፍ ሰባት
እግዚአብሔር ከሰው ጋር ያደረገው ቃል ኪዳን

1. በእግዚአብሔርና በፍጡሩ መካከል ያለው ርቀት እጅግ ታላቅ ስለሆነና እንዲሁም አእምሮ ያላቸው ፍጡሮቹ ለሱ ለፈጣሪያቸው የመታዘዝ ግዴታ ስላለባቸው፥ ብፅዕናንና ሽልማትን የሥራቸው ዋጋ አድርገው ከሱ መጠየቅ አይችሉም። ነገር ግን እግዚአብሔር በፈቃደኝነት ራሱን ዝቅ አድርጎ በቃል ኪዳን መንገድ ለመታዘዛቸው ዋጋ ለመስጠት በጎ ፈቃዱ ሆነ[1]።

1. ኢሳ. 40፡13–17፤ ኢዮ. 9፡32፥33፤ መዝ. 113፡5፥6፤ ኢዮ. 22፡2፥3፤ 35፡7፥8፤ ሉቃ. 17፡10፤ የሐዋ. 17፡24፥25

2. እግዚአብሔር በመጀመሪያ ከሰው ጋር ያደረገው ቃል ኪዳን የሥራ ቃል ኪዳን ነበር[2]። በዚህም ቃል ኪዳን በኩል አዳም

በግሉና በሙሉ ለእግዚአብሔር ቢታዘዝ፥ እሱና ዘሩ[3] በሕይወት ሊኖሩ የሕይወትን ተስፋ ተቀበለ[4]።

2. ዘፍ. 2፡16፥17፤ ሆሴ. 6፡7፤ ገላ. 3፡12
3. ዘፍ. 3፡22፤ ሮሜ 10፡5፤ 5፡12–14፤ 5፡15–20
4. ዘፍ. 2፡17፤ ገላ. 3፡10

3. ሰው በኃጢአት ስለወደቀ፥ በዚያ በመጀመሪያው ቃል ኪዳን በኩል ሕይወትን ለማግኘት ባለመቻሉ፥ የሕይወት ቃል ኪዳን የተባለውን ሁለተኛውን ቃል ኪዳን፥ ጌታ በበጎ ፈቃዱ መሠረተ[5]። በዚህም ቃል ኪዳን በኩል ይድኑ ዘንድ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያምኑ በማዘዝ፤ ሕይወትንና ደኅንነትን ለኃጢአተኞች ይሰጣል[6]። እንዲሁም ለዘላለም ሕይወት የተዘጋጁ ሁሉ ፈቃደኛ እንዲሆኑና ማመን እንዲችሉ መንፈስ ቅዱስን እንደሚሰጣቸው ተስፋ ሰጠ[7]።

5. ገላ. 3፡21፤ ሮሜ 3፡20፥21፤ 8፡3፤ ዘፍ. 3፡12
6. ዘፍ. 3፡22፤ ሮሜ 10፡5፥12–14፤ 5፡15–20
7. ዘፍ. 2፡17፥ ገላ. 3፡10

4. ይህ የሕይወት ቃል ኪዳን በመጽሐፍ ቅዱስ የኦዛዜ ቃል ተብሎ ተሰይሟል። ይህም የሆነበት የተናዛዡን የኢየሱስ ክርስቶስን ሞት በማመልከትና በኦዛዜ የሚሰጡትን የዘላለም ውርስ፤ ከውርሱም ጋር አብረው የሚመጡትን ነገሮች ሁሉ በማመልከት ነው[8]።

8. ዕብ. 9፡15–17

5. ይህ የሕይወት ቃል ኪዳን በሕግ ዘመንና በወንጌል ዘመን በተለያየ መንገድ በሥራ ላይ ውሏል[9]። በሕግ ዘመን በተሰፋ ቃል፥ በትንቢት፥ በመሥዋዕት፥ በግርዘት፥ በፋሲካው በግ፥ በሌሎችም ምሳሌዎችና ሥርዓቶች የሚመጣውን ክርስቶስን እንዲያመለክቱ ለአይሁድ ሕዝብ ተሰጠ[10]። እነዚህ ነገሮች ለዚያን ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ አሠራር፥ የተመረጡትን ለማስተማርና በሚመጣው መሲሕ እምነትን ለመገንባት በቂ በመሆን ከንውንን ያስከተሉ ነበሩ[11]። ይህም ሊሆን የቻለው ሙሉ የኃጢአት ይቅርታና የዘላለም ደኅንነትን ወደሚሰጠው ወደሚመጣው መሲሑ በመጠቆም ነበር[12]። ይህ የሕግ አስተዳደር ብሉይ ኪዳን ይባላል።

9. 2ኛ ቆሮ. 3፡6–9
10. ዕብ. 8፡9፥10፥10፤ ሮሜ 4፡11፤ ቆላ. 2፡11፥12፤ 1ኛ ቆሮ. 5፡7

11. 1ኛ ቆሮ. 10፡1-4፤ ዕብ. 11፡13፤ ዮሐ. 8፡56
12. ገላ. 3፡7፥8፥14፤ መዝ. 32፡1፥2፥5

6. የብሉይ ኪዳን ጥላዎች አካል የሆነው ክርስቶስ በተገለጠበት[13] በወንጌል ዘመን ይህ የሕይወት ቃል ኪዳን በሥራ ላይ የሚውለው በቃለ እግዚአብሔር ስብከት፥ በጥምቀትና በቅዱስ ቁርባን ሥርዓት[14] በኩል ነው። እነዚህ ምንም እንኳ ጥቂት፥ ቀላልና አንስተኛ፥ እንዲሁም የውጭ ክብር የሌላቸው ቢሆኑም፤ በእነሱ አማካይነት የበለጠ ሙላት፥ ማረጋገጫና ክንውን[15]፥ ለአይሁድም ለአሕዛብም ይገኛል[16]። ይህም አስተዳደር አዲስ ኪዳን ይባላል[17]። ስለዚህ በመሠረታዊ ትርጉም የሚለያዩ ሁለት የሕይወት ቃል ኪዳኖች ሳይሆኑ፤ ያው አንዱ የሕይወት ቃል ኪዳን በተለያዩ ዘመናት ተሰጥቷል ማለት ነው[18]።

13. ቆላ. 2፡17
14. 1ኛ ቆሮ. 1፡21፤ ማቴ. 28፡19፥20፤ 1ኛ ቆሮ. 11፡23-25
15. ዕብ. 12፡22-24፤ 2ኛ ቆ.ጶ. 3፡9-11፤ ኤር. 31፡33፥34
16. ሉቃ. 2፡32፤ የሐዋ. 10፡34፤ ኤፌ. 2፡15-19
17. ሉቃ. 22፡20
18. ገላ. 3፡8፥9፥14፥16፤ ሮሜ 3፡21፥22፥30፤ 4፡3፥6፥7፥8፤ ዘፍ. 15፡6፤ መዝ. 32፡1፥2፤ ሮሜ 4፡16፥17፥23፥24፤ ዕብ. 4፡2፤ ሮሜ 10፡6-10፤ 1ኛ ቆሮ. 10፡3፥4

ምዕራፍ ስምንት
ስለ መካከለኛው ስለ ክርስቶስ

በሰዎችና በእግዚአብሔር መካከል የቆመ አንድ መካከለኛ ብቻ አለ

1. እግዚአብሔር በዘለዓለማዊ ዓለማው ጌታ ኢየሱስን አንድያ ልጁን፤ በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል መካከለኛ[1] እንዲሁም ነቢይ[2]፥ ካህን[3]፥ ንጉሥ[4]፥ የቤተ ክርስቲያን ራስና አዳኝ[5]፥ የሁሉም ነገር ወራሽና[6] የዓለም ፈራጅ[7] እንዲሆን ለመምረጥና ለመሾም መልካም ፈቃዱ ሆነ። ለእርሱም እግዚአብሔር ከዘላለም ጀምሮ ዘሩ[8] ይሆኑ ዘንድና ዘመኑ ሲደርስ በሱ ይዋጁ፥ ይጸድቁ፥ ይቀደሱና ይከብሩ ዘንድ[9] ሕዝብ ሰጠው።

1. ኢሳ. 42፡1፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡19፥20፤ ዮሐ። 3፡16፤ 1ኛ ጢሞ. 2፡5
2. የሐዋ. 3፡20፥22፤ ዘዳ. 18፡15

3. ዕብ. 5፡5፥6
4. መዝ. 2፡6፤ ሉቃ. 1፡23፤ ኢሳ. 9፡5፥6፤ የሐዋ. 2፡29-36፤ ቆላ. 1፡13
5. ኤፌ. 5፡23
6. ዕብ. 1፡2
7. የሐዋ. 17፡31
8. ዮሐ. 17፡6፤ መዝ. 22፡30፤ ኢሳ. 53፡10፤ ኤፌ. 1፤4
9. 1ኛ ጢሞ. 2፡6፤ ኢሳ. 55፡4፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡30፥ ሮሜ 8፡30

2. የእግዚአብሔር ልጅ ወልድ ራሱ ፍጹምና የዘላለም አምላክ፥ ከአብ ጋር በባሕርይና በመብት እኩል ሆኖ ሳለ፤ ጊዜው ሲድርስ ሰው ሆኖ መጣ።[10] ከኃጢአት በሰተቀር፥ ሙሉ የሰውን ባሕርይ ከነድካሙ ለራሱ ወሰዶ መጣ።[11] በድንግል ማርያም ማኅፀን በመንፈስ ቅዱስ ተፀነሰ፥ ከሷም የሰውን ባሕርይ ወሰደ።[12] ስለዚህ ምንም የማይጎድላቸው ሁለት የአምላክነትና የሰውነት ባሕርዮች አሉት። እነዚህም ባሕርዮች ባለመነጣጠል፥ ባለመከፋፈል፥ ባለመደባላለቅ በአንድነት በአንድ አካል ተዋሕደዋል።[13] ይህም አካል ሙሉ አምላክና ሙሉ ሰው የሆነው ክርስቶስ፤ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለው አንዱ መካከለኛ፥ ወይም የደኅንነት አማላጃችን ነው።[14]

10. ዮሐ. 1፡1፥14፤ 1ኛ ዮሐ. 5፡20፤ ፊል. 2፡6፤ ገላ. 4፡4
11. ፊል. 2፡7፤ ዕብ. 2፡14፥16፥17፤ 4፡15
12. ሉቃ. 1፡27፥31፥35፤ ገላ. 4፡4፤ ማቴ. 1፡18፥20፥21
13. ማቴ. 16፡16፤ ቆላ. 2፡9፤ ሮሜ 9፡5፤ 1ኛ ጢሞ. 3፡16
14። ሮሜ 1፡3፥4፤ 1ኛ ጢሞ. 2፡5

3. ጌታ ኢየሱስ የሰውነት ባሕርዩ ከአምላክነት ባሕርዩ ጋር ስለተዋሐደ፥ የሰውነት ባሕርዩ በመንፈስ ቅዱስ ከመጠን በላይ ተቀድሷል፥ ተቀብቷል።[15] ስለዚህም በውስጡ የጥበብንና የእውቀትን ሁሉ መዝገብ ይዟል።[16] በእርሱም ውስጥ ሙላት ሁሉ ያድር ዘንድ የአብ መልካም ፈቃዱ ሆኖአል።[17] ይህም ስለሆነ ጌታ ቅዱስ፥ የዋህ፥ ገር፥ ንጹህ፥ በጸጋና በእውነት የተሞላ ሆነ።[18] በዚህ ምክንያት የመካከለኝነትንና የዋስትናን ሥራ ለመቀበል ፍጹም ብቃትን አገኘ።[19] ይህንንም ሥልጣን እራሱ ጨብጦ ሳይሆን፥ አብ ሰጥቶታል።[20] አብም ኃይልንና ፍርድን በእጁ ካስረከበው በኋላ፥ ይህን ሥልጣን በሥራ ላይ እንዲያውል አዘዘው።[21]

15. መዝ. 45፡7፤ ዮሐ. 3፡34፤ ኢሳ. 61፡1፤ ሉቃ. 4፡18፤ ዕብ. 1፡8፥9
16. ቆላ. 2፡3

17. ቆላ. 1፡19
18. ዕብ. 7፡26፤ ዮሐ. 1፡14
19. የሐዋ. 10፡38፤ ዕብ. 12፡24፤ 7፡22
20. ዕብ. 5፡4፥5
21. ዮሐ. 5፡22፥27፤ ማቴ. 28፡18፤ የሐዋ. 2፡36

4. ይህንንም ጎላፊነት ከርስቶስ በፈቃደኝነት ተቀበለ።[22] ጎላፊነቱንም ለመፈጸም ከሕግ በታች ሆነ።[23] ሕግንም ምንም ሳያጓድል ለመፈጸም[24] በነፍሱ ታላቅ የጭንቀት መከራን ተቀበለ።[25] በሥጋውም ትላቅ፣ ሥቃይን ተቀበለ፥[26] ተሰቀለ፥ ሞተ፥[27] ተቀበረ። መበስበስን ሳያይ በሞት ሥር ቆየ።[28] በሦስተኛውም ቀን ተነሣ።[29] ከመቃብር የተነሣው ያው ሥቃይ የተቀበለው ሰውነቱ ነው።[30] በዚሁም ሰውነት ወደ ሰማይ አርጎ በአብ ቀኝ ተቀምጧል።[31] በዚሁ ሰውነት ለኛ በማማለድ ላይ ይገኛል።[32] በዚሁ ሰውነት ዳግመኛ ተመልሶ በሰዎች፥ በመላእክትና በዓለም ላይ ይፈርዳል።[33]

22. መዝ. 40፡7፥8፤ ዕብ. 10፡5–10፤ ዮሐ. 4፡34፤ 10፡18፤ ፊል. 2፡8
23. ገላ. 4፡4
24. ማቴ. 3፡15፤ 5፡17፤ ዕብ. 5፡8፥9
25. ማቴ. 26፡37፥38፤ 27፡27–50
26. ማቴ. 26፡60፤ የሐዋ. 20፡24፥27፤ 13፡29፥37፤ ሮሜ 6፡9
27. ማር. 15፡24፥37፤ ፊል. 2፡8
28. ማቴ. 27፡60፤ የሐዋ. 2፡24፥27፤ 13፡29፥37፤ ሮሜ 6፡9
29. 1ኛ ቆሮ. 15፡3፥4
30. ሉቃ. 24፡39፤ ዮሐ. 20፡25፥27
31. ሉቃ. 24፡50፥51፤ 1ኛ ጴጥ. 3፡22
32. ሮሜ 8፡34፤ ዕብ. 7፡25፤ 9፡24
33. የሐዋ. 1፡11፤ ዮሐ. 5፡28፥29፤ ሮሜ 14፡10፤ የሐዋ. 10፡42፤ ማቴ. 13፡40–42፤ ይሁ. 6፤ 2ኛ ጴጥ. 2፡4

5. ጌታ ኢየሱስ ፍጹም በመታዘዙ በዘላለም መንፈስም ራሱን መሥዋዕት አድርጎ አንድ ጊዜ ለእግዚአብሔር በማቅረቡ የአባቱን ፍርድ ፈጽሞ አርከቷል።[34] በዚህም ሥራው እርቅን ማስገኘት ብቻ ሳይሆን በመንግሥተ ሰማይ የዘለዓለምን ርስት ከአብ ለተቀበላቸው ሁሉ አዘጋጅቶላቸዋል።[35]

34. ሮሜ 5፡9፤ ዕብ. 9፡14፤ 10፡14፤ ኤፌ. 5፡2፤ ሮሜ 3፡25፥26
35. ዳን. 9፡24፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡18፤ ቆላ. 1፡20፤ ኤፌ. 1፡11፥14፤ ዕብ. 9፡12፥15፤ ዮሐ. 17፡2

6. ምንም እንኳ የደኅንነት ሥራ የተፈጸመው ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ ከመጣ በኋላ ቢሆንም ነገር ግን ይህ የደኅንነት ሥራ ዋጋው፥ ውጤቱና ጥቅሙ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ለተመረጡት ሁሉ ነው። በዘመናት ሁሉ የተሰጡት የተስፋ ቃሎች፥ ምሳሌዎችና መሥዋዕቶች የነበሩት ዘመኑ ሲደርስ በክርስቶስ ፍጻሜያቸውን ተቀብለዋል። እነዚህም ነገሮች የአባብን ራስ የሚቀጠቅጠው የሴትዮዋ ዘር፤ ዓለም ከተፈጠር ጀምሮ የተሰዋው በግ ትናንትናም ዛሬም ለዘላለምም የማይለወጠው ለመሆኑ ይገልጣሉ፥ ይመስላሉ።[36]

36. ገላ. 4፡4፥5፤ ዘፍጥ. 3፡15፤ 1ኛ ቆሮ. 10፡4፤ ራእ. 13፡8፤ ሮሜ 3፡25፤ ዕብ. 9፡15

7. ክርስቶስ ለእያንዳንዱ ባሕርዩ ተገቢ የሆነውን ሥራ በመፈጸም ለደኅንነት የማማለድ ሥራውን በሁለቱም ባሕርዮቹ ያከናውናል።[37] ሁለቱም ባሕርዮቹ በአንድ አካል ስለተዋሐዱ፥ አንዳንድ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ለአንደኛው ባሕርይ ብቻ ተገቢ የሆነውን ሥራ ለሌላው ባሕርይ በመስጠት፤ ያው አንዱ ክርስቶስ እንደፈጸመው ያመለክታል።[38]

37. ዮሐ. 10፡17፥18፤ 1ኛ ጴጥ. 3፡18፤ ዕብ. 1፡3፤ 9፡14
38. የሐዋ. 20፡28፤ ሉቃ. 1፡43፤ ሮሜ 9፡5

8. ክርስቶስ ደኅንነት ላወጀላቸው ሁሉ ደኅንነትን በርግጥና በማያጠራጥር መንገድ ይሰጣቸዋል።[39] ይህም በማማለድ[40] የደኅንነትን ምሥጢር በቃሉ ውስጥና በቃሉ አማካይነት በመግለጥ፥[41] በመንፈሱ ኃይል እንዲያምኑና እንዲናዘዙ በማድረግ፤ በቃሉና በመንፈሱ ልባቸውን ይገዛል።[42] ለሚያስደንቀው አስተዳደሩ በሚያመች ሁኔታና መንገድ ጠላቶቻቸውን ሁሉ በኃይሉና በጥበቡ ድል ያደርግላቸዋል።[43]

39. ዮሐ. 6፡37፥39፤ 10፡15፥16፥27፥28
40. 1ኛ ዮሐ. 2፡1፤ ሮሜ 8፡34
41. ዮሐ. 15፡15፤ ኤፌ. 1፡9፤ ዮሐ. 17፡6
42. ዮሐ. 14፡26፤ 2ኛ ቆሮ. 4፡13፤ ሮሜ 8፡9፥14፤ 15፡18፥19፤ ዮሐ. 17፡17
43. መዝ. 110፡1፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡25፥26፤ ቆላ. 2፡15፤ ሉቃ. 10፡19

ምዕራፍ ዘጠኝ
የሰው የመምረጥ ችሎታ

የሰውን የመምረጥ ችሎታ እግዚአብሔር ነፃ ስላደረገለት፤ መልካምንም ሆነ ክፉን ለመሥራት አይገደድም፥ ወይም በውጭ ኃይል አይወሰንም።[1]

1. ያዕ. 1፡13፥14፤ ዘዳ. 30፡19፤ ኢሳ. 7፡11፥12፤ ማቴ. 17፡12፤ ዮሐ. 5፡40፤ ያዕ. 4፡7

2. ሰው በኃጢአት ከመውደቁ በፊት መልካሙንና እግዚአብሔር የሚወደውን ለመምረጥና ለማድረግ ችሎታ ነበረው።[2] ሆኖም ይህ ችሎታ ተለዋጭ ስለነበር ሰው በኃጢአት ከወደቀ ሊያጣው የሚችል ነበር።[3]

2. መክ. 7፡29፤ ዘፍ. 1፡26፥31፤ ቆላ. 3፡10
3. ዘፍ. 2፡16፥17፤ 3፡6፥17

3. ሰው በኃጢአት ከወደቀ በኋላ ወደ ደኅንነት የሚመያመራ መንፈሳዊ ነገርን ለመምረጥ ችሎታ ጨርሶ አጣ።[4] ስለዚህ ከዚያ ዓይነት መልካም ነገር ጋር በመቃቃሩና[5] በኃጢአት ሙት በመሆኑ[6]፤ በራሱ ኃይል ራሱን ወደ መልካም ሊመልስ ወይም ሊያዘጋጅ አይችልም።[7]

4. ሮሜ 8፡7፥8፤ ዮሐ. 6፡44፥65፤ 15፡5፤ ሮሜ 5፡5
5. ሮሜ 3፡9፥10፥12፥23
6. ኤፌ. 2፡1፥5፤ ቆላ. 2፡13
7. ዮሐ. 6፡44፥65፤ 3፡3፥5፥6፤ 1ኛ ቆሮ. 2፡14፤ ቲቶ 3፡3–5

4. እግዚአብሔር ሰውን ሊመልሰውና ወደ ጸጋ ስፍራ ሊያመጣው ከተፈጥሮ የኃጢአት ቀንበር ያላቅቀዋል።[8] በጸጋውም ብቻ መንፈሳዊ የሆነውን መልካም ነገር በነፃነት ለመምረጥና ለማድረግ ያስችለዋል።[9] ይህም ሆኖ ግን በውስጡ የኃጢአት ርኩሰት ገና ስላለ፤ መልካሙን ነገር ሁሉ አጠቃሎ አይመርጥም ወይም መጥፎውንም ጨርሶ ከመምረጥ አይቆጠብም።[10]

8. ቆላ. 1፡13፤ ዮሐ. 8፡34፥36፤ ሮሜ 6፡6፥7
9. ፊል. 2፡13፥ ሮሜ 6፡14፥17፥18፥19፥22
10. ገላ. 5፡17፤ ሮሜ 7፡14–25፤ 1ኛ ዮሐ. 1፡8፥10

5. የሰው የመምረጥ ችሎታ ያለመወላወል መልካሙን ነገር ብቻ ለመምረጥ የሚችለው በትንሥኤ ክብርን ሲጎናጸፍ ብቻ ነው።11

11. ዕብ. 12፡23፤ 1ኛ ዮሐ. 3፡2፤ ይሁ. 24፤ ራእ. 21፡27

ምዕራፍ 10
የእግዚአብሔር ልዩ ጥሪ

1. እግዚአብሔር አስቀድሞ ለሕይወት የወሰናቸውን ሁሉ፥ እነሱንም ብቻ፥ ራሱ በወሰነውና ደስ ባለው ወቅት፥ በልዩ ጥሪው ለመጥራት መልካም ፈቃዱ ሆነ።[1] ይህም ጥሪ በቃሉና በመንፈሱ[2] መገሪያነት ነው። በባሕርያቸው ከሚገኙበት ከኃጢአትና ከሞት በኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ጸጋና ወደ ደኅንነት ጠራቸው።[3] የእግዚአብሔርን ነገር እንዲገነዘቡ አእምሮአቸውን ለመንፈሳዊና ለደኅንነት ነገሮች አበራላቸው።[4] የድንጋዩንም ልብ ወስዶ የሥጋን ልብ ሰጣቸው።[5] ፈቃዳቸውን በማደስ፥ በታላቅ ኃይሉ መልካሙን እንዲመርጡ አደረጋቸው።[6] በርግጥም ወደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አቀረባቸው።[7] ይህንንም ሁሉ ሲያደርግላቸው፥ ተገደው ሳይሆን በራሳቸው ምርጫ በጸጋው ፈቃደኛ እንዲሆኑ በማድረግ ነው።[8]

1. የሐዋ. 13፡48፤ ሮሜ 8፡28፥30፤ 11፡7፤ ኤፌ. 1፡5፥11፤ 2ኛ ጢሞ. 1፡9፥10
2. 2ኛ ተሰ. 2፡13፥14፤ ያዕ. 1፡18፤ 2ኛ ቆሮ. 3፡3፥6፤ 1ኛ ቆሮ. 2፡12
3. 2ኛ ጢሞ. 1፡9፥10፤ 1 ጴጥ. 2፡9፤ ሮሜ 8፡2፤ ኤፌ. 2፡1–10
4. የሐዋ. 26፡18፤ 1ኛ ቆሮ. 2፡10፥12፤ ኤፌ. 1፡17፥18፤ 2ኛ ቆሮ. 4፡6
5. ሕዝ. 36፡26
6. ሕዝ. 11፡19፤ ዘዳግም 30፡6፤ ሕዝ. 36፡27፤ ዮሐ. 3፡5፤ ቲቶ 3፡5፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡23
7. ዮሐ. 6፡44፥45፤ የሐዋ. 16፡14
8. መዝ. 110፡3፤ ዮሐ. 6፡37፤ ማቴ. 11፡28፤ ራእ. 22፡17፤ ሮሜ 6፡6–18፤ ኤፌ. 2፡8፤ ፊል. 1፡29

2. ይህ ልዩው ጥሪ የእግዚአብሔር ነፃና ልዩ የሆነ ጸጋ እንጂ፥ አስቀድሞ ከሰው ሊገኝ የሚችል ሆኖ በታየ ነገር ላይ የተመረኮዘ አይደለም።[9] በመንፈስ ቅዱስ ሕይወት እስኪሰጠውና እስከሚታደስ ድረስ ሰው ጥሪውን መቀበል አይችልም።[10] በመንፈስ ቅዱስ ሕይወት ከተሰጠውና ከታደሰ በኋላ ግን ጥሪውን መቀበልና በጥሪው በኩል የተሰጠውን ጸጋ ማቀፍ እንዲችል ይደረጋል።[11]

9. 2ኛ ጢሞ. 1፡9፤ ኤፌ. 2፡8፥9፤ ሮሜ 9፡11
10. 1ኛ ቆሮ. 2፡14፤ ሮሜ 8፡7–9፤ ቲቶ 3፡4፥5
11. ዮሐ. 6፡37፤ ሕዝ. 36፡27፤ 1ኛ ዮሐ. 5፡1፤ 3፡9

3. የተመረጡት ሕፃናት በሕፃንነታቸው ቢሞቱ መቼ፥ የት፥ እንዴት ለመሥራት በፈቃዱ በሚወስነው[12] መንፈስ ቅዱስ በኩል በክርስቶስ ዳግመኛ ተወልደው ይድናሉ።[13] በአካለ ጎደሎነት ምክንያት በቃሉ የሚሰጠውን ጥሪ አድምጠው በማስተዋል መቀበል የማይችሉም ሌሎች የተመረጡ ሰዎች ሁሉ እንዲሁ በተመሳሳይ መንገድ ይድናሉ።[14]

12. ዘፍ. 17፡7፤ ሉቃ. 18፡15፥16፤ የሐዋ. 2፡39፤ ዮሐ. 3፡3፥5፤ 1ኛ ዮሐ. 5፡12፤ ሉቃ. 1፡15
13. ዮሐ. 3፡8
14. ዮሐ. 16፡7፥8፤ 1ኛ ዮሐ. 5፡12፤ የሐዋ. 4፡12

4. ያልተመረጡት ግን በወንጌል ስብከት ቢጋበዙም እንኳ[15]፤ መንፈስ ቅዱስ ዓለምን እንደሚወቅስ ቢወቅሳቸውም[16]፤ በርግጥ ወደ ክርስቶስ ስለማይመጡ ሊድኑ አይችሉም።[1] በተለይ የክርስትናን ሃይማኖት ያልተቀበሉ ሰዎች፤ ምንም እንኳ በተፈጥሮ ብርሃንና በየመረጡት የግል የሃይማኖት ሕጋቸው ሕይወታቸውን ሊመሩ ትጋት ቢያደርጉም፤ ነገር ግን በክርስቶስ ካላመኑ በሰተቀር በሌላ በምንም ዓይነት መንገድ ሊድኑ አይችሉም።[18] እነዚህ ሰዎች ይድናሉ ብሎ ማስተማር በጣም አደገኛ ጉዳት አድራሽና አስጸያፊ ነው።[19]

15. ማቴ. 13፡14፥15፤ የሐዋ. 28፡24፤ 13፡48፤ ማቴ. 22፡14
16. ማቴ. 13፡20፥21፤ 7፡22፤ ዕብ. 6፡4፥5
17. ዮሐ. 6፡37፥64፥65፥66፤ 8፡44፤ 13፡18፤ 17፡12
18. የሐዋ. 4፡12፤ 1ኛ ዮሐ. 4፡2፥3፤ 2ኛ ዮሐ. 9፤ ዮሐ. 14፡6፤ ኤፌ. 2፡12፤ ዮሐ. 4፡22፤ 17፡3፤ ሮሜ 10፡13–17
19. 2ኛ ዮሐ. 9–11፤ 1ኛ ቆሮ. 16፡22፤ ገላ. 1፡6፥7፥8

ምዕራፍ አሥራ አንድ
መጽደቅ

1. እግዚአብሔር በርግጥ ለደኅንነት የጠራቸውን ሁሉ ያጸድቃቸዋል።[1] በውስጣቸው በመሥራት ሳይሆን፤ ኃጢአታቸውን ይቅር በማለት፥ ራሳቸውን እንደ ጻድቅ በመቁጠርና በመቀበል ነው። በውስጣቸው ስለተደረገ ነገር፤ ወይም እነርሱ ባደረጉት ነገር

ሳይሆን ስለክርስቶስ ሲል ብቻ ነው። እምነትን እራሱን ወይም ሌሎች ለወንጌል የሚደረጉትን መታዘዝ እንደጽድቅ በመቁጠር አይደለም፤ ነገር ግን የክርስቶስን መታዘዝና ክርስቶስ የፈጸመውን ጽድቅ ለነሱ በመቁጠር ነው።[2] እነርሱም በእምነት እርሱን በመቀበል፥ በእርሱና በእርሱ ጽድቅ ላይ በማረፍ፥ የእግዚብሔርን ጽድቅ ይቀበላሉ። ይህም እምነት ከራሳቸው የሚገኝ ሳይሆን የእግዚአብሔር ስጦታ ነው።[3]

1. ሮሜ 8፡30፤ 3፡24፤ 5፡15፥16
2. ሮሜ 4፡5–8፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡19፥21፤ ሮሜ 3፡22–28፤ ቲቶ 3፡5፥7፤ ኤፌ. 1፡7፤ ኤር. 23፡6፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡30፥31፤ ሮሜ 5፡17–19
3. ዮሐ. 1፡12፤ የሐዋ. 10፡43፤ 13፡38፥39፤ ፊል. 3፡9፤ ኤፌ. 2፡7፥8፤ ዮሐ. 6፡44፥45፥65፤ ፊል. 1፡29

2. ስለዚህ ክርስቶስን በመቀበልና በክርስቶስ ጽድቅ ላይ በማረፍ ጽድቅን የመቀበያ መሣሪያ የሆነው እምነት ብቻ ነው።[4] ይሁን እንጂ፣ ጽድቅን በሚቀበሉት ሕይወት ውስጥ የሚገኘው እምነት ብቻውን ሆኖ የሞተ እምነት ሳይሆን፥ በፍቅር እየሠራ ሁል ጊዜ በሌሎቹ የደኅንነት ጸጋዎች ይታጀባል።[5]

4. ዮሐ. 3፡18፥36፤ ሮሜ 3፡28፤ 5፡1
5. ያዕ. 2፡17፥22፥26፤ ገላ. 5፡6

3. ክርስቶስ በመታዘዙና በመሞቱ፤ እንዲህ የሚጸድቁትን ሰዎች እዳ በሙሉ በማስወገድ፣ ተገቢ እርግጠኛና ሙሉ የጽድቅ ብድራት በእነሱ ምትክ በማቅረብ፣ የአባቱን ፍርድ አርክቷል።[6] ክርስቶስ ለእነርሱ ብሎ በፈቃደኝነት በአብ ተሰጠ[7]። በእነርሱም ምትክ የእርሱ መታዘዝና የጽድቅ ብድራት በፈቃደኝነት ተቀባይ ሆነ[8]። ስለዚህ ምእመናን መጽደቅ ይሚችሉት ከእነርሱ በተገኘ ነገር ምክንያት ሳይሆን፣ በነፃ በተሰጠ ጸጋ ምክንያት ብቻ ነው።[9] የእግዚአብሔር የጽድቅ ብድራትና የተትረፈረፈው ጸጋው የተሰጠበት ዋናው ዓላማም በኃጢአተኞች መጽደቅ እግዚአብሔር እንዲከበር ነው።[10]

6. ማር. 10፡45፤ ሮም 5፡8–10፥18፥19፤ ገላ. 3፡13፤ 1ኛ ጢሞ. 2፡5፥6፤ ኢዕ. 1፡3፤ 10፡10፥14፤ ዳን. 9፡24፥26፤ ኢሳ. 52፡13–53፡12
7. ሮም 8፡32፤ ዮሐ. 3፡16
8. 2ኛ ቆሮ. 5፡21፤ ኤፌ. 5፡2፤ ፊል. 2፡6–9፤ ኢሳ. 53፡10፥11
9. ሮሜ 3፡24፤ ኤፌ. 1፡7
10. ሮሜ 3፡26፤ ኤፌ. 2፡7፤ ዘካ. 9፡9፤ ኢሳ. 45፡21

4. እግዚአብሔር ከዘለዓለም ጀምሮ የመረጣቸውን ለማጽደቅ አስቀድሞ ወስኗል።[11] ዘመኑ ሲፈጸምም ክርስቶስ ለኃጢአታቸው ሲል ሞቷል። ለጽድቃቸውም ከሙታን ተነሥቷል።[12] ይህ ሁሉ ሆኖ ሳለ፤ በወቅቱ መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስን ለእነርሱ በግላቸው እስኪሰጣቸው ድረስ አይጸድቁም።[13]

11. ሮሜ 8፡29፥30፤ ገላ. 3፡8፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡2፥19፥20
12. ገላ. 4፡4፤ 1ኛ ጢሞ. 2፡6፤ ሮሜ 4፡25
13. ኤፌ. 2፡3፤ ቲቶ 3፡3–7፤ ገላ. 2፡16፤ ቆላ. 1፡21፥22

5. የጸደቁትን ሰዎች ኃጢአት እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ይቅር በማለት ላይ ይገኛል።[14] ምንም እንኳ ከጽድቅ አቋማቸው ፈጽመው መውደቅ ባይችሉም፤[15] እራሳቸውን አዋርደው ኃጢአታቸውን በመናዘዝ ምሕረትን እስኪለምኑ ድረስ፤ እምነታቸውንና ንስሐቸውን እስኪያድሱ ድረስ፤ በኃጢአታቸው ምክንያት በእግዚአብሔር አባታዊ ተግሣጽ ሥር ሊወድቁና የፊቱን ብርሃን ሊያጡ ይችላሉ።[16]

14. ማቴ. 6፡12፤ 1ኛ ዮሐ. 1፡7፥9፤ 2፡1፥2
15. ገላ. 4፡4፤ 1ኛ ጢሞ. 2፡6፤ ሮሜ 4፡25
16. ኤፌ. 2፡3፤ ቲቶ 3፡3–7፤ ገላ. 2፡16፤ ቆላ. 1፡21፥22

6. በእነዚህ ሁሉ ረገድ፤ የብሉይ ኪዳን አማኞችም መጽደቅ ከአዲስ ኪዳን አማኞች መጽደቅ ጋር አንድ ዓይነት ነበር።[17]

17. ገላ. 3፡9፥13፥፥14፤ ሮሜ 4፡6–8፥22–24፤ 10፡6–13፤ ዕብ. 13፡8

ምዕራፍ አሥራ ሁለት
የእግዚአብሔር ልጅነት

1. በጸጋው ያጸደቃቸውን ሁሉ በአንድ ልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት የልጅነትን ጸጋ አንዲቀበሉ ሰጥቷቸዋል።[1] በዚህም የእግዚአብሔር ልጆች ሆኖ መቆጠርና የእግዚአብሔር ልጅነትን መብት ተካፋይ ይሆናሉ።[2] ስሙን ይቀበላሉ፥[3] የልጅነትን መንፈስ ይቀበላሉ፥[4] በድፍረት ወደ ጸጋው ዙፋን ለመግባት ይፈቀድላቸዋል፥[5] እግዚአብሔርን አባ አባት ብለው የመጥራት መብት ይሰጣቸዋል፥[6] እግዚአብሔር ይራራላቸዋል፥[7]

ይንከባከባቸዋል፥[8] የሚያስፈልጋቸውን ይሰጣቸዋል፥[9] እንደ ልጅ በእርሱ ይቀጣሉ[10] እንጂ ፈጽመው አይጣሉም[11]፥ ለመዳንም ቀን ታትመዋል፥[12] የተስፋዎቹ ወራሾች ናቸው[13]፥ የዘላለምንም የደኅንነት ተስፋ ይወርሳሉ።[14]

1. ኤፌ. 1፡5፤ ገላ. 4፡4፥5
2. ሮሜ 8፡17፤ ዮሐ. 1፡12
3. ዘኍ. 6፡24–26፤ ኤር. 14፡9፤ አሞ. 9፡12፤ የሐዋ. 15፡17፤ 2ኛ ቆሮ. 6፡18፤ ራእ. 3፡12
4. ሮሜ 8፡15
5. ኤፌ. 3፡12፤ ዕብ. 4፡16
6. ሮሜ 8፡15፤ ገላ. 4፡6፤ ሮሜ 8፡16
7. መዝ. 103፡13
8. ምሳ. 14፡26
9. ማቴ. 6፡30፥32፤ 1ኛ ጴጥ. 5፡7
10. 12፡6
11. ሰቆ. 3፡31፥32፤ መዝ. 89፡30–35
12. ኤፌ. 4፡30
13. ዕብ. 6፡12
14. 1ኛ ጴጥ. 1፡3፥4፤ ዕብ. 1፡14

ምዕራፍ አሥራ ሦስት
ቅድስና

1. በልብ ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ በሚመጣው በእግዚአብሔር ጥሪ አንድ ጊዜ የተጠሩትና ዳግመኛ የተወለዱት፤ በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ምክንያት፥ በውስጣቸው በሚኖረው መንፈስ ቅዱስና የቃለ እግዚአብሔር አሠራር፥[1] አዲስ ልብና አዲስ መንፈስ በውስጣቸው በእውነት ስለተተከለ[2]፤ የኃጢአት ኃይል ከሕይወታቸው ተሽሯል።[3] ብዙዎች ምኞቶቻቸውም በየጊዜው እየደከሙና እየተገደሉ ናቸው።[4] እነዚህ ምእመናን በየጊዜው በደኅንነት ሕይወት በመጎልመስ ላይ ይገኛሉ።[5] በቅድስና ኑሮ ያድጋሉ፤ ያለቅድስናም ማንም እግዚአብሔርን ሊያይ አይችልም።[6]

1. 1ኛ ተሰ. 5፡23፥24፤ 2ኛ ተሰ. 2፡13፥14፤ ሕዝ. 36፡22–28፤ ቲቶ 3፡5፤ የሐዋ. 20፡32፤ ፊል. 3፡10፤ ሮሜ 6፡5፥6
2. ዮሐ. 17፡17፥19፤ ኤፌ. 5፡26፤ ሮሜ 8፡13፥14፤ 2ኛ ተሰ. 2፡13
3. ሮሜ 6፡6፥14
4. ገላ. 5፡24፤ 8፡13
5. ቆላ.ስ. 1፡10፥11፤ ኤፌ. 3፡16–19

6. 2ኛ ቆሮ. 7፡1፤ ቆላ. 4፡12፤ ዕብ. 12፡14

2. ይህ ቅድስና በጠቅላላ ሙሉውን ሰውናታችንን ይዳስሳል።[7] ይህም ሆኖ ግን በዚህ ሕይወት ፍጹምነትን አናገኝም። የርኩሰት ቅሬታ ከሁለንተናችን ጨርሶ ስለማይጠፋ፤[8] ሥጋ በመንፈስ ላይ፥ መንፈስ በሥጋ ላይ እየተነሣ፣ እርቅ የማያውቀው ጦርነት ሁልጊዜ በሕይወታችን ይካሄዳል።[9]

7. 1ኛ ተሰ. 5፡23፤ ሮሜ 12፡1፥2
8. 1ኛ ዮሐ. 1፡8–10፤ ሮሜ 7፡14–25፤ ፊል. 3፡12
9. ገላ. 5፡17

3. በዚህ ጦርነት ምንም እንኳ የርኩሰት ቅሬታ ለጊዜው ቢያይልም፤[10] ነገር ግን ቅድስናን ከሚሰጠን ከክርስቶስ የማያቋርጥ ጥንካሬ ስለሚፈልቅልን፤ አዲስ የተወለደው የሕይወታችን ክፍል ሁል ጊዜ ድልን ይጎናጸፋል።[11] ስለዚህ ቅዱሳን በእግዚአብሔር ፍርሃት የቅድስናን ሥራ ፍጹም በማድረግ[12] በጸጋ ይጎለምሳሉ።[13]

10. ሮሜ 7፡23
11. 1ኛ ዮሐ. 1፡8–10፤ ሮሜ 7፡14–25፤ ፊል. 3፡12
12. ገላ. 5፡17

ምዕራፍ 14
እምነት፥ የደኅንነት መሣሪያ

1. የተመረጡት ለነፍሳቸው ደኅንነት[1] የደኅንነት መሣሪያ በሆነው እምነት ሊያምኑ የሚችሉት፤ ያ እምነት በክርስቶስ መንፈስ ሥራ በልባቸው ስለተተከለ ነው።[2] ይህም አብዛኛውን ጊዜ በቃሉ አገልግሎት አማካይነት ይሆናል።[3] ይህ እምነት በዚሁ በቃሉ አገልግሎት፥ በጥምቀት፥ በቅዱስ ቁርባንና በጸሎት አማካይነት እየበለጸገ ይመጣል።[4]

1. ቲቶ 1፡1፤ ዕብ. 10፡39
2. 1ኛ ቆሮ. 12፡3፤ ዮሐ. 3፡5፤ ቲቶ 3፡5፤ ዮሐ. 6፡44፥45፤ ኤፌ. 2፡8፤ ፊል. 1፡29፤ 2ኛ ጴጥ. 1፡1፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡2
3. ማቴ. 28፡19፥20፤ ሮሜ 10፡14፥17፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡21
4. 1ኛ ጴጥ. 2፡2፤ የሐዋ. 20፡32፤ ሮሜ 1፡16፥17፤ ማቴ. 28፡19፤ የሐዋ. 2፡38፤ 1ኛ ቆሮ. 10፡16፤ 1ኛ ቆሮ. 11፡23–29፤ ሉቃ. 17፡5፤ ፊል. 4፡6፥7

2. ከርስቲያን የራሱ የእግዚአብሔር ሥልጣን በውስጡ ስለሚያስተጋባለት5፥ በዚህ እምነት በቃሉ የተጻፈውን ሁሉ ይጨብጣል። ለትእዛዛቱ በመገዛት፥6 የቃሉን ማስጠንቀቂያ በፍርሃት በመጠበቅ፥7 ለዚህ ሕይወትና ለሚመጣው ሕይወት በቃሉ የተሰጠውን የእግዚአብሔርን ተስፋ በመመርኮዝ8፥ ቃሉ በሚሰጠው መምሪያ በሠረት እርምጃውን ይቀይሳል። ሆኖም ዋናዎቹ የእምነት ተግባሮች መቀበል፥ መረከብ፥ ለጽድቅና ለቅድስና እንዲሁም ለዘላለም ሕይወት በጸጋ ቃል ኪዳን መሠረት በክርስቶስ ላይ ብቻ መደገፍ ናቸው።9

5. 2ኛ ጴጥ. 1፡20፥21፤ ዮሐ. 4፡42፤ 1ኛ ተሰ. 2፡13፤ 1ኛ ዮሐ. 5፡9፥10፤ የሐዋ. 24፡14
6. መዝ. 119፡10፥11፤48፥97፥98፥167፥168፤ ዮሐ. 14፡15
7. እዝ. 9፡4፤ ኢሳ. 66፡2፤ ዕብ. 4፡1
8. ዕብ. 11፡13፤ 1ኛ ጢሞ. 4፡8
9. ዮሐ. 1፡12፤ የሐዋ. 16፡31፤ ገላ. 2፡20፤ የሐዋ. 15፡11፤ 2ኛ ጢሞ. 1፡9፥10

3. የእምነት ደካማነት ወይም ጠንካራነት በየጊዜው የተለያየ ሊሆን ይችላል፤10 ብዙ ጊዜም በልዩ ልዩ መንገድ በመጎሰም ይደክማል፤ ግን ያሸንፋል።11 በሕይወታችንም እየጎለመስን፣ የእምነታችን ጅማሪና ፈጻሚ በሆነው በክርስቶስ ሙሉ እርግጠኛነትን ለመጎናጸፍ12፤ እምነታችን ከጊዜ ወደ ጊዜ ያድጋል።13

10. ዕብ. 5፡13፥14፤ ሮሜ 14፡1፥2፤ ማቴ. 6፡30፤ ሮሜ 4፡19፥20፤ ማቴ. 8፡10
11. ሉቃ. 22፡31፥32፤ ኤፌ. 6፡16፤ 1ኛ ዮሐ. 5፡4፥5
12. ዕብ. 6፡11፥12፤ 10፡22፤ ቆላ. 2፡2
13. ዕብ. 12፡2

ምዕራፍ አሥራ አምስት
ወደ ሕይወት የሚመራው ንስሐ

1. ወደ ሕይወት የሚመራው ንስሐ፤ የወንጌል ጸጋ ነው።1 ስለዚህ ይህ የንስሐ ትምሕርትና እንዲሁም በክርስቶስ የማመን ትምህርት፣ በወንጌል ሰባኪዎች ሁሉ ሊሰጡ ይገባቸዋል።2

1. የሐዋ. 11፡18፤ 2ኛ ቆሮ. 7፡10፤ ዘካ. 12፡10

2. ሉቃ. 24፡47፤ ማር. 1፡5፤ የሐዋ. 20፡21

2. በዚህ ንስሐ ኃጢአተኛ አደጋን በማየትና በመፍራት ብቻ ሳይሆን፥ ነገር ግን ከኃጢአቱም እድፈትና አስጸያፊነት የተነሣ፤ ኃጢአቱም ከእግዚአብሔር ቅዱስ ባሕርይ ጋር ስለማይገጥምና ከእግዚአብሔር ቅዱስ ሕግ ጋር ስለሚቃረን፤ በኃጢአቱ ተጸጸቶ፥ ኃጢአቱን ጠልቶ፥ ወደ እግዚአብሔር ተመልሶ[3] ከእርሱ ጋር በትእዛዛቱ ሁሉ ለመራመድ የሚወስንበትና የሚጣጣርበት መንገድ ነው።[4]

3. ሕዝ. 18፡30፥31፤ ኢሳ. 30፡22፤ መዝ. 51፡4፤ ኤር. 31፡8፥19፤ ኢዩ. 2፡12፥13፤ አሞ. 5፡15፤ መዝ. 119፡128፤ 2ኛ ቆሮ. 7፡11፤ 1ኛ ተሰ. 1፡9
4. መዝ. 119፡6፥59፥106፤ 2ኛ ነገ. 23፡23፡25፤ ሉቃ. 1፡6

3. ንስሐ መግባት ምንም እንኳ ኃጢአትን የሚከፍል የኃጢአት ዋጋ ነው ተብሎ ባይደገፉበትም[5]፥ ወይም በክርስቶስ በኩል የሚሰጥ የእግዚአብሔር የነፃ የጸጋው ስጦታ የሆነውን የኃጢአትን ይቅርታ የማግኛ ዋጋ ባይሆንም[6]፥ ያለንስሐ ማንም ሰው የኃጢአትን ምሕረት እቀበላለሁ ብሎ ማሰብ አይገባውም።[7]

5. ሕዝ. 36፡31፥32፤ 16፡61–63፤ ኢሳ. 43፡25
6. ሆሴ. 14፡2፥4፤ ሮሜ 3፡24፤ ኤፌ. 1፡7
7. ሉቃ. 13፡3፥5፤ ማር. 1፡4፤ የሐዋ. 17፡30፥31

4. ኃጢአት ሁሉ ፍርድ ስለሚገባው የኃጢአት ትንሽ የለውም።[8] እንዲሁም በእውነት ንስሐ ለሚገቡት ትልቅ ከመሆኑ የተነሣ ምሕረት የሌለው ኃጢአት የለም።[9]

8. ሮሜ 6፡23፤ ገላ. 3፡10፤ ማቴ። 12፡36
9. ኢሳ. 55፡7፤ ሮሜ 8፡1፤ ኢሳ. 1፡16–18

5. ሰዎች ባጠቃላይ ብቻ ስለ ኃጢአታቸው ንስሐ መግባት በቂ እንዳልሆነ መረዳት አለባቸው። ሰው በእያንዳንዱ ኃጢአቱ በዝርዝር ንስሐ መግባት አለበት።[10]

10. መዝ. 19፡13፤ ማቴ. 26፡75፤ ሉቃ. 19፡8፤ 1ኛ ጢሞ. 1፡13፥15

6. ምሕረትን ለማግኘት በመጸለይ እያንዳንዱ ሰው ኃጢአቱን በግሉ ለእግዚአብሔር መናዘዝ አለበት።[11] ንስሐ ስለሚገባና ኃጢአቱን ስለሚናዘዝ፥ ምሕረትን ይቀበላል።[12] እንዲሁም

ወንድሙንና የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን የሚያሰድብ፤ በግል ወይም በይፋ የፈጸመውን ኃጢአት ለመናዘዝና ስለ ኃጢአቱ ለማዘን፥ በኃጢአቱም ላስቀየማቸው ንስሐውን ለመግለጽ ፈቃደኛ መሆን አለበት።[13] የተበደሉትም ከሱ ጋር ሊታረቁና በፍቅር ሊቀበሉት ይገባል።[14]

11. መዝ. 32፡5፥6፤ 51፡1–14
12. ምሳ. 28፡13፤ ኢሳ. 55፡7፤ 1ኛ ዮሐ. 1፡9
13. ያዕ. 5፡16፤ ሉቃ. 17፡3፥4፤ ኢያ. 7፡19፤ ማቴ. 18፡15–18
14. 2ኛ ቆሮ. 2፡7፥8፤ ገላ. 6፡1፥2

ምዕራፍ አሥራ ስድስት
ጥሩ ሥራ

1. ጥሩ ሥራ የሚባሉት እግዚአብሔር በቅዱስ ቃሉ ያዘዛቸው ነገሮች ብቻ[1] እንጂ፤ ሰዎች በጭፍን ስሜት ተነሣሰተውና «ጥሩ ላድርግ ባይ» ሆነው ያለ እግዚአብሔር ሥልጣን፥ እንዲሁ የደነገጓቸው ነገሮች አይደሉም።[2]

1. ሚክ. 6፡8፤ ሮሜ 12፡2፤ ዕብ. 13፡21
2. ማቴ. 15፡9፤ ኢሳ. 29፡13፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡18፤ ዮሐ. 16፡2 ሮሜ 10፡2፤ 1ኛ ሳሙ. 15፡21–23፤ ዘዳ. 10፡12፥13፤ ቆላ. 2፡16፥17፥20–23

2. የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመጠበቅ የሚደረጉ ጥሩ ሥራዎች የእውነተኛና የሕያው እምነት ፍሬዎችና ማስረጃዎች ናቸው።[3] በነዚህ ጥሩ ሥራዎች አማካይነት አማኞች ምስጋናቸውን ይገልጻሉ፥[4] ደኅንነታቸውን ያረጋግጣሉ፥[5] የሃይማኖት ባልደረቦቻቸውን ያበረታታሉ፥[6] ሃይማኖታቸውን ያስጌጣሉ፥[7] የተቃዋሚዎችን አፍ ያዘጋሉ፥[8] መልካም ሥራ እንዲሠሩ በክርስቶስ ያዘጋጃቸውን[9] እግዚአብሔርን ያከብራሉ፥[10] በቅድስና ፍሬ ተካፋዮች በመሆን የዘላለምን ሕይወት ይወርሳሉ።[11]

3. ያዕ. 2፡18፥22፤ ቆላ. 3፡15–17፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡9
4. መዝ. 116፡12–14፤
5. 1ኛ ዮሐ. 2፡3፥5፤ 2ኛ ጴጥ. 1፡5–10
6. 2ኛ ቆሮ. 9፡2፤ ማቴ. 5፡16፤ 1ኛ ጢሞ. 4፡12
7. ቲቶ 2፡5፥9–12፤ 1ኛ ጢሞ. 6፡1
8. 1ኛ ጴጥ. 2፡15
9. ኤፌ. 2፡10

10. 1ኛ ጴጥ. 2፡12፤ ፊል. 1፡11፤ ዮሐ. 15፡8
11. ሮሜ 6፡22

3. አማኞች ጥሩ ሥራ ለመሥራት ችሎታቸው ፈጽሞ ከራሳቸው ሳይሆን በጠቅላላው ከክርስቶስ መንፈስ ስለሆነ፤[12] ከተቀበሉት ጸጋ በተጨማሪ ስለበጎ ፈቃዱ፥ መፈለግንም ማድረግንም በውስጣቸው የሚሠራው የመንፈስ ቅዱስ መገፋፋት ያስፈልጋቸዋል።[13] ይህም ሆኖ ግን፥ በውስጣቸው ያለውን የእግዚአብሔርን ጸጋ በመቀስቀስ መትጋት ይገባቸዋል እንጂ፥ የመንፈስ ቅዱስ ልዩ መገፋፋት ካልተሰማቸው መልካም ሥራን የመሥራት ግዴታ የሌለባቸው ይመስል፥ ቸልተኛ መሆን የለባቸውም።[14]

12. ዮሐ. 15፡4–6፤ ሮሜ 8፡4–14፤ ሕዝ. 36፡26፥27
13. ፊል. 2፡13፤ 4፡13፤ 2ኛ ቆሮ. 3፡5፤ ኤፌ. 3፡16
14. ፊል. 2፡12፤ ዕብ. 6፡11፥12፤ 2ኛ ጴጥ. 1፡3፥5፥10፥11፤ ኢሳ. 64፡7፤ 2ኛ ጢሞ. 1፡6፤ የሐዋ. 26፡6፥7፤ ይሁ. 20፥21

4. በዚህ ሕይወት ሊደረስበት ከሚቻለው የመታዘዝ ከፍታ የሚደርሱ እግዚአብሔር ከሚጠብቅባቸው አትርፈው መሥራት ቀርቶ፥ ሊፈጽሙ የሚገባቸውን ግዴታቸውን እንኳ አያሟሉም።[15]

15. ሉቃ. 17፡10፤ ነህ. 13፡22፤ ሮሜ 8፡21–25፤ ገላ. 5፡17

5. በኛ መልካም ሥራና በዘላለም ሕይወት ከብር መካከል፤ እንዲሁም በእኛና በእግዚአብሔር መካከል በሚዛን ሊገመት የማይቻል የክብር መራራቅ ስለ አለ፤ ምርጥ በሆኑት መልካም ሥራዎቻችን የኃጢአትን ሥርየት ወይም የዘላለምን ሕይወት ከእግዚአብሔር እጅ ልንገዛ አንችልም። በመልካም ሥራዎቻችንም እግዚአብሔርን ልንጠቅመው ወይም በዳላችንን ይቅር እንዲሰን ልንደልለው አንችልም።[16] እነዚህንም መልካም ሥራዎች ሠርተን በተገኘን ጊዜ፥ የሚገባንን ብቻ የፈጸምን የማንጠቅም ባሪያዎች ነን።[17] ይህም ሁሉ የሆነበት ምክንያት መልካም ሥራዎቻችን ሁሉ ከእርሱው መንፈስ ስለሚመነጩና[18] በእኛ እስከተፈጸሙም ድረስ ከድካምና ካለመብቃት ጋር ተቀላቅለው ስለሚረክሱ፥ የእግዚአብሔርን ጥብቅ ሚዛን ሊቋቋሙ ባለመቻላቸው ነው።[19]

16. 16. ሮሜ 3፡23፤ 4፡2፥4፥6፤ 8፡18፥22–24፤ ኤፌ. 2፡8፥9፤ ቲቶ 3፡5–7፤ መዝ. 16፡2፤ ኢዮ. 22፡2፥3፤ 35፡7፥8
17. ሉቃ. 17፡10
18. ሮሜ 8፡13፥14፤ ገላ. 5፡22፥23

19. ኢሳ. 64፡6፤ ገላ. 5፡17፤ ሮሜ 7፡15፥18፤ መዝ. 143፡2፤ 130፡3

6. ይህም ሆኖ ሳለ ግን፥ እግዚአብሔር አማኞችን በክርስቶስ በኩል ስለተቀበላችው፥ መካልም ሥራዎቻቸውንም በእርሱው ምክንያት ይቀበልላቸዋል።[20] በዚህ ሕይወት እስካለን ድረስ፥ መልካም ሥራዎቻችን ምንም ነቀፋ የሌለባቸውና በእግዚአብሔር ፊት ተግሣጽ የማይገኝባቸው ሆነው ሳይሆን[21]፤ እሱ በልጁ ውስጥ እንዳሉ ተመልከቶ፥ ከልብ የተፈጸሙትን ሊቀበላቸው በጎ ፈቃዱ ስለሆነ ብቻ ነው።[22]

20. ኤፌ. 1፡6፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡5፤ ዘጸ. 28፡38፤ ዘፍ. 4፡4፤ ዕብ. 11፡4
21. ኢዮ. 9፡20፤ መዝ. 143፡2፤ 1ኛ ዮሐ. 1፡8
22. ዕብ. 13፡20፥21፤ 6፡10፤ 2ኛ ቆሮ. 8፡12፤ ማቴ. 25፡21፥23፤ 1ኛ ቆሮ. 3፡14፤ 4፡5

7. ዳግም ባልተወለዱ ሰዎች የሚሠሩ ጥሩ ሥራዎች ምንም እንኳ ሥራዎቹ እግዚአብሔር በቃሉ እንዳዘዛቸውና እንዲሁም ፍሬአቸውም እነርሱንና ሌሎችን ጠቃሚ ቢሆኑም፤[23] ነገር ግን በእምነት ከተቀደሰ ልብ ስለማይመነጩና[24] በትክክለኛ መንገድ እንደቃሉ ስለማይፈጸሙ[25]፤ ዓላማቸውም ለእግዚአብሔር ክብር ስላልሆነ[26]፤ ፍጹም የረከሱና እግዚአብሔርን የማያስደስቱ፥ ለሠሪውም ከእግዚአብሔር ጸጋን የማያስገኙ ናቸው።[27] ይህም ሆኖ ግን እነዚህን ሥራዎች አለመፈጸም፥ የባሰ ኃጢአትና እግዚአብሔርን አስከፊ ነው።[28]

23. 2ኛ ነገ. 10፡30፥31፤ 1ኛ ነገ. 21፡27፥29፤ ሉቃ. 18፡2–7፤ ሮሜ 13፡4
24. ዕብ. 11፡4፥6፤ ዘፍ. 4፡3–5
25. 1ኛ ቆሮ. 13፡3፤ ኢሳ. 1፡12
26. ማቴ. 6፡2፥5፥16፤ 1ኛ ቆሮ. 10:31
27. ምሳ. 21፡27፤ ሐጌ 2፡14፤ ቲቶ 1፡15፤ 3፡5፤ አሞ. 5፡21፥22፤ ማር. 7፡6፥7፤ ሆሴ. 1፡4፤ ሮሜ 9:16
28. መዝ. 14፡4፤ 36፡3፤ ማቴ. 25፡41–45፤ 23፡23፤ ሮሜ 1፡21–32

LAPSLEY / BROOKS FOUNDATION, INC.
1701 N. GREENVILLE AVE. ST. 810
RICHARDSON, TEXAS 75081, USA

ምዕራፍ አሥራ ሰባት
እስከ መጨረሻ ጸንቶ መቆም

1. እግዚአብሔር በሚወደው ልጁ የተቀበላቸው፥ በልዩ የመንፈስ ቅዱስ ጥሪ በልቦናቸው ጥሪውን ያስቀመጠላቸው፥ በመንፈሱ የቀደሳቸው፣ ፈጽመው ወይም እስከ መጨረሻው ከጸጋው አቋም ሊወድቁ አይችሉም፤ ነገር ግን በእርግጥ እስከ ፍጻሜ ይጸናሉ፥ ለዘላለምም ደኅንነት ይጠበቃሉ።[1]

1. ፊል. 1፡6፤ 2ኛ ጴጥ. 1፡10፤ ሮሜ 8፡28–30፤ ዮሐ. 10፡28፥29፤ 1ኛ ዮሐ. 3፡9፤ 1ኛ ዮሐ. 5፡18፤ 1ኛ ጴጥ. 1፥5፥9

2. ይህ እስከ ፍጻሜ መጽናታቸው በራሳቸው ምርጫ ላይ የተመረኮዘ አይደለም፤ ነገር ግን በማይለወጠው በአብ ፍቅር፥[2] ተሰሚነት ባለው በኢየሱስ ክርስቶስ አማላጅነት፥[3] በውስጣቸው በሚኖረው መንፈስ ቅዱስ፥ በውስጣቸው ካለው በእግዚአብሔር ዘርና[4] ከሕይወት ቃል ኪዳን በሚመነጨው በማይሻረው በእግዚአብሔር የምርጫ ውሳኔ ላይ የተመረኮዘ ነው።[5] የደኅንነታቸው እርግጠኛነትና አለመለውጥም ከዚሁ የተነሣ ነው።[6]

2. መዝ. 89፡3፥4፥28–33፤ 2ኛ ጢሞ. 2፡18፥19፤ ኤር. 31፡3
3. ዕብ. 10፡10፥14፤ 13፡20፥21፤ 9፡12–15፤ 7፡25፤ ሮሜ 8፡33–39፤ ዮሐ. 17፡11፥24፥ ሉቃ. 22፡32
4. ዮሐ. 14፡16፥17፤ 1ኛ ዮሐ. 2፡27፤ 3፡9
5. ኤር. 32፡40፤ 31፡31–34፤ መዝ. 89፡34–37
6. ዮሐ. 6፡38–40፤ 10፡28፤ 2ኛ ተሰ. 3፡3፤ 1ኛ ዮሐ. 2፡19

3. ይህም ሆኖ ግን በሰይጣን ፈተና፥ በዓለም አባባይነት፥ በውስጣቸው በቀረው የርኩሰት ግየልና ጽናትን የሚሰጧቸውን የጸጋ መሣሪያዎች ችላ ከማለት የተነሣ፣ በመጥፎ ኃጢአቶች ሊወድቁ ይችላሉ።[7] ለተወሰነ ጊዜም በነዚህ ኃጢአቶች ሊቆዩ ይችላሉ።[8] በዚህም ምክንያት እግዚአብሔርን ሊያሳቀይሙ፥[9] መንፈስ ቅዱስን ሊያሳዝኑ፥[10] አንዳንዶቹን ጸጋዎቻቸውንና መጽናናታቸውን ሊያጡ፥[11] ልባቸው እንዲደነድን ሊያደርጉ፥[12] ሕሊናቸውን ሊያቆስሉ፥[13] ሌሎችን ሊበድሉና ሊያሰድቡ፥[14] በራሳቸውም ላይ ጊዜያዊ ፍርድን ሊያስከትሉ ይችላሉ።[15]

7. ዘጸ. 32፡21፤ ዮና. 1፡3፥10፤ መዝ. 51፡14፤ ማቴ. 26፡70፥72፥74
8. 2ኛ ሳሙ. 12፡9፥13፤ ገላትያ 2፡11–14
9. ዘኁ. 20፡12፤ 2ኛ ሳሙ. 11፡27፤ ኢሳ. 64፡7፥9

10. ኤፌ. 4፡30
11. መዝ. 51፡8+10+12፤ ራእ. 2፡4፤ ማቴ. 26፡75
12. ኢሳ. 63፡1
13. መዝ. 32፡3+4፤ 51፡8
14. ዘፍ. 12፡10-20፤ 2ኛ ሳሙ. 12፡14፤ ገላ. 2፡13
15. መዝ. 89፡31+32፤ 1ኛ ቆሮ. 11፡32

ምዕራፍ አሥራ ስምንት
ጸጋና የደኅንነት ዋስትና

1. ግብዞችና ዳግመኛ ያልተወለዱ ሰዎች በክንቱ ተስፋና በሥጋዊ ድፍረት እግዚአብሔር ታርቆናል ወይም ደኅንነትን አግኝተናል ብለው ቢገምቱም ቅሉ፤[1] መጨረሻቸው ጥፋት ብቻ ሲሆን፤[2] ነገር ግን በእርግጥ በጌታ ኢየሱስ የሚያምኑት፥ ከልባቸው የሚያፈቅሩትና በመልካም ሕሊና በፊቱ ለመኖር የሚጥሩት፤ እነሱ ብቻ በዚህ ሕይወት ሳሉ በጸጋው ውስጥ እንዳሉ እርግጠኛ ሊሆኑና[3] በእግዚአብሔርም ከብር ተስፋ ፍስሐ ሊያደርጉ ይችላሉ። ይህም ተስፋ በፍጹም አያሳፍራችውም።[4]

1. ሚክ. 3፡11፤ ዘዳ. 29፡19፤ ዮሐ. 8፡41
2. አሞ. 9፡10፤ ማቴ. 7፡22+23
3. 1ኛ ዮሐ. 5፡13፤ 2፡3፤ 3፡14+18+19+21+24
4. ሮሜ 5፡2+5

2. ይህ እርግጠኝነት በባዶ ግምትና በምናልባት እምነት ላይ የተመሠረተ ከንቱ ተስፋ ሳይሆን፤[5] በእግዚአብሔር እውነተኛ ቃል፥ በተሰጠን የደኅንነት ተስፋ ላይ የተመረኮዘ፣ የማይናወጥ የእምነት እርግጠኝነት ነው።[6] የእምነት እርግጠኝነት በተጨማሪም በተስፋው በተሰጡት በልቦናችን በሚገኙ የጸጋ ፍሬዎችና[7] የእግዚአብሔር ልጆች ለምሆናችን ከመንፈሳችን ጋር በሚመሰክርልን በልጅነት መንፈስ ምስክርነት ላይ የተመረኮዘ ነው።[8] ይህም መንፈስ ለቤዛ ቀን የታተምንበት የርስታችን መያዣ ነው።[9]

5. ዕብ. 6፡11+19
6. ዕብ. 6፡17+18
7. 2ኛ ጴጥ. 1፡4-15+16
8. ሮሜ 8፡15+16
9. ኤፌ. 1፡13+14፤ 4፡30፤ 2ኛ ቆሮ. 1፡21+22

3. ይህ የደኅንነት እርግጠኛነት ደኅንነትን ከሚያስገኝልን እምነት ጋር የተቆራኘ ስላይደለ፣ እውነተኛ አማኝ ይህን እርግጠኝነት ከማግኘቱ በፊት፣ ለብዙ ጊዜ ሊጠብቅና ከብዙ ችግሮች ጋር መዋጋት ይኖርበት ይሆናል።[10] ነገር ግን አማኙ ከእግዚአብሔር በነፃ የተሰጡትን በረከቶች ለማወቅ በመንፈስ ቅዱስ በመመራት ልዩ እርግጠኝነት ሊጎናጸፍ ይችላል።[11] ስለዚህ መጠራቱንና መመረጡን ማጽናት፣ የእያንዳንዱ አማኝ ግዴታ ነው።[12] በዚህም መሠረት በሰላምና በመንፈስ ቅዱስ ደስታ፥ በእግዚአብሔር ፍቅርና ምስጋና፥ በመታዘዝ ግዴታው፥ በጥንካሬና በደስተኛነት ልቡ ይሞላ ዘንድ ነው።[13] እንግዲህ የዚህ እርግጠኛነት ትክክለኛ ፍሬ ሰዎችን ወደ ስንፍና ከመምራት ፈጽሞ የራቀ መሆኑ ግልጽ ነው።[14]

10. 1ኛ ዮሐ. 5፡13
11. 1ኛ ቆሮ. 2፡12፤ 1ኛ ዮሐ. 4፡13፤ ዕብ. 6፡11፥12፤ ኤፌ. 3፡17፥18
12. 2ኛ ጴጥ. 1፡10
13. ሮሜ 5፡1፥2፥5፤ 14፡17፤ 15፡13፤ ኤፌ. 1፡3፥4፤ መዝ. 4፡6፥7፤ 119፡32
14. 1ኛ ዮሐ. 2፡1፥2፤ 3፡2፥3፤ 1፡6፥7፤ ሮሜ 6፡1፥2፤ ቲቶ 2፡11፥12፥14፤ 2ኛ ቆሮ. 7፡1፤ ሮሜ 8፡1፥12፤ መዝ. 130፡4፤

4. እርግጠኛነታቸውን ባለመንከባከብ፥ ሕሊናን በሚያቆስልና መንፈስን በሚያሳዝን በአንድ ዓይነት ልዩ ኃጢአት በመውደቅ፥ በድንገተኛና በከፉ ፈተና በመመታት፥ እግዚአብሔር ከሚፈሩት እንኳ በጭለማና ያለብርሃን ይራመዱ ዘንድ፣ የፊቱን ብርሃን በመንሳቱ፤ በነዚህና እነዚህን በመሳሰሉት ምክንያቶች እውነተኞች አማኞች የደኅንነት እርግጠኛነታቸው ሊነቃነቅባቸው፥ ሊመነምንባቸው፥ ሊያቋርጥባቸው ይችላል።[15] ይህም ቢሆን እንኳ የእግዚአብሔር ዘር፥ የእምነት ሕይወት፥ ያ የክርስቶስና የክርስቲያን ወንድሞች ፍቅር፥ ያ የልባቸው እውነተኛነትና የኃላፊነት ግዴታ፣ ከሕይወታቸው ፈጽሞ አይጠፉም። በነዚህም አማካይነትና በመንፈስ ቅዱስ ሠራተኛነት፣ ይህ የመዳን እርግጠኛነት ከጊዜ በኋላ ሊታደስላቸው ይችላል።[16] እስኪታደሰላቸውም ድረስ፣ ፈጽመው ተስፋ ከመቁረጥ በነዚህ ነገሮች ይጠበቃሉ።[17]

15. መዝ. 51፡8፥12፥14፤ 77፡1–10፤ 31፡22፤ ኤፌ. 4፡30፥31፤ ማቴ. 26፡69–72፤ ሉቃ. 22፡31–34
16. 1ኛ ዮሐ. 3፡9፤ ሉቃ. 22፡32፤ መዝ. 51፡8፥12፤ 73፡15
17. ሚክ. 7፡7–9፤ ኤር. 32፡40፤ ኢሳ. 54፡7–14፤ 2ኛ ቆሮ. 4፡8–10

ምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ
የእግዚአብሔር ሕግ

1. እግዚአብሔር ለአዳም ሕግን የሥራ ቃል ኪዳን አድርጎ ሰጠው። በዚህም ሕግ እርሱንና ዘሩን በግል፥ በሙሉ፥ በትክክል፤ ሁልጊዜ ይታዘዙ ዘንድ አሰራቸው። ሕጉንም ቢጠብቅ የዘላለምን ሕይወት ሊቀበል፤ ቢተላለፍ ግን ሞትን ሊቀበል ነበር። ከዚህም ጋር አብሮ ሕጉን የመጠበቅ ኃይልና ችሎታ ሰጠው።[1]

1. ዘፍ. 1፡26፥27፤ 2፡17፤ ኤፌ. 4፡24፤ ሮሜ 2፡14፥15፤ 10፡5፤ 5፡12፥19፤ ገላ. 3፡10፥12፤ መክ. 7፡29

2. ይህ ሕግ ሰው በኃጢአት ከወደቀም በኋላ ትክክለኛ የጽድቅ መለኪያ ሆኖ ቆየ። እንዲህም ስለሆነ፤ በሲና ተራራ ላይ በአሥር ትእዛዛትና በሁለት ጽላት ላይ ተጽፎ በእግዚአብሔር ተሰጠ።[2] የመጀመሪያዎቹ አራቱ ትእዛዛት ለእግዚአብሔር ያለንን ግዴታ ሲገልጹ፤ የቀሩት ስድስቱ ለሰው ያለንን ግዴታ ይገልጻሉ።[3]

2. ያዕ. 1፡25፤ 2፡8፥10-12፤ ሮሜ 3፡19፤ 13፡8፥9፤ ዘዳ. 5፡32፤ 10፡4፤ ዘጸ. 34፡1
3. ዘጸ. 20፡3-17፤ ማቴ. 22፡37-40

3. የሥነ ምግባር ሕግ ከሆኑት ከነዚህ ከአሥሩ በተጨማሪም፥ እግዚአብሔር ገና ላልነለመሰችው ቤተ ክርስቲያን (ለእስራኤል ሕዝብ) ልዩ ልዩ ምሳሌ ያዘሉ የሥነ ሥርዓት ሕግጋት ሰጣቸው። እነዚህም የሥነ ሥርዓት ሕግጋት በከፊል ክርስቶስን፥ ጸጋውን፥ ሥራውን፥ ሥቃዩን፥ በረከቱን ሲያመለክቱ፤[4] በከፊል ደግሞ የተለያዩ የሥነ ምግባር ትምህርቶችን ያዘሉ ናቸው።[5] አሁን በአዲስ ኪዳን እነዚህ የሥነ ሥርዓት ሕግጋት በሙሉ በመፈጸም ተወግደዋል።[6]

4. ዕብ. 10፡1፤ 9፡1-28፤ ገላ. 4፡1-3፤ ቆላ. 2፡17
5. ዘጸ. 19፡9፥10፥19፥23፥27፤ ዘዳ. 24፡19-21፤ 1ኛ ቆሮ. 5፡7፤ 2ኛ ቆሮ. 6፡17፤ ይሁ. 23
6. ቆላ. 2፡14፥16፥17፤ ዳን. 9፡27፤ ኤፌ. 2፡15፥16፤ ዕብ. 9፡10፤ የሐዋ. 10፡9-16፤ 11፡2-10

4. እስራኤላውያን እንደ አንድ መንግሥት የቆሙ ስለነበሩ፤ የተለያዩ የመንግሥት መተዳደሪያ ሕግጋትን ሰጣቸው። እነዚህ

ሕግጋት የእስራኤል መንግሥት ሲፈርስ አብረው ተወግደዋል። ከአጠቃላይ ትምሕርታቸው በስተቀር፤ አሁን ሌሎች መንግሥታትን አያስገድዱም።[7]

7. ዘጸ. 21፡1–23፥19። ዘፍ. 49፡10ን ከ1ኛ ጴጥ. 2፡13፥14ና፤ ከ1ኛ ቆሮ. 9፡8–10 ጋር አወዳድር።

5. የሥነ ምግባር መመሪያ የሆኑት ትእዛዛት ግን የዳኑትንም ምእመናን ጭምር እንደሌሎቹ ሰዎች ለዘላቂታ በሥልጣናቸው አስረዋቸዋል።[8] ይህም የሆነበት ከሥነ ምግባር መምሪያ ትልቅነታቸው የተነሣ ብቻ ሳይሆን፤ የሰጣቸውን የእግዚአብሔርን የፈጣሪነት ሥልጣን ስለሚያንጸባርቁም ነው።[9] ከርስቶስም በአዲስ ኪዳን አጠነከራቸው እንጂ በምንም ዓይነት መንገድ አልሻራቸውም!"[10]

8. ሮሜ 13፡8–10፤ 3፡13፤ 7፡25፤ 1ኛ ቆሮ. 5፡7፤ 2ኛ ቆሮ. 9፡21፤ ገላ. 5፡14፤ ኤፌ. 6፡2፥3፤ 1ኛ ዮሐ. 2፡3፥4፥7። ሮሜ 3፡20ን፤ 7፡7፥8ንና 1ኛ ዮሐ. 3፡4ን ከሮሜ 6፡15 ጋር አወዳድር።
9. ዘዳ. 6፡4፥5፤ ዘጸ. 20፡11፤ ሮሜ 3፡19፤ ያዕ. 2፡8፥10፥11፤ ማቴ. 19፡4–6፤ ዘፍ. 17፡1
10. ማቴ. 5፡17–19፤ ሮሜ 3፡31፤ 1ኛ ቆሮ. 9፡21፤ ሉቃ. 16፡17፥18

6. እውነተኛ አማኞች ምንም እንኳ እንደ ሥራ ቃል ኪዳን በሕግ ለመጽደቅም ሆነ በሕግ ለመኮነን፥ ከሕግ ሥር ባይሆኑም፤[11] ሕጉ ለነሱም ሆነ ለሌሎች፥ የሕይወት መምሪያ በመሆንና የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማስረዳት፤ በጣም ይጠቅማቸዋል፤ በሕጉም መሠረት እንዲራመዱ ያዛቸዋል።[12] በኃጢአት ያደፈ ባሕርያቸውን፥ ልቦናቸውን፥ ሕይወታቸውን ይገልጣል።[13] ይህንንም በማድረጉ ራሳቸውን እየመረመሩ ስለ ኃጢአታቸው ይወቀሳሉ፥ ትሕትናን ይማራሉ፥ ኃጢአታቸውን ይጠላሉ።[14] ከዚህም ሁሉ ጋር ከርስቶስ ምን ያህል እንደሚያስፈልጋቸውና እሱም ለእግዚአብሔር ምን ያህል ፍጹም መታዘዝ እንዳቀረበ እየተረዱ ይመጣሉ።[15] ዳግመኛ ለተወለዱትም እንዲሁ ሕጉ ኃጢአትን በመከልከልና ርኩሰታቸውን በመግታት ይጠቅማቸዋል።[16] በሚሰጠውም የኃጢአት ማስጠንቀቂያ፤ ኃጢአታቸው የሚገባው ምን እንደሆነ ይረዳሉ። ምንም እንኳ ሕጉ ከሚያስጠነቅቀው እርግማን ነፃ ቢሆኑም፤ በዚህ ሕይወት ከኃጢአታቸው የተነሣ ምን መከራ እንደሚገጥማቸው ያሳያቸዋል።[17] እንዲሁም እግዚአብሔር ለሚታዘዙት ያለውን የበረከት የተስፋ ቃል ያሳያቸዋል፤ በመታዘዛቸውም ምን በረከት እንደሚያገኙ ያስረዳቸዋል።[18] ሆኖም

ይህ በረከት በሥራ ቃል ኪዳን በኩል የሚሰጥ የብዳራት ዋጋ አይደለም።[19] ስለዚህ ሰው ሕጉ ስለሚያዘው መልካም ሲሠራ፣ ሕጉም ስለሚከለክለው ከመጥፎ ነገር ሲወገድ፣ ከሕግ በታች ሆነ ማለት አይደለም፤ ወይም ከጸጋ ሥር አይደለም ማለትም አይደለም።[20]

11. ሮሜ 6፡14፤ 7፡4፤ 8፡1፥33፤ ገላ. 2፡16፤ 3፡13፤ 4፡4፥5፤ የሐዋ. 13፡38፥39፤
12. ሮሜ 7፡12፥22፥25፤ መዝ. 119፡1–6፤ 1ኛ ቆሮ. 7፡19፤ ገላ. 5፡14–23
13. ሮሜ 7፡7፥13፤ 3፡20
14. ያዕ. 1፡23–25፤ ሮሜ 7፡9፥14፥24
15. ገላ. 3፡24፤ ሮሜ 7፡24፥25፤ 8፡3፥4
16. ያዕ. 2፡11፥12፤ መዝ. 119፡101፥104፥128
17. ዕዝ. 9፡13፥14፤ መዝ. 89፡30–34፤ ገላ. 3፡13
18. ዘጸ. 19፡5፥6፤ ዘዳ. 5፡33፤ ዘኍ. 18፡5፤ 26፡1–13፤ ማቴ. 19፡17፤ 5፡5፤ 2ኛ ቆሮ. 6፡16፤ ኤፌ. 6፡2፥3፤ መዝ. 37፡11
19. ገላ. 2፡16፤ ሉቃ. 17፡10
20. ሮሜ 6፡12–15። 1ኛ ጴጥ. 3፡8–12ን ከመዝ. 34፡12–16ና ከዕብ. 12፡28፥29 ጋር አስተያይ።

7. ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት የሕግ ጥቅሞች ከወንጌል ጸጋ ጋር አይጋጩም፤ ነገር ግን ድርና ማግ ሆነው ባንድነት ይጣመራሉ።[21] ይህም የሚሆነው መንፈስ ቅዱስ በሕጉ የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ አማኙ በነፃነትና በደስታ እንዲመርጥና እንዲፈጽም ስለሚማርከውና ስለሚያስችለው ነው።[22]

21. ሮሜ 3፡31፤ ገላ. 3፡21፤ ቲቶ 2፡11–14
22. ሕዝ. 36፡27። ዕብ.. 8፡10ን ከኤር. 31፡33፤ ከመዝ. 119፡35፥47ና ከሮሜ 7፡22 ጋር አስተያይ።

ምዕራፍ ሃያ
የክርስቲያንና የሕሊና ነፃነት

1. ክርስቶስ በወንጌል በኩል ምእመናንን ከኃጢአት በደለኝነት፥ ከእግዚአብሔር ኮናኝ ቁጣ፥ ከሕግ እርግማን፥[1] ከፉ ከሆነው ከዚህ ዓለምና ከሰይጣን ባርነት፥ ከኃጢአት ቀንበር፥[2] ከጭንቀት፥ ከሞት ፍርሃት፥ ከመቃብር ድልና ከዘላለም ኩነኔ ነጻ አውጥቷቸዋል።[3] ከእነዚህ ነገሮች ነፃ ከማውጣቱም በላይ፣ ወደ እግዚአብሔር ፊት የመቅረብ መብትን ሰጣቸው።[4] ክርስቲያን እግዚአብሔርን የሚታዘዘው እንደ ባርያ በፍርሃት ተገዶ ሳይሆን፣ እንደ ልጅ

በፍቅርና በአእምሮ ፈቃደኝነት ነው።[5] ይህ የምእመናን ነፃነት በኦሪት ሥር ከነበሩት የምእመናን ነፃነት ጋር እኩል[6] ሲሆን፣ በተጨማሪ የአዲስ ኪዳን ምእመናን የሚከተሉት ተጨማሪ ነፃነቶች ተሰጥተዋቸዋል። የብሉይ ኪዳን አማኞች ይገዙበት ከነበረው ከኦሪት ሥነ ሥርዓትና ሕግጋት ቀንበር[7] የአዲስ ኪዳን አማኞች ነፃ ሆነው፣ በበለጠ ድፍረት ወደ ጸጋው ዙፋን መቅረብን አግኝተዋል።[8] የብሉይ ኪዳን አማኞች ዘወትር ይቀበሉት ከነበረው የበለጠ የመንፈስ ቅዱስን ሙላት ተቀብለዋል።[9]

1. ቲቶ 2፡4፤ 1ኛ ተሰ. 1፡10፤ ገላ. 3፡13
2. ገላ. 1፡4፤ ቆላ. 1፡13፤ የሐዋ. 26፡18፤ ሮሜ 6፡14
3. ሮሜ 8፡28፤ ፡9፤ 8፡1፤ 1ኛ ተሰ. 1፡10፤ መዝ. 119፡71፤ 2ኛ ቆሮ. 4፡15-18፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡54-57፤
4. ሮሜ 5፡1፥2
5. ሮሜ 8፡14፥15፤ ገላ. 4፡6፤ 1ኛ ዮሐ. 4፡18
6. ገላ. 3፡8፥9፥14፤ ሮሜ 4፡6-8፤ 1ኛ ቆሮ. 10፡3፥4፤ ዕብ. 11፡1-40
7. ገላ. 4፡1-7፤ 5፡1፤ የሐዋ. 15፡10፥11
8. ዕብ. 4፡14-16፤ 10፡19-22
9. ዮሐ. 7፡38፥39፤ የሐዋ. 2፡17፥18፤ 2ኛ ቆሮ. 3፡8፥13፥17፥18፤ ኤር. 31፡31-34

2. የሕሊና ጌታ እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ[10] ሃይማኖትንና አምልኮን በሚመለከት ከቃሉ ከሚቃረኑ ከሰዎች ትምህርትና ትእዛዛት ሕሊናችንን ነፃ አድርጎልናል።[11] ስለዚህ በሕሊና ተገዶ እነዚህን ትምሕርቶች ማመንና ትእዛዛቱንም መጠበቅ እውነተኛ የሕሊናን ነፃነት መወርወር ነው።[12] ያለ አንዳች ጥያቄና በጭፍን እምነት እንዲቀበሏቸው ማድረግም የሕሊናን ነፃነትና አእምሮን ማጥፋት ነው።[13]

10. ያዕ. 4፡12፤ ሮሜ 14፡4፥10፤ 1ኛ ቆሮ. 10፡29
11. የሐዋ. 4፡19፤ 5፡29፤ 1ኛ ቆሮ. 7፡22፥23፤ ማቴ. 15፡1-6፤ 23፡8-10፤ 15፡9፤ 2ኛ ቆሮ. 1፡24
12. ቆላ. 2፡20-23፤ ገላ. 1፡10፤ 2፡4፥5፤ 5፡1
13. ሮሜ 10፡17፤ ኢሳ. 8፡20፤ የሐዋ. 17፡11፤ ዮሐ. 4፡22፤ ራእ. 13፡12፥16፥17፤ ኤር. 8፡9፤ 1ኛ ጴጥ. 3፡15

3. በክርስቲያን ነፃነት አስታከው ኃጢአትን የሚሠሩ፥ ወይም ምኞቶቻቸውን የሚንከባከቡ፣ የዚህን የክርስቲያንን ነፃነት ዓላማ ያጠፋሉ። ያም ዓላማ ከጠላቶቻችን እጅ ነፃ ወጥተን ጌታን ያለፍርሃት፥ በቅድስናና በጽድቅ በሕይወታችን ዘመን ሁሉ እንድናገለግለው ነው።[14]

14. ገላ. 5፡13፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡16፤ 2ኛ ጴጥ. 2፡19፤ ሮሜ 6፡15፤ ዮሐ. 8፡34፤ ሉቃ. 1፡74፥75

4. እግዚአብሔር የሾማቸው ሥልጣናትና ክርስቶስ የገዛው ነፃነት፥ እርስ በርስ እንዲጠፋፉ ሳይሆን፤ እርስ በርስ እንዲቋቋሙና እንዲደጋገፉ እግዚአብሔር አቅዱል። ስለዚህ በክርስቲያን ነፃነት አስታከው፥ የመንግሥትንም ቢሆን የቤተ ክርስቲያንን፥ ማንኛውንም ሕጋዊ ሥልጣን፥ ወይም አስተዳደር፤ የሚቃወሙ የእግዚአብሔርን ሥነ ሥርዓት ይቃወማሉ።[15] እንደዚህ ያለውንም አስተሳሰብ የሚያስፋፉ ወይም እንደዚህ ያሉትን በሥራ ላይ የሚያውሉ፥ ክርስቶስ በቤተ ክርስቲያን የመሠረተውን ውጫዊ ሰላምና ሥርዓት አፍራሽ ስለሆኑ፤ በሕግ ፊት ሊቀርቡና የቤተ ክርስቲያንም ቅጣት ሊሰጣቸው ይገባል።[16]

15. 1ኛ ጴጥ. 2፡13፥14፥16፤ ሮሜ 13፡1–8፤ ዕብ. 13፡17፤ 1ኛ ተሰ. 5፡12፥13
16. ሮሜ 1፡32፤ 16፡17፤ ማቴ. 18፡15–17፤ 1ኛ ቆሮ. 5፡1፥5፥11–13፤ 2ኛ ዮሐ. 10፥11፤ 2ኛ ተሰ. 3፡6፥14፤ 1ኛ ጢሞ. 6፡3፥4፤ 1፡19፥20፤ ቲቶ 1፡10፥11፥13፥14፤ 3፡10፤ ራእ. 2፡214፥15፥20

ምዕራፍ ሃያ አንድ
አምልኮተ እግዚአብሔርና ሰንበት

1. አንድ አምላክ እንዳለ፥ እሱም በሁሉም ላይ ጌትነትና ሥልጣን እንዳለውና ለሁሉም ቸርነትን እንደሚያደርግ፤ ስለዚህም በሙሉ ልብ፥ በሙሉ ነፍስና በሙሉ ኃይል መፈራት፥ መፈቀር፥ መወደስ፥ መጠራት፥ መታመን፥ መገልገል እንዳለበት፤ ሰው በተፈጥሮው ያገኘው የሕሊና ብርሃን ያመለክታል።[1] ነገር ግን ተቀባይነት ያለው ሕያውን አምላክ የማምለክ ሥርዓት፤ በራሱ በእግዚአብሔር የተመሠረተ ነው። ይህም ሥርዓት እርሱ በሚሰጠው መግለጫ ብቻ ስለተወሰነ፤ በሰዎች ግምትና ዘዴ ወይም ሰይጣን በሚሰጠው ሐሳብ መሠረት፤ በሚታይ ነገር በመመሰል ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ ባልተሰጠ በማንኛውም ዓይነት መንገድ እንዳናመልከው ተከልክለናል።[2]

1. ሮሜ 1፡20፤ መዝ. 19፡1–4፤ 97፡6፤ 145፡9–12፤ 104፡1–35፤ 86፡8–10፤ 95፡1–6፤ 89፡5–7፤ የሐዋ. 14፡17፤ ዘዳ. 6፡4–5
2. ዘዳ. 12፡32፤ 4፡15–20፤ ዘጸ. 20፡4–6፤ ዮሐ. 4፡23፥24፤ ማቴ. 15፡9፤ 4፡9፥10፤ የሐዋ. 17፡23–25፤ ቆላ. 2፡18–23

2. ስግደትና አምልኮ ለአብ፥ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ብቻ ሊሰጥ ይገባል።[3] ለመላእክት ወይም ለሌሎች ፍጡሮች መሰጠት የለበትም።[4] ደግሞም ሰው በኃጢአት ከወደቀ ወዲህ፣ ያለ አማላጅ እግዚአብሔርን ማምለክ አይችልም። ከጌታ ከኢየሱስም ብቻ በስተቀር ሌላ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የቆመ አማላጅ ወይም መካከልኛ የለም።[5]

3. ዮሐ. 5፡23፤ 10፡25፥26፤ ማቴ. 28፡19፤ 2ኛ ቆሮ. 13፡14፤ ኤፌ. 3፡14፤ ራእ. 5፡11–14፤
4. ቆላ. 2፡18፤ ራእ. 19፡10፤ ሮሜ 1፡25
5. ዮሐ. 14፡6፤ 1ኛ ጢሞ. 2፡5፤ ኤፌ. 2፡18፤ ቆላ. 3፡17

3. እያመሰገኑ መጸለይ፥ እግዚአብሔር ከሚመለከባቸው መንግዶች አንዱ መንገድ ስለሆነ[6] ከሰዎች ሁሉ ይጠበቅባቸዋል።[7] ይህም ጸሎት ተቀባይነት እንዲያገኝ፣ በወልድ ስም፥[8] በመንፈስ ቅዱስ ረዳትነት፥[9] እንደፈቃዱ መሠረት፥[10] ትርጉሙ በሚገባን መንገድ፥ በአክብሮት፥ በትሕትና፥ በትጋት፥ በእምነት፥ በፍቅር፥ በጽናት ሊሆን ይገባል።[11] በሚሰማ ድምጽ ከሆነም በሚታወቅ ቋንቋ መሆን አለበት።[12]

6. ፊል. 4፡6፤ 1ኛ ጢሞ. 2፡1፤ ቆላ. 4፡2
7. መዝ. 65፡2፤ 67፡3፤ 96፡7፥8፤ 148፡11–13፤ ኢሳ. 55፡6፥7
8. ዮሐ. 14፡13፥14፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡5

4. ጸሎት ለተፈቀዱ ነገሮች ብቻ ሊደረግ ይገባል።[13] በሕይወት ላሉና ወደፊትም ለሚወለዱት ሰዎች ሁሉ እንጂ[14]፤ ከዚህ ዓለም በሞት ለተለዩት ሰዎች መጸለይ ክልክል ነው።[15] ምሕረት የማይደረግለትን ኃጢአት የፈጸሙ መሆናቸው ለታወቀም መጸለይ ክልክል ነው።[16]

13. ሮሜ 8፡26፤ ኤፌ. 6፡18
14. 1ኛ ዮሐ. 5፡14
15. መዝ. 47፡7፤ መክ. 5፡1፥2፤ ዕብ. 12፡28፤ ዘፍ. 18፡27፤ ያዕ. 5፡16፤ 1፡6፥7፤ ማር. 11፡24፤ ማቴ. 6፡12፥14፥15፤ ቆላ. 4፡2፤ ኤፌ. 6፡18
16. 1ኛ ዮሐ. 5፡16

5. እግዚአብሔርን እያከበሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፥[17] ትክክለኛ የሆነ የቃለ እግዚአብሔር ስብከት፥[18] እግዚአብሔርን በመታዘዝ፥ በማስተዋል፥ በእምነት፥ በአክብሮትና በመረዳት ቃሉን መስማት፥[19]

ጸጋ በተሞላ ልብ መዘመር፥20 በክርስቶስ የተመሠረቱትን የምሥጢር ሥርዓቶች በትክክል እየተፈጸሙ ተገቢ በሆነው መንገድ መቀበል፤ እነዚህ ሁሉ ዘወትር እግዚአብሔር የሚመለከባቸው መንገዶች ናቸው።21 በተጨማሪም ደግሞ በተወሰኑ ጊዜዎች በቅድስናና ሃይማኖታዊ በሆነ መንገድ22 መሐላ፥23 ስእለት፥24 ጾም፥25 ምስጋና ሊደረጉ ይገባል።26

17. ሉቃ. 4፡16፥17፤ የሐዋ. 15፡21፤ ቆላ. 4፡16፤ 1ኛ ተሰ. 5፡27፤ ራእ. 1፡3
18. 2ኛ ጢሞ. 4፡2፤ የሐዋ. 5፡42
19. ያዕ. 1፡22፤ የሐዋ. 10፡33፤ ማቴ. 13፡19፤ ዕብ. 4፡2፤ ኢሳ. 66፡2
20. ቆላ. 3፡16፤ ኤፌ. 5፡19፤ ያዕ. 5፡13፤ 1ኛ ቆሮ. 14፡15
21. ማቴ. 28፡19፤ 1ኛ ቆሮ. 11፡23-29፤ የሐዋ. 2፡42
22. ያዕ. 12፡28
23. ዘዳ. 6፡13፤ ነህ. 10፡29፤ 2ኛ ቆሮ። 1፡23
24. መዝ. 116፡14፤ ኢሳ. 19፡21፤ መክ. 5፡4፥5
25. ኢዩ. 2፡12፤ አስቴር 4፡16፤ ማቴ. 9፡15፤ የሐዋ. 14፡23
26. ዘጸ. 15፡1-21፤ መዝ. 107፡1-43፤ ነህ. 12፡27-43፤ አስ. 9፡20-22

6. አሁን በወንጌል ዘመን ማንኛውም የአምልኮ ክፍል በቦታ የተወሰነ አይደለም፤ ወይም በቦታው ምክንያትና ወደ ቦታው አቅጣጫ በመደረጉ ተቀባይነት አይኖረውም።27 ነገር ግን፥ እግዚአብሔርን በማንኛውም ቦታ በመንፈስና በእውነት ማምለክ ይቻላል።28 በየቀኑ30፥ በቤተሰብና31 በግል ይመለካል።32 እንዲሁም አከብሮት ባለው መንገድ በጉባኤ ይመለካል።33 እግዚአብሔር በቃሉና በአስተዳደሩ ለነዚህ የአምልኮ አገልግሎቶች ሲጠራ፣ በግዴለሽነትና በእምቢተኝነት መቅረት ወይም መሰረዝ አይገባም።33

27. ዮሐ. 4፡21
28. ሚል. 1፡11፤ 1ኛ ጢሞ. 2፡8
29. ዮሐ. 4፡23፥24
30. ኤር. 10፡25፤ ዘዳ. 6፡6፥7፤ ኢዮ. 1፡5፤ 2ኛ ሳሙ. 6፡18፥20
31. ማቴ. 6፡11፤ ኢዮብ 1፡5
32. ማቴ. 6፡6፥16-18፤ ነህ. 1፡4-11፤ ዳን. 9፡3፥4
33. ኢሳ. 56፡6፥7፤ ዕብ. 10፡25፤ መዝ. 100፡4፤ 122፡1፤ 84፡1-12፤ ሉቃ. 4፡16፤ የሐዋ. 13፡42፥44፤ 2፡42

7. ከጊዜ ተከፍሎ እግዚአብሔርን ማምለኪያ መወሰን የተፈጥሮ ሕግ እንደሆነ ሁሉ፤ እንዲሁም በቃሉ ዘላቂ በሆነና ሰዎችን ሁሉ በሚመለከት ሕግ በዘመናት ሁሉ ከሰባት አንድ ቀን ለሱ የተቀደሰ ሰንበት እንዲሆን ደንግጓል።34 ይህም ቀን ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ

ጸጋ በተሞላ ልብ መዘመር፥[20] በክርስቶስ የተመሠረቱትን የምሥጢር ሥርዓቶች በትክክል እየተፈጸሙ ተገቢ በሆነው መንገድ መቀበል፤ እነዚህ ሁሉ ዘወትር እግዚአብሔር የሚመለከባቸው መንገዶች ናቸው።[21] በተጨማሪም ደግሞ በተወሰኑ ጊዜዎች በቅድስናና ሃይማኖታዊ በሆነ መንገድ[22] መሐላ፥[23] ስእለት፥[24] ጾም፥[25] ምስጋና ሊደረጉ ይገባል።[26]

17. ሉቃ. 4፡16፥17፤ የሐዋ. 15፡21፤ ቆላ. 4፡16፤ 1ኛ ተሰ. 5፡27፤ ራእ. 1፡3
18. 2ኛ ጢሞ. 4፡2፤ የሐዋ. 5፡42
19. ያዕ. 1፡22፤ የሐዋ. 10፡33፤ ማቴ. 13፡19፤ ዕብ. 4፡2፤ ኢሳ. 66፡2
20. ቆላ. 3፡16፤ ኤፌ. 5፡19፤ ያዕ. 5፡13፤ 1ኛ ቆሮ. 14፡15
21. ማቴ. 28፡19፤ 1ኛ ቆሮ. 11፡23–29፤ የሐዋ. 2፡42
22. ያዕ. 12፡28
23. ዘዳ. 6፡13፤ ነህ. 10፡29፤ 2ኛ ቆሮ። 1፡23
24. መዝ. 116፡14፤ ኢሳ. 19፡21፤ መክ. 5፡4፥5
25. ኢዩ. 2፡12፤ አስቴር 4፡16፤ ማቴ. 9፡15፤ የሐዋ. 14፡23
26. ዘጸ. 15፡1–21፤ መዝ. 107፡1–43፤ ነህ. 12፡27–43፤ አስ. 9፡20–22

6. አሁን በወንጌል ዘመን ማንኛውም የአምልኮ ክፍል በቦታ የተወሰነ አይደለም፤ ወይም በቦታው ምክንያትና ወደ ቦታው አቅጣጫ በመደረጉ ተቀባይነት አይኖረውም።[27] ነገር ግን፥ እግዚአብሔርን በማንኛውም ቦታ በመንፈስና በእውነት ማምለክ ይቻላል።[28] በየቀኑ[30]፥ በቤተሰብና[31] በግል ይመለካል።[32] እንዲሁም አክብሮት ባለው መንገድ በጉባኤ ይመለካል።[33] እግዚአብሔር በቃሉና በአስተዳደሩ ለነዚህ የአምልኮ አገልግሎቶች ሲጠራ፣ በግዴለሽነትና በእምቢተኝነት መቅረት ወይም መሰረዝ አይገባም።[33]

27. ዮሐ. 4፡21
28. ሚል. 1፡11፤ 1ኛ ጢሞ. 2፡8
29. ዮሐ. 4፡23፥24
30. ኤር. 10፡25፤ ዘዳ. 6፡6፥7፤ ኢዮ. 1፡5፤ 2ኛ ሳሙ. 6፡18፥20
31. ማቴ. 6፡11፤ ኢዮብ 1፡5
32. ማቴ. 6፡6፥16–18፤ ነህ. 1፡4–11፤ ዳን. 9፡3፥4
33. ኢሳ. 56፡6፥7፤ ዕብ. 10፡25፤ መዝ. 100፡4፤ 122፡1፤ 84፡1–12፤ ሉቃ. 4፡16፤ የሐዋ. 13፡42፥44፤ 2፡42

7. ከጊዜ ተከፍሎ እግዚአብሔርን ማምልኪያ መወሰን የተፈጥሮ ሕግ እንደሆነ ሁሉ፤ እንዲሁም በቃሉ ዘላቂ በሆነና ሰዎችን ሁሉ በሚመለከት ሕግ በዘመናት ሁሉ ከሰባት አንድ ቀን ለሱ የተቀደሰ ሰንበት እንዲሆን ደንግጓል።[34] ይህም ቀን ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ

እስከ ክርስቶስ ትንሣኤ ድረስ የሳምንቱ መጨረሻ ቀን ሲሆን፤ ከክርስቶስ ትንሣኤ በኋላ ደግሞ ወደ ሳምኑት መጀመሪያ ቀን ተቀይሯል።[35] ይህም የጌታ ቀን ተብሎ ይጠራል።[36] የክርስቲያን ሰንበትም ሆኖ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ይጸናል።[37]

34. ዘጸ. 20፡8–11፤ ኢሳ. 56፡2–7
35. ዘፍ. 2፡2፥3፤ 1ኛ ቆሮ. 16፡1፥2
36. ራእ. 1፡10
37. ማቴ. 5፡17፥18፤ ማር. 2፡27፥28፤ ሮሜ 13፡8–10፤ ያዕ. 2፡8–12

8. ሰዎች ልባቸውን በሚገባ ካዘጋጁ በኋላ፥ አስቀድመውም የዕለት ተግባራቸውን በማከናወን፥ ዓለማዊ ሥራቸውንና መዝናኛቸውን[38] ሥራቸውን፥ የማይገባ ቃላቸውንና ሐሳባቸውን አስወግደው፤ የተቀደሰ እረፍት በማድረግ ብቻ ሳይሆን፤ ጠቃላላ ጊዜውን ለጉባኤና ለግል አምልኮተ እግዚአብሔር፥ እንዲሁም ለአስፈላጊና ለምሕረት ሥራ[39] ሲያውሉ፥ ሰንበት ያን ጊዜ ለጌታ ይቀደሳል።

38. ዘጸ. 20፡8፤ 16፡23–30፤ 31፡15–17፤ ኢሳ. 58፡13፥14፤ ነህ. 13፡15–22
39. ኢሳ. 58፡13፥14፤ ሉቃ. 4፡16፤ ማቴ. 12፡1–13፤ ማር. 3፡1–5

ምዕራፍ ሃያ ሁለት
መሐላና ሥዕለት

1. መሐላ ከአምልኮት ክፍል አንዱ ሲሆን፤[1] ተገቢ በሆነበት ወቅት መሐላውን የሚሰጠው ሰው ለሚመሰክረው ነገር ወይም ለሚሰጠው ተስፋ ምስክር እንዲሆንና ለሚምልበት ነገር እውነት ወይም ውሸት እንደሆነ እንዲፈርድ እግዚአብሔርን ይጠራል።[2]

1. ዘዳ. 10፡20፤ ኢሳ. 45፡23፤ ሮሜ 14፡11፤ ፊል. 2፡10፥11
2. ዘጸ. 20፡7፤ ዘሌ. 19፡12፤ ሮሜ 1፡9፤ 2ኛ ቆሮ. 11፡31፤ ገላ. 1፡20፤ 2ኛ ዜና 6፡22፥23

2. ሰዎች ሊምሉበት የሚገባ የእግዚአብሔር ስም ብቻ ነው። ስለሆነም በተቀደሰ ፍርሃትና አክብሮት መፈጸም አለበት።[3] ስለዚህ በከንቱ ወይም በቸኮላ፥ በዚያ በከበረውና በሚያስፈራው ስም መማል ወይም በሌላ ነገር መማል፤ ፍጹም ኃጢአትና ልንጸየፈው የሚገባ ነው።[4] ነገር ግን ከባድ ለሆኑ ነገሮችና ወቅቶች መሐላ፥ በአዲስ ኪዳንም እንደ ብሉይ ኪዳን ጊዜ በእግዚብሔር ቃል

ተፈቅዱል።[5] ስለዚህ እንደዚህ ላሉ ነገሮች መሐላ በባለሥልጣን በሚጠየቅበት ጊዜ ሊፈጸም ይገባል።[6]

3. ዘዳ. 6፡13፤ ኢያ. 23፡7
4. ዘጸ. 20፡7፤ ኤር. 5፡7፤ ማቴ. 5፡33–37፤ ያዕ. 5፡12
5. ዕብ. 6፡16፤ 2ኛ ቆሮ. 1፡23፤ ኢሳ. 65፡16
6. 1ኛ ነገ. 8፡31፤ ነህ. 13፡25፤ ዕዝ. 10፡5

3. መሐላን የሚፈጽም ሁሉ የመሐላን ከባድነትና ጥብቅነት ማስተዋል ይገባዋል። ስለሆነም ሰው እውነት ለመሆኑ እርግጠኛ ለሆነበት ነገር ብቻ ምስክር ሊሆን ይገባዋል።[7] እንዲሁም ሰው መልካምና ጽድቅ ለሆነ ነገር፥ ለሚያምንበት ነገር፥ ሊፈጽመው የወሰነበትና ለመፈጸም ችሎታው ለሚፈቅድለት ነገር ብቻ እንጂ፥ ለሌላ ነገር ራሱን በመሐላ ማሰር የለበትም።[8]

7. ዘጸ. 20፡7፤ ዘሌ. 19፡12፤ ኤር. 4፡2፤ ሆሴ. 10፡4
8. ዘፍ. 24፡2–9፤ ነህ. 5፡12፥13፤ መክ. 5፡2፥5

4. መሐላ የቃላቱ ትርጉም ግልጽ በሆነ መንገድና መንታ የሆነ ትርጉም በሌለው አነጋገር ያለማመንታት መፈጸም አለበት።[9] ምን ጊዜም ቢሆን መሐላ ኃጢአትን ለመፈጸም ሊያስገድድ አይገባም። ኃጢአት ባልሆነ ነገር ሁሉ ግን ራስን ጎጂ ሆኖ ቢገኝም እንኳ፥ መሐላ ከተወሰደ ግዴታው መፈጸም አለበት።[10] ለሐሰተኞች ወይም ለማያምኑ ቢሰጥም መሐላው መጣስ የለበትም።[11]

9. ኤር. 4፡2፤ መዝ. 24፡4
10. 1ኛ ሳሙ. 25፡22፥32–34፤ መዝ. 15፡4
11. ሕዝ. 17፡16–19፤ አያ. 9፡18፥19፤ 2ኛ ሳሙ. 21፡1

5. ሥዕለት ቃል ኪዳን ስለሆነ በሃይማኖት ጥብቅነት መታየት አለበት። እንደ ሃይማኖትም ታማኝነት መፈጸም አለበት።[12]

12. ዘኍ. 30፡2፤ ኢሳ. 19፡21፤ መክ. 5፡4–6፤ መዝ. 61፡8፤ 66፡13፥14

6. ሥዕለት ለፍጡር ሳይሆን ለእግዚአብሔር ብቻ ሊሰጥ ይገባዋል።[13] ተቀባይነት እንዲኖረውም በፈቃደኝነት፥ በእምነት፥ ሐላፊነትን በመገንዘብ፥ ለተቀበልነው ምሕረት ምስጋናን በሚገልጽ ሁኔታ፥ የምንፈልገውን ለመቀበያ እንሳላለን። ሥዕለት የሃይማኖት ግዴታችንን ለመፈጸም፤ ወይም ወደዚሁ ዓላማ እስከመሩን ድረስ

ሌሎች ነገሮችን ለማድረግ በበለጠ ጥብቅነት ራሳችንን የምናስርበት ነው።[14]

13. መዝ. 50፡14፤ 76፡11፤ 116፡14
14. ዘዳ. 23፡21–23፤ ዘፍ. 28፡20–22፤ 1ኛ ሳሙ. 1፡11፤ መዝ. 66፡13፥14፤ 132፡2–5

7. ማንም ሰው በእግዚአብሔር ቃል የተከለከውን ከማስወገድና የታዘዘውን ከመፈጽም የሚያግደውን ነገር እፈጽማለሁ ብሎ ወይም ደግሞ ስእለቱን ለመፈጸም የሚያስችለው ከእግዚአብሔር የተሰጠው ተሰፋና ችሎታ ሳይኖረው፣ በድፍረትና ባለማስተዋል ተነሣስቶ፣ መሳል የለበትም።[15] በዚህ ረገድ የካቶሊኮች ለሁል ጊዜ ሳያገቡ በምንኩስና፥ በድህነትና በፍጹም ታዛዥነት ለመኖር መሳል ከፍተኛ የጽድቅ ኑሮ ከመሆን እጅግ የራቀ፥ ከንቱ አምልኮና የኃጢአት ወጥመድ ነው። እነዚህን በመሳሰሉ ትብታቦች ክርስቲያን ራሱን ማጠላለፍ የለበትም።[16]

15. የሐዋ. 23፡12–14፤ ማር. 6፡26፤ ዘኍ. 30፡5፥8፥12፥13
16. ማቴ. 19፡11፥12፤ 1ኛ ቆሮ. 7፡2፥9፤ ዕብ. 13፡4፤ ኤፌ. 4፡28፤ 1ኛ ተሰ. 4፡11፥12፤ 1ኛ ቆሮ. 7፡23

ምዕራፍ ሃያ ሦስት
የሕዝብ አስተዳዳሪዎች

1. የዓለም ሁሉ ጌታና ንጉሥ የሆነው እግዚአብሔር በእርሱ ሥር እንዲሆን፥ በሕዝብ ላይ ሥልጣን እንዲይዝ፥ ለክብሩና ለሕዝቡ በጎ እንዲሆን መንግሥትን መሥርቷል። የመልካም አድራጊዎችን መብት በማስጠበቅ፥ በበጎ ሥራቸው እንዲያበረታታቸውና ክፉ አድራጊዎችን እንዲቀጡበት ባለሥልጣንን ሰይፍ አስታጥቋል።[1]

1. ሮሜ 13፡1–4፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡13፥14

2. ክርስቲያን ለመንግሥት አገልግሎት በተጠራ ጊዜ ጥሪውን ለመቀበልና አገልግሎቱን ለመፈጸም ተፈቅዶለታል።[2] እንደየአገሩም ሕግና ደንብ መሠረት፣ የመንግሥት ሥራውን፥ እግዚአብሔርን በመፍራት፥ በትሕትናና በሰላም ሊያካሂድ ይገባዋል።[3] ዓመፃን ለመቃወም አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ፥ በሕግ መሠረት አሁንም በአዲስ ኪዳን ለጦርነት መሰማራት ይኖርበታል።[4]

2. ዘፍ. 41፡39-43፤ ነህ. 12፡26፤ 13፡15-31፤ ዳን. 2፡48፥49፤ ምሳ. 8፡15፥16፤ ሮሜ 13፡1-4
3. መዝ. 2፡10-12፤ 1ኛ ጢሞ. 2፡2፤ መዝ. 82፡3፥፤ 2ኛ ሳሙ. 23፡3፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡13
4. ሉቃ. 3፡14፤ ሮሜ 13፡4፤ ማቴ። 8፡9፥10፤ የሐዋ. 10፡1፥2

3. የእግዚአብሔር መንግሥት መከፈቻ ለእነርሱ አልተሰጠምና፤ የመንግሥት ባለሥልጣናት ቃሉን መስበክ፥ ጥምቀትንና ቁርባንን መፈጸም፥ ሥራቸው ሊያደርጉት አልተፈቀደላቸውም።[5] በሃይማኖት ነገር በምንም ዓይነት ጣልቃ ገብ መሆን የለባቸውም።[6] ነገር ግን መንግሥት እግዚአብሔርን በመታዘዝ፥ ቤተ ክርስቲያንን ሕገወጥ ከሆነ ጥቃት እንደአባት ሊጠብቃት ይገባል። ይህም በግዛቱ ውስጥ ለሚገኙት በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ያለ አድልዎ ሊሆን ይገባል። በየትኛውም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለ ሰው፤ የሃይማኖት ተግባሩን በነፃነትና ያለ ፍርሃት እንዲያካሄድ መንግሥት ለዜጎቹ የነፃነት መከታ ሊሆን ይገባል።[7] ለቤተ ክርስቲያንም ኢየሱስ ክርስቶስ እንደመሠረተው አስተዳደርና ደንብ መሠረት ቤተ ክርስቲያን ሥራዋን በምታራምድበት ጊዜና ለተለያዩት አብያተ ክርስቲያናትም በፈቃዳቸው አባል የሆኑት እንደየእምነታቸው የሃይማኖት ግዳጃቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ፤ ማንኛውም መንግሥት በጣልቃ ገብነት ሊያስገድድ፥ ሊያዝ፥ ወይም ሊከለክል አይገባም።[8] ሕዝባቸውንና የሕዝባቸውን ጥሩ ስም ማስከበር፥ የመንግሥት ባለሥልጣናት ግዴታ ነው። ይህም በሃይማኖት ወይም በከህደት በማሳበብ ማንም ሰው ሌላውን እንዳይበድል፥ እንዳይጎዳ፥ እንዳያሰድብ፥ የአብያተ ክርስቲያናትም ጉባኤዎች እንዳይንገላቱና እንዳይበጠበጡ መንግሥት መከላከል አለበት።[9]

5. 2 ዜና 26፡18፤ ማቴ. 18፡17፤ 16፡19፤ 1ኛ ቆሮ. 12፡28፥29፤ 4፡1፥12፤ ሮሜ 10፡15፤ ዕብ. 5፡4፤
ኤፌ. 4፡11፥12
6. ዮሐ. 18፡36፤ የሐዋ. 5፡29፤ ኤፌ. 4፡11፥12
7. ኢሳ. 49፡23፤ ሮሜ 13፡1-6
8. መዝ. 105፡15
9. ሮሜ 13፡4፤ 1ኛ ጢሞ. 2፡2

4. ለባለሥልጣናት መጸለይ የሕዝቡ ግዴታ ነው።[10] ባለሥልጣንን ማክበር[11]፥ የሚገባቸውን ክብር ወይም ግብር መስጠት፥[12] በሕሊና ምክንያት ሕጋዊ ትእዛዛቸውን መታዘዝ ተገቢ ነው።[13] ከህደት ወይም ለሃይማኖት ግዴለሽ መሆን የባለሥልጣንን ሕጋዊ ሥልጣን

አይሽረውም።[14] ሕዝቡም ከመታዘዝ ነፃ መሆን አይገባቸውም።[15] ጳጳሱም፥ ባለሥልጣንንም ሆነ በአስተዳደራቸው ውስጥ ያለው ሕዝባቸውን፣ ከመንግሥት አስተዳደር ውስጥ ጣልቃ ገብተው፣ ሊያዟቸው አይገባም። ጳጳሳት ተቃዋሚዎቻቸውን ሐሰተኞች አስተማሪዎች ናቸው በማለት፣ ከሥልጣናቸው ውጭ በመንግሥት ሥልጣን ሥር ሾልከው እየገቡ፥ መብታቸውንና ሕይወታቸውን ሊጎዱ አልተፈቀደላቸውም።[16]

10. 1ኛ ጢሞ. 2፡1-3
11. 1ኛ ጴጥ. 2፡17
12. ማቴ. 22፡21፤ ሮሜ 13፡6፥7
13. ሮሜ 13፡5፤ ቲቶ 3፡1
14. 1ኛ ጴጥ. 2፡13-16
15. ሮሜ 13፡1፤ የሐዋ. 25፡9-11፤ 2ኛ ጴጥ. 2፡1፥10፥11፤ ይሁ. 8-11
16. ማር. 10፡42-44፤ ማቴ. 23፡8-12፤ 2ኛ ጢሞ. 2፡24፤ 1ኛ ጴጥ. 5፡3

ምዕራፍ ሃያ አራት
ጋብቻና ፍቺ

1. ጋብቻ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል ሊሆን ይገባል። ለማንም ሰው ከአንዲት ሴት በላይ ማግባት አልተፈቀደለትም፤ እንዲሁም አንዲት ሴት በአንድ ጊዜ ከአንድ በላይ ባል ሊኖራት አይገባም።[1]

1. ዘፍ. 2፡24፤ ማቴ. 19፡4-6፤ ሮሜ 7፡3፤ ምሳ. 2፡17

2. ጋብቻ ለባልና ለሚስት እርስበርስ መደጋገፊያ፥[2] በሕጋዊ መንገድ የሰውን ልጅ ዘር ለማባዣ፥ ቤተ ክርስቲያንን በቅዱስ ዘር ለመገንቢያና[3] የዝሙትን ርኩሰት መከላከያ እንዲሆን ተመሥርቷል።

2. ዘፍ. 2፡18፤ ኤፌ. 5፡28፤ 1ኛ ጴጥ. 3፡7
3. ዘፍ. 1፡28፤ 9፡1፤ ሚል. 2፡15
4. 1ኛ ቆሮ. 7፡2፥9

3. በማስተዋል መወሰን እስከቻሉ ድረስ ሁሉም ዓይነት ሰዎች ማግባት ተፈቅዶላቸዋል።[5] ሆኖም ክርስቲያን በጌታ ውስጥ ብቻ

ለመጋባት ግዴታ አለበት።[6] ስለዚህም በርግጥ በተሐድሶ[1] ሃይማኖት የሚያምኑ፣ የማያምኑትን፥ የጳጳስ ተከታዮችን ወይም ሌሎችን ጣዖት አምላኪዎችን ማግባት የለባቸውም። እንዲሁም እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎች በሕይወታቸው መጥፎ የሆኑትንና ፍርድ የሚያስከትል ሐሰተኛ ትምህርት የሚከተሉትን በማግባት በማይመች አኳኋን መጠመድ የለባቸውም።[7]

5. ዕብ. 13፡4፤ 1ኛ ጢሞ. 4፡3፤ 1ኛ ቆሮ. 7፡36-38፤ ዘፍ. 24፡57፥58
6. 1ኛ ቆሮ. 7፡39
7. ዘፍ. 34፡14፤ ዘጸ. 34፡16፤ 2ኛ ቆሮ. 6፡14፤ ዘዳ. 7፡3፥4፤ 1ኛ ነገ. 11፡4፤ ነህ. 13፡25-27፤ ሚል. 2፡11፥12

4. ጋብቻ በቃሉ በተከለከለ የቅርብ ዘመድ መካከል መሆን የለበትም።[8] ይህም ዓይነት ጋብቻ በምንም የሰው ሕግ ወይም በሰዎች ውል በመመረቅ ጸድቆ፥ እነዚያ ሰዎች በባልና ሚስትነት አብረው ለመኖር አይችሉም።[9]

8. ዘሌ. 18፡6-17፥24-30፤ 20፡19፤ 1ኛ ቆሮ. 5፡1፤ አሞ. 2፡7
9. ማር. 6፡18፤ ዘሌ. 18፡24-28

5. አመንዝራነት ወይም ዝሙት ከጋብቻ ውል በኋላ ተፈጽሞ፥ ጋብቻው ከመፈጸሙ በፊት ከታወቀ፤ በደሉን ያልፈጸመው ውሉን ለማፍረስ መብት አለው።[10] ከጋብቻ በኋላ ስለሚፈጽም ምንዝርና፥ በደሉን ያልፈጸመው ወገን፣ በሕግ ፍችን መጠየቅ ይችላል።[11] ከፍችውም በኋላ አጥፊው እንደሞተ ያህል ተቆጥሮ፤ በደሉን ያልፈጸመው ዳግመኛ ለማግባት ተፈቀዶለታል።[12]

10. ማቴ. 1፡18-20፤ ዘዳ. 22፡23፥24
11። ማቴ. 5፡31፥32
12. ማቴ. 19፡9፥ ሮሜ 7፡2፥3

6. ምንም እንኳ የሰው ርኩሰት እጅግ ከመከፋቱ የተነሣ እግዚአብሔር በጋብቻ አንድ ያደረጋቸውን ያለ አግባብ ለመለያየት ከርከር ቢያጠነጥንም ቅሉ፤ ጋብቻ ሊፈርስ የሚችለው በዝሙት ምክንያት ነው። ጋብቻን በእንቢተኝነት ጥሎ ሄዶ፥ ቤተ

---

[1]ተሐድሶ የተባሉት በ16ኛው መቶ ዓመት በአውሮፓ የሮማን ቤተ ክርስቲያን ስሕተት ትምህርት በመቃወም የተነሡት ናቸው። በተጫማሪም ጳጳስ የሚለው ቃል እንዲሁ የሮማ ቤተ ክርስቲያንን ጳጳስ ነው።

ክርስቲያንም ሆነች መንግሥት፥ አጥፊውን ሊያርሙት ሳይችሉ ሲቀሩ፤ መፍታት ተፈቅዱል።[13] ይህም ሆኖ ሳለ ግን፥ ፍቾው ሕግንና ሥነ ሥርዓትን የተከተለ እንጂ፣ ነገሩ በሚፋቱት ሰዎች መካከል ብቻ ተወስኖ፤ በራሳቸው ፈቃድና መብት ብቻ ሊፈጸም አይገባም።[14]

13. ማቴ. 19፡8፥9 1ኛ ቆሮ. 7፡15፤ ማቴ. 19፡6
14. ዘዳ. 24፡1-4

ምዕራፍ ሃያ አምስት
ቤተ ክርስቲያን

1. የማትታየው ዓለም አቀፍ ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ሥርና በአንድ አካል ሆና፤ የተመረጡት ሁሉ ቁጥር ሙላት ናት። እነርሱም እስከ አሁን ያመኑትና ወደፊት የሚያምኑት ሁሉ ናቸው። ይህችም አንዲቷ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ሙሽራ፥ የክርስቶስ አካል፥ ሁሉን የሚሞላ የእርሱ ሙላት ናት።1

1. ኤፌ. 1፡10፥22፥23፥ 5፡23፥27፥32፤ ቆላ. 1፡18

2. የምትታየው ቤተ ክርስቲያንም ዓለም አቀፍ ናት። እንደ ብሉይ ኪዳን ጊዜ በአንድ ሕዝብ ብቻ ሳትወሰን፤ በዓለም ሁሉ እውነተኛውን የክርስቲያን ኃይማኖት የሚቀበሉትን[2] ልጆቻቸውን[3] ሁሉ የምታቅፍ ናት። የክርስቶስ መንግሥት ናት፥[4] የእግዚአብሔር ቤተሰብ ናት።[5] ከእርሷም ውጭ በመሆን ደኅንነትን የምንቀበልበት ሌላ መንገድ አልተሰጠንም።[6]

2. 1ኛ ቆሮ. 1፡2፤ 12፡12፥13፤ መዝ. 2፡8፤ ራእ. 7፡9፤ ሮሜ 15፡9-12
3. 1ኛ ቆሮ. 7፡14፤ የሐዋ. 2፡39፤ ዘፍጥ. 17፡7-12፤ ሕዝ. 16፡20፥21፤ ሮሜ 11፡16፤ 4፡12፥16፥24፤ ገላ. 3፡7፥9፥14
4. ማቴ። 13፡47፤ ኢሳ. 9፡7፤ ሉቃ. 1፡32፥33፤ የሐዋ. 2፡30-36፤ ቆላ. 1፡13፤ ኤፌ. 2፡19፤ 3፡15
5. ኤፌ. 2፡19፤ 3፡15
6. የሐዋ. 2፡47

3. ስለዚህ ለምትታየው ለዓለም አቀፊቱ ቤተ ክርሲቲያን፣ በዚህ ሕይወት፣ ዓለም እስከሚፈጸምበት ጊዜ ድረስ፣ ቅዱሳንን እንድትሰበስብባቸውና እንድታንጽባቸው ክርስቶስ አገልግሎትን፥ ቃሉን፥ ሥርዓትን ሰጥቷታል። ራሱም አብሮ በመገኘትና በመንፈሱ

እንደተስፋው፣ በቃሉ መሠረት፣ የሰጣትን አገልግሎት ለዚህ ዓላማ እንዲበቁ ያደርጋቸዋል።[7]

7. 1ኛ ቆሮ. 12፡28፤ ኤፌ. 4፡11–13፤ የሐዋ. 28፡19፥20፤ ኢሳ. 59፡12

4. ይህች የምትታየው ዓለም አቀፊቱ ቤተ ክርስቲያን አንዳንድ ጊዜ በበለጠ ስትታይ፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ ባነሰ የምትታይበት ወቅት አለ።[8] የዚህች ዓለም አቀፍ ቤተ ክርስቲያን አባላት፣ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በውስጣቸው የወንጌል ትምህርት እንደመሠጠቱና ተቀባይነት እንደማግኘቱ መጠን፥ ምሥጢራት እንደመፈጸማቸው መጠን፥ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ እንደቃሉ እንደመካሄዱ መጠን፣ ንጽሕናቸውም እንዲሁ ይሆናል።[9]

8. ሮሜ 11፡3–5፤ የሐዋ. 9፡31፤ 2፡41፥47፤ 18፡8–10
9. የሐዋ. 2፡41፥42፥ 1ኛ ቆሮ. 5፡6፥7፤ ራእ. ምእራፍ 2ና 3።

5. በምድር ላይ እጅግ ንጹሕ የተባሉት አብያተ ክርስቲያናት እውነትም ስሕተትም ተደብልቆ ይገኝባቸዋል።[10] አንዳንዶችም ፍጹም ስለተበላሹ፣ የክርስቶስ አብያተ ክርሲያናት መሆናቸው ቀርቶ፣ የሰይጣን ምኩራብ ሆነዋል።[11] ይህም ሆኖ ግን በምድር ላይ እግዚአብሔርን እንደ ፈቃዱ የምታመልክ ቤተ ክርስቲያን መኖሯ አይቀርም።[12]

10. 1ኛ ቆሮ. 13፡12፤ ራእ. ምእራፍ 2ና 3፤ ማቴ. 13፡24–30፥47
11. ማቴ. 23፡37–39፤ ሮሜ 11፡18–22
12. ማቴ. 16፡18፤ 28፡19፥20፤ መዝ. 45፡16፥17፤ 72፡17፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡51፥52፤ 1ኛ ተሰ. 4፡17

6. ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በስተቀር ሌላ የቤተ ክርስቲያን እራስ ማንም የለም።[13] የሮማም ጳጳስ በምንም መልክ ቢሆን የቤተ ክርስቲያን ራስ ሊሆኑ አይችሉም።[14]

13. ቆላ. 1፡18፤ ኤፌ. 1፡22
14. ማቴ. 23፡8–10፤ 1ኛ ጴጥ. 5፡2–4

ምዕራፍ ሃያ ስድስት
የቅዱሳን አንድነት

1. ራስ ከሆናቸው ከክርስቶስ ጋር የተጣመሩ ቅዱሳን ሁሉ፤ ክርስቶስን በመንፈስ ቅዱስና በእምነት በጸጋው፥ በሥቃዩ፥ በሞቱ፥ በትንሣኤው፥ በክብሩ ይተባበሩታል።[1] እርስ በእርሳቸውም በፍቅር በመተሳሰር፤ ከእያንዳንዳቸው ስጦታና ጸጋ፤ ኅብረት አላቸው።[2] ስለዚህም በግልም ሆነ በኅብረት፥ ለሥጋና ለነፍስ ጠቃሚ የሆኑትን ተገቢ አገልግሎቶች እርስ በእርሳቸው ሊሰጣጡ ግዳጅ አለባቸው።[3]

1. 1ኛ ዮሐ. 1፡3፤ ኤፌ. 3፡16–18፤ 2፡5፥6፤ ዮሐ. 1፡16፤ ፊል. 3፡10፤ ሮሜ 6፡5፥6፤ 8፡17፤ 2ኛ ጢሞ. 2፡12
2. ኤፌ. 4፡15፥16፤ 1ኛ ቆሮ. 12፡7፥12፤ 3፡21–23፤ ቆላ. 2፡19
3. 1ኛ ተሰ. 5፡11፥14፥ ሮሜ 1፡11፥12፥14፤ 1ኛ ዮሐ. 3፡16–18፤ ገላ. 6፡10

2. ቅዱሳን በኅብረት የእግዚአብሔርን አምልኮ በመፈጸም መትጋት፥ የጋራ በልጽግና የሚያስከትሉትን የመንፈሳዊ አገልግሎቶች ማካሄድ፥ እንደ አቅማቸውና እንደ አሰፈላጊነቱ የቁሳቁስ ችጋራቸውን ለማስወገድ መጣጣርና የተቀደሰ አንድነትና ኅብረት ለማድረግ፤ በእምነታቸው ይገደዳሉ።[4] ይህም ኅብረት እግዚአብሔር እንዳስቻለ መጠን፤ በየቦታው ሁሉ የጌታ የኢየሱስን ስም ለሚጠሩ ሁሉ ሊሰጥ ይገባዋል።[5]

4. ዕብ. 10፡24፥25፤ የሐዋ. 2፡42፥46፤ ኢሳ. 2፡3፤ 1ኛ ቆሮ. 11፡20
5. 1ኛ ዮሐ. 3፡17፤ 2ኛ ቆሮ. ምእራፍ 8ና 9፤ የሐዋ. 11፡29፥30፤ 2፡44፥45

3. ቅዱሳን ከክርስቶስ ጋር ያላቸው ኅብረት በምንም ዓይነት የአምላክነቱን ባሕርይ እንዲካፈሉ አያደርጋቸውም፤ ወይም በምንም ዓይነት ከክርስቶስ ጋር እኩል አያደርጋቸውም። ከነዚህ ሁለት ስሕተቶች ውስጥ አንዱንም እንኳ ማሰብ ትልቅ በደል ነው፤ ትልቅም ስድብ ነው።[6] እንዲሁም ቅዱሳን ከእርስ በእርሳቸው ጋር ያላቸው ኅብረት፤ በየግል ያላቸውን የሐብት መብት የሚቀማ ወይም የሚሻማ አይደለም።[7]

6. ቆላ. 1፡18፥19፤ 1ኛ ቆሮ. 8፡6፤ መዝ. 45፡6፥7፤ ዕብ. 1፡6–9፤ ዮሐ. 1፡14፤ 20፡17
7. ዘጸ. 20፡15፤ ኤፌ. 4፡28፤ የሐዋ. 5፡4

ምዕራፍ ሃያ ሰባት
ምሥጢራት

1. ምሥጢራት ቅዱስ የሆኑ የሕይወት ቃል ኪዳን ምልክቶችና ማኅተሞች ናቸው።[1] የመሠረታቸውም በቀጥታ ራሱ እግዚአብሔር ነው።[2] ዓላማቸውም ከርስቶስንና የሚሰጠንን ጸጋ ለማመልከትና በክርስቶስ ያለንን የእኛ የሆነውን ሁሉ ለማረጋገጥ ነው።[3] እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባሉትና በዓለም ውስጥ ባሉት መካከል የሚታይ ልዩነትን ለማስቀመጥ ነው።[4] በቤተ ክስቲያን ክልል ውስጥ ያሉትንም፣ እንደቃሉ መሠረት በክርስቶስ እግዚአብሔርን እንዲያገለግሉ በጥብቅ ያሳስቧቸዋል።[5]

1. ሮሜ 4፡11፤ ዘፍ. 17፡7፥10፡11
2. ማቴ. 28፡19፤ 1ኛ ቆሮ. 11፡23
3. ሮሜ 6፡3፥4፤ ቆላ. 2፡12፤ 1ኛ ቆሮ. 10፡16፤ 11፡25፥26፤ ገላ. 3፡27
4. ዘጸ. 12፡48፤ ዘፍ. 34፡14፤ 1ኛ ቆሮ. 10፡21
5. ሮሜ 6፡3፥4 ገላ. 3፡27፤ 1ኛ ጴጥ. 3፡21፤ 1ኛ ቆሮ. 10፡16፤ 5፡7፥8

2. በእያንዳንዱ ምሥጢር ውስጥ፣ በምልክቱና ምልክቱ በሚያመለክተው መካከል፣ ሥጋዊ ያልሆነ ነገር፥ ግን መንፈሳዊ የሆነ የምሥጢር ኅብረት ስለአለ፣ ያንዱ ስምና ውጤት ለሌላው ተላልፎ እናየዋለን።[6] (ኅብስቱን፥ ሥጋዬ፣ ወይኑን፥ ደሜ ይላቸዋል)

6. ዘፍ. 17፡10፤ ማቴ. 26፡27፥28፤ 1ኛ ቆሮ. 10፡16–18

3. በትክክል በሚሰጡ ምሥጢራት በኩል የሚቀርበው ጸጋ፣ ከራሳቸው ከምሥጢራቱ የሚመነጭ አይደለም። እንዲሁም፣ ምሥጢራቱ ጠቃሚ የሚሆኑት፣ በሚሰጣቸው ሰው መንፈሳዊነት ወይም ፍላጎት ላይ የተመረኮዘ አይደለም።[7] ምሥጢራት ጸጋ አስተላላፊና መሣሪያዎች እንዲሆኑ፣ ወሳኙ መንፈስ ቅዱስና[8] የሚመሠርታቸው የእግዚአብሔር ቃል ናቸው። ይህም የእግዚአብሔር ቃል እንዴት በሥራ ላይ መዋል እንዳለባቸው መምሪያ ይሰጣል፤ በትክክለኛ መንገድ ለሚቀብሏቸውም የበረከትን ተስፋ ያበስራል።[9]

7. ሮሜ 2፡28፥29፤ 1ኛ ጴጥ. 3፡21
8. 1ኛ ቆሮ. 12፡13
9. ማቴ. 26፡26–28፤ 28፡19፥20፤ ሉቃ. 22፡19፥20፤ 1ኛ ቆሮ. 11፡26

4. በክርስቶስ በጌታችን በወንጌል የተመሠረቱ ሁለት ምሥጢራት ብቻ አሉ። እነሱም ጥምቀትና ቅዱስ ቁርባን ናቸው። በቃሉ መሠርት በሥነ ሥርዓት ቅስና[2] በተቀበለ መጋቢ እንጂ በሌላ በማንም ሊሰጡ አይገባም።[10]

10. ማቴ. 28፡19፤ 1ኛ ቆሮ. 11፡20፥23፤ 4፡1፤ ኤፌ. 4፡11፥12

5. የብሉይ ኪዳን ምሥጢራት መንፈሳዊ ነገሮችን ያመለክቷቸውና ይመስሏቸው እንደነበር ሁሉ፣ እንዲሁም አሁን የአዲስ ኪዳን ምሥጢራት እንደዚያው ያደርጋሉ። የሁለቱም ኪዳኖች ምሥጢራት አሠራር አንድ ዓይነት ነው።[11]

11. 1ኛ ቆሮ. 10፡1–4፤ ሮሜ 4፡11፤ ቆላ. 2፡11፥12

ምዕራፍ ሃያ ስምነት
ጥምቀት

1. ጥምቀት በጌታችን በክርስቶስ የተመሠረተ የአዲስ ኪዳን ሥርዓት ነው።[1] ጥምቀት የሚጠመቀውን በምትታየው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለማስገባት ብቻ ሳይሆን፣[2] ተጠማቂው የሕይወት ቃል ኪዳን ወራሽ መሆኑን፥[3] ከክርስቶስ ጋር ተባባሪነቱን፥[4] ዳግመኛ መወለዱን፥[5] የኃጢአት ስርየት መቀበሉን፥[6] በአዲስ ሕይወት ለመራመድ በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ሕይወቱን ያስረከበ መሆኑን ለማረጋገጥ፣ ምልክትና ማኅተም እንዲሆን ነው።[7] ጥምቀት በራሱ በክርስቶስ የተመሠረተ ,ው፤ በክርስቶስም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሊጸና ይገባዋል።[8]

1. ማቴ. 28፡19
2. 1ኛ ቆሮ. 12፡13፤ ገላ. 3፡27፥28
3. ሮሜ 4፡11፤ ቆላ. 2፡11፥12
4. ገላ. 3፡27፤ ሮሜ 6፡5
5. ዮሐ. 3፡5፤ ቲቶ 3፡5
6. ማር. 1፡4፤ የሐዋ. 2፡38፤ 22፡16

---

[2]ቋሲ የምንለው ለቃሉ አገልግሎት እጅ በመጫን የተለየና ሥልጣንን የተቀበለ የቤተ ክርስቲያን ሹም ነው። ቤተ ክርስቲያንን ቃሉን ይሰብካል፥ ምሥጢራትን ይሰጣል፥ እንዲሁም ከሽማግሌዎች ጋር በመተባበር ቤተ ክርስቲያንን ያስተዳድራል።

7. ሮሜ 6፡3፥4
8. ማቴ. 28፡19፥20

2. ለዚህ ምሥጢር አገልግሎት የሚውለው ውሃ ሆኖ፣ ተጠማቂው በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም፣ ለወንጌል ሥራ በሥርዓት በተሾመ የቃሉ አገልጋይ (ቄስ) ይጠመቃል።[9]

9. የሐዋ. 10፡47፤ 8፡36፥38፤ ማቴ. 28፡19

3. ተጠማቂውን በውሃ ውስጥ መንከር አስፈላጊ ስላይደለ፣ ጥምቀት በማፍሰስና በመርጨትም ሊፈጸም ይችላል።[10]

10. ዕብ. 9፡10፥13፥19፥21፤ ማር. 7፡2–4፤ ሉቃ. 11፡38
4. መጠመቅ የሚገባቸው በክርስቶስ አምነው የሚታዘዙት[11] ብቻ ሳይሆኑ፣ ሁለቱም ወይም አንዱ ብቻ አማኝ ከሆኑ ወላጆች የሚወለዱ ሕፃናት ጭምር ናቸው።[12]

11. የሐዋ. 2፡41፤ 8፡12፥13፤ 16፡14፥1512. ዘፍ. 17፡7–14፤ ገላ. 3፡9፥14፤ ቆላ. 2፡11፥12፤ 2፡38፥39፤ ሮሜ 4፡11፥12፤ ማቴ. 19፡13፤ 28፡19፤ ማር. 10፡13–16፤ ሉቃ. 18፡15–17፤ 1ኛ ቆሮ. 7፡14

5. ምንም እንኳ ይህንን ሥርዓት መናቅ ወይም መተው ትልቅ ኃጢአት ቢሆንም[13]፤ ያለጥምቀት ሰው የማይድንና ዳግም የማይወለድ እስኪሆን ድረስ[14] ወይም የተጠመቁ ሁሉ ያለጥርጥር ዳግመኛ ተወልደዋል ለማለት እስከምንደፍር ድረስ ጸጋና ደኅንነት ከጥምቀት ጋር ያልመለያየት አልተቆራኙም።[15]

13. ዘፍ. 17፡14፤ ማቴ. 28፡19፤ የሐዋ. 2፡38፤ ሉቃ. 7፡30
14. ሮሜ 4፡11፤ የሐዋ. 10፡2፥4፥22፥31፥45፥47
15. የሐዋ. 8፡13፥23

6. የጥምቀት መንፈሳዊ ፍሬ ጥምቀቱ በተፈጸመ ወቅት ላይገኝ ይችላል።[16] ይህም ሆኖ ሳለ ግን ሥነ ሥርዓቱ በትክክል ሲፈጸም ለአዋቂም ሆነ ለሕፃን ያ ጸጋ በራሱ በእግዚአብሔር የፈቃድ ምክርና ራሱ በወደደው ጊዜ ለጠራቸው ይፈጸምላቸዋል። ለእነርሱ በመንፈስ ቅዱስ ሥራ በተስፋው የተሰጠው ጸጋ በሥርዓቱ በውጭ ዓይን መታየት ብቻ ሳይሆን በእርግጥ በልባቸውም ይሰጣቸዋል።[17]

16. ዮሐ. 3፡5፥8
17. ሮሜ 6፡3–6፤ ገላ. 3፡27፤ 1ኛ ጴጥ. 3፡21፤ የሐዋ. 2፡38፥41

7. የጥምቀት ሥርዓት ለአንድ ሰው አንድ ጊዜ ብቻ መፈጸም አለበት።[18]

18. ሮሜ 6፡3–11

ምዕራፍ ሃያ ዘጠኝ
ቅዱስ ቁርባን

1. በዚያች አልፎ በተሰጠባት ምሽት የጌታ እራት ተብሎ የሚጠራውን የሥጋውንና የደሙን ምሥጢር ጌታችን መሠረተ። ዳግም እስከሚመለስ ድረስ በመሠረታት ቤተ ክርስቲያን ሁልጊዜ እንዲጠበቅ አዘዘ። ክርስቶስ በሞቱ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ እንደሠዋ ይህ ሥርዓት የሁልጊዜ መታሰቢያው ነው። በተጨማሪም ይህ ምሥጢር ለእውነተኛ አማኞች የክርስቶስን የመሥዋዕት ፍሬ፥ በክርስቶስ እድገታቸውንና ከክርስቶስ መመገባቸውን፥ ለክርስቶስ ለመታዘዝ ያለባቸውን ዕዳ ያትምላቸዋል። ከክርስቶስ ጋር ላላቸው ኅብረትና የክርስቶስ መንፈሳዊ አካል አባሎች ስለሆኑ እርስ በእርሳቸው ላላቸው ኅብረት ማስረጃና ማረጋገጫ ይሆናቸዋል።[1]

1. 1ኛ ቆሮ. 11፡23–26፤ 10፡16፥17፤ 12፡13

2. በዚህ ምሥጢር ክርስቶስ በተደጋጋሚ መሥዋዕት ሆኖ ለአብ አይቀርብም። በፍጹምም ለሕያዋንና ለሙታን ኃጢአት ማስተስሪያ የሚቀርብ መሥዋዕት አይደለም።[2] ግን ለዚያ ክርስቶስ በመስቀል ላይ አንድ ጊዜ ለፈጸመው አንዱ መሥዋዕት የመታሰቢያ መንፈሳዊ ቁርባን ሆኖ ለእግዚአብሔር ማመስገኛ ይቀርባል።[3] ስለዚህ የሮማ ቤተ ክርስቲያን ይህንን መሥዋዕት አድርጋ ማቅረቧ አስጸያፊ ነው። ይህ ሁኔታ ያንን አንዱን የክርስቶስን መሥዋዕት ተቀናቃኝ በመሆን ያበላሻል። ለተመረጡትም የኃጢአት ማስተስሪያ የሚሆነው አንዱ የክርስቶስ መሥዋዕት ብቻ ነው።[4]

2. ዕብ. 9፡22፥25፥26፥28፤ 10፡10–14
3. 1ኛ ቆሮ. 11፡24–26፤ ማቴ. 26፡26፥27፤ ሉቃስ 22፡19፥20
4. ዕብ. 7፡23፥24፥27፤ 10፡11፥12፥14፥18

3. ጌታ ኢየሱስ በዚህ ምሥጢር ሥርዓት መሥራች ቃሉን ለሕዝቡ እንዲሰብኩ፥ እንዲጸልዩ፥ ኅብስቱንና ወይኑን በመባረክ ከተራነት ወደ ቅዱስ አገልግሎት እንዲለዩአቸው፥ ኅብስቱን እንዲቆርሱ፥

እራሳቸው በመካፈል ጽዋውንም አንስተው ለምእመናኑ እንዲሰጡ[5] ቀሳውስትን ወይም የቃሉን መጋቢያንን ሾሟቸዋል። የቁርባኑ ሥርዓት በሚካሄድበት ጊዜ በቤተ ክርስቲያኑ ጉባኤ ያልተገኙ ከቁርባኑ መካፈል አይችሉም።[6]

5. 1ኛ ቆሮ. 10፡16
6. ማቴ. 26፡27፥28፤ ማር. 14፡23፤ 1ኛ ቆሮ. 11፡25-29

4. በግል ቅዱስ ቁርባንን መቀበል፥ የቃሉ አገልጋይ ወይም ሌላ ሰው በራሱ ብቻውን ቁርባንን መቀበል፥[7] እንዲሁም ከምእመናኑ ጽዋውን መንፈግ፥[8] ጎብስቱንና ጽዋውን ማምለክ፥ ጎብስቱንና ጽዋውን ወደላይ ከፍ እያደረጉ ማዞርና የአምልኮ ስግደት መስጠት፥ በቃሉ ላልተፈቀደ የሃይማኖት ተግባር ላይ ማዋል፥ እነዚህ ሁሉ የቅዱስ ቁርባንን ባሕርይና ከርስቶስ ቁርባንን ሲመሠርት ያቀደውን ዓላማ ይቃወማሉ።[9]

7. 1ኛ ቆሮ. 10፡16
8. ማቴ. 26፡27፥28፤ ማር. 14፡23፤ 1ኛ ቆሮ. 11፡25-29
9. ማቴ. 15፡9

5. ለዚህ ተግባር የተለዩት ጎብስቱና ወይኑ በክርስቶስ የተመሠረቱ እንደመሆናቸው መጠን ከክርስቶስ ሥቃይ ጋር እውነተኛ ዝምድና አላቸው። ይህ ዝምድና ግን መንፈሳዊ ብቻ ነው። በዚህ ዘምድና ምክንያት ጎብስቱና ወይኑ በሚመስሉት በክርስቶስ ሥጋና ደም ይሰየማሉ።[10] ይሁን እንጂ ባሕርያቸው ሳይቀየር እንደበፊቱ ያው ጎብስትና ወይን ናቸው።[11]

10. ማቴ. 26፡26-28
11. 1ኛ ቆሮ. 11፡26-28፤ ማቴ. 26፡29

6. ጎብስቱና ወይኑ በመጋቢው መባረክ ወይም በሌላ መንገድ ወደ ፍጹም የክርስቶስ ሥጋና ደም ይለወጣሉ የሚለው ትምህርት ለመጽሐፍ ቅዱስ ቀርቶ ለሰው አእምሮና ግምት እንኳ አስጸያፊ ነው። ይህ ትምህርት የቅዱስ ቁርባንን ትርጉም ማበላሸት ብቻ ሳይሆን ለብዙ ዓይነት ከንቱ አምልኮና ጣዖት መነሻ ሆኗል።[12]

12. የሐዋ. 3፡21፤ 1ኛ ቆሮ. 11፡24-26፤ ሉቃ. 24፡6፥39

7. ምእመናን በትክክለኛ መንገድ ከጎብስቱና ከወይኑ በአፋቸው ሲካፈሉ[13] በእምነት ደግሞ በእርግጥ፥ በሥጋ ሳይሆን በመንፈስ፥

የተሰቀለውን ክርስቶስን ይመገባሉ። ከሞቱም የሚገኘውን በረከት ሁሉ ይቀበላሉ። በሚታይና በሚጨበጥ መንገድ ሳይሆን፣ ወይም ከኅብስቱና ከወይኑ ጋር በሥጋ በመዛመድ ሳይሆን፣ ኅብስቱና ወይኑ ለምእመናን እጅ፥ ዓይንና አፍ እንደሚቀርቡላቸው ሁሉ፣ እንዲሁም ደግሞ የክርስቶስ ሥጋና ደም ከኅብስቱና ከወይኑ ጋር በመንፈሳዊ ኅብረት ተቆራኝቶ ለእምነታቸው ይቀርብላቸዋል።[14]

13. 1ኛ ቆሮ. 11፡28
14. 1ኛ ቆሮ. 10፡16፤ 10፡3፥4

8. ምንም እንኳ የማያውቁና በኃጢአት የሚኖሩ ሰዎች በውጭ ከኅብስቱና ከወይኑ ቢካፈሉም ኅብስቱና ወይኑ የሚመስሉትን መንፈሳዊዩን በረከት አይቀበሉም። ነገር ግን በማይገባ መንገድ በመካፈላቸው የጌታ ሥጋና ደም ባለዕዳ ይሆናሉ፤ ለፍርድም ይሆንባቸዋል። ስለዚህ የማያውቁና በኃጢአት የሚኖሩ ከክርስቶስ ጋር ኅብረት ሊኖራቸው እንደማይችል ሁሉ፣ ለክርስቶስ ገበታም በቂ አይደሉም። በኃጢአት እየኖሩ ሳሉ ከቅዱስ ቁርባን ቢካፈሉ[15] ወይም ወደ ገበታው እንዲቀርቡ ቢደረጉ[16] በክርስቶስ ላይ ታላቅ በደል ይፈጽማሉ።

15. 1ኛ ቆሮ. 11፡27–29፤ 10፡21፤ 2ኛ ቆሮ. 6፡14–16
16. 1ኛ ቆሮ. 4፡11፥12፤ 12፡28፤ ማቴ. 12፡28፤ 28፡18–20፤ ዮሐ. 18፡36

ምዕራፍ ሠላሳ
የቤተ ክርስቲያን ቅጣት

1. የቤተ ክርስቲያን ንጉሥና ራስ ጌታ ኢየሱስ ከመንግሥት በተለየ መልኩ በቤተ ክርስቲያን መሪዎች እጅ ለቤተ ክርስቲያን አስተዳደርን መሥርቷል።[1]

1. ኢሳ. 9፡6፥7፤ ቆላ. 1፡18፤ 1ኛ ጢሞ. 5፡17፤ 1ኛ ተሰ. 5፡12፤ የሐዋ. 20፡17፥28፤ ዕብ. 13፡7፥17፥24፤ ኤፌ. 4፡11፥12፤ 1ኛ ቆሮ. 12፡28፤ ማቴ. 28፡18–20፤ ዮሐ. 18፡36

2. የመንግሥተ ሰማይ መክፈቻ ለእነዚህ የቤተ ክርሲትያን አስተዳዳሪዎች ተሰጥቷል። ስለዚህም በኃጢአት ለማሰርና ኃጢአትን ለመፍታት ሥልጣን አላቸው። ይህም ማለት ንስሐ ለማይገቡ በቃሉና በቤተ ክርስቲያን ቅጣት መንግሥተ ሰማይን

ለመዝጋት፥ ንስሐ ለሚገቡ በወንጌል አገልግሎትና ቅጣትን በማንሳት መንግሥተ ሰማይን ለመክፈት ይችላሉ።[2]

2. ማቴ. 16፡19፤ 18፡17፥18፤ ዮሐ. 20፡21–23፤ 2ኛ ቆሮ. 2፡6–8

3. ለጊዜው በጎጢአት የወደቁ ወገኖችን ለመመለስና ገንዘብ ለማድረግ፥ ሌሎች ተመሳሳይ ጥፋት እንዳይፈጽሙ ለማስጠንቀቅ፥ መላው ሊጥ እንዳይቦካ እርሾውን ለማስወገድ፥ የክርስቶስን ክብርና የወንልን ቅዱስ እምነት ለመጠበቅ፥ የእግዚአብሔርን ፍርድ ለመከላከል አጥፊ ክርስቲያኖችን ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ልትቀጣ ያስፈልጋታል።[3] ቃል ኪዳኑንና የቃል ኪዳኑ ማኅተም በመጥፎዎችና በአመጸኞች ሲረከስ ቤተ ክርስቲያን ችላ ብትል፥ የእግዚአብሔር ቁጣ በራሷም ላይ ሊወርድባት ይችላል።

3. 1ኛ ቆሮ. 5፡1–13፤ 1ኛ ጢሞ. 5፡20፤ ማቴ. 7፡6፤ 1፡20፤ 11፡27–34፤ ይሁ. 23

4. ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ዓላማዎች በበለጠ እንዲከናወኑ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቅጣት እንደጥፋቱና እንደአጥፊው በደል መጠን በመጀመሪያ በተግሣጽ፥ ከዚያም ለተወሰነ ጊዜ ከቅዱስ ቁርባን በማግለል፥ ከዚያም ጭራሽ ከቤተ ክርስቲያን አባልነት በማግለል ሊካሄድ ይገባል።[4]

4. 1ኛ ተሰ. 5፡12፤ 2ኛ ተሰ. 3፡6፥14፥15፤ 1ኛ ቆሮ. 5፡4፥5፥13፤ ማቴ. 18፡17፤ ቲቶ 3፡10

ምዕራፍ ሠላሳ አንድ
ሲኖዶስና ጉባኤ

1. ቤተ ክርስቲያን በሚገባ እንድትተዳደርና እንድትታነጽ ሲኖዶስና ጉባኤ ያስፈልጋሉ።[1] እነዚህን ሲኖዶሶችና ጉባኤዎች ለመመሥረት የሚችሉ፤ በየአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን፥ ለማፍረስ ሳይሆን ለመገንባት፥ በክርስቶስ የተሾሙት መሪዎች ናቸው።[2] እነዚህ መሪዎች ለቤተ ክስቲያን ያስፈልጓታል ብለው በገመቱት ቁጥር ሲኖዶሶችና ጉባኤዎች ሊሰባሰቡ ይገባል።[3]

1. የሐዋ. 15፡2፥4፥6
2. የሐዋ. 15፡1–35
3. የሐዋ. 15፡1–35፤ 20፡17

2. እምነትን በሚመለከት፥ ክርክርና ሕሊናን በሚመለከት፥ እንዲሁም የአምልኮ ስብሰባዎች በሚገባ እንዲካሄዱና ቤተ ክርስቲያን በሚገባ እንድትተዳደር፥ ሕግንና መመሪያን ለማውጣት፥ በተዛቡ ውሳኔዎች ምክንያት የሚነሱትን አቤቱታዎች ሰምቶ ተገቢ ፍርድ ለመስጠት፣ መብት ያላቸው ሲኖዶስና ጉባኤዎች ናቸው። ሲኖዶስና ጉባኤዎች የሚያስተላልፉአቸው ውሳኔዎች ከእግዚአብሔር ቃል ጋር በመስማማታቸው ብቻ ሳይሆን፣ በቃሉ በመመሥረት ሥልጣን ያላቸው ሥርዓቶች ስለሆኑ፣ በአክብሮት ሊቀበሏቸው ይገባል።[4]

4. የሐዋ. 15፡15፥19፥24፥27-31፤ 16፡4፤ ማቴ. 18፡17-20

3. ከሐዋሪያት ዘመን ጀምረው የነበሩት፥ ልዩ የሆኑም ሆኑ ጠቅላላ ሲኖዶሶችና ጉባኤዎች፥ ሊሳሳቱ ይችላሉ፤ ብዙዎቹም ተሳስተዋል። ስለዚህ ሲኖዶስና ጉባኤ እምነትንና ሕይወትን እንዲረዱ እንጂ እንዲገዙ አልተፈቀደም።[5]

5. ኤፌ. 2፡20፤ የሐዋ. 17፡11፤ 1ኛ ቆሮ. 2፡5፤ 2ኛ ቆሮ. 1፡24፤ ኢሳ. 8፡19፥20፤ ማቴ. 15፡9

4. ሲኖዶስና ጉባኤ የሚመለከታቸውና የሚወስኗቸው ነገሮች የቤተ ክርስቲያን ጉዳዮች ብቻ ሊሆኑ ይገባል። ከሥልጣናቸው ውጭ ስለሆኑ ነገሮች በትሕትና አቤቱታና ልመና ከማቅረብ በስተቀር ወይም በመንግሥት ባለሥልጣን በተጠየቁ ጊዜ ሕሊናን ለማሳረፍ ምክርን ለመስጠት ካልሆነ በስተቀር በመንግሥት ጉዳዮች ጣልቃ መግባት የለባቸውም።[6]

6. ሉቃ. 12፡13፥14፤ ዮሐ. 18፡36፤ ማቴ. 22፡21

ምዕራፍ ሠላሳ ሁለት
ከሞት በኋላ የሰዎች ሁኔታና የሙታን ትንሣኤ

1. ሰዎች ከሞቱ በኋላ *ሥጋ* ወደ አፈር ይመለሳል፤ መበስበስንም ያያል።[1] ነፍሳቸው ግን አትሞትም ወይም አትተኛም። የማትሞትም ስለሆነች ወዲያውኑ ወደሰጣት ወደ እግዚአብሔር ትመለሳለች።[2] የጻድቃን ነፍስ በዚያን ጊዜ በቅድስና ብፁዕ በመሆን ወደ

መንግሥተ ሰማይ ትሄዳለች። እዚያም የእግዚአብሔርን ፊት በብርሃንና በክብር እያየች የሥጋዋን ትንሣኤ ተጠባበቃለች።[3] የኃጢአተኞች ነፍስ ግን ወደ ሲኦል ትጣላለች። በሥቃይና በፍጹም ጨለማ ለታላቁ የፍርድ ቀን ተጠበቃለች።[4] ከእነዚህም ከሁለቱ ቦታዎች በስተቀር ከሥጋ ተለይተው ለሄዱ ነፍሳት ሌላ ቦታ አለ ብሎ መጽሐፍ ቅድስ አይናገርም።

1. ዘፍ. 3፡19፤ የሐዋ. 13፡36
2. ሉቃ. 23፡43፤ መክ. 12፡7
3. ዕብ. 12፡23፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡1፥6፥8፤ ፊል. 3፡21፤ ኤፌ። 4፡10፤ ሮሜ 3 8፡23
4. ሉቃ. 16፡23፥24፤ የሐዋ. 1፡25፤ ይሁ. 6፥7፤ 1ኛ ጴጥ. 3፡19

2. በመጨረሻው ቀን በሕይወት ያሉት ምእመናን አይሞቱም ነገር ግን ይለወጣሉ።[5] በክርስቶስ የሆኑ ሙታን ሁሉ ሥጋቸው ከነፍሳቸው ጋር ዳግመኛ ለዘላለም በመገናኘት በዚያው በነበራቸው ሥጋ በክብር ተለውጠው ይነሣሉ።[6]

5. 1ኛ ተሰ. 4፡17፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡51፥52
6. ዮሐ. 5፡25–29፤ የሐዋ. 24፡15፤ ኢዮ. 19፡26፥27፤ ዳን. 12፡2፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡42–44

3. የኃጥአን ሥጋ በክርስቶስ ኃይል ለውርደት ይነሣል። የጻድቃን ሥጋ በመንፈስ ቅዱስ የክርስቶስን የክብር ሥጋ መስሎ ለክብር ይነሣል።[7]

7. የሐዋ. 24፡15፤ ዮሐ. 5፡25–29፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡43፤ ፊል. 3፡21

ምዕራፍ ሠላሳ ሦስት
የመጨረሻው ፍርድ

1. እግዚአብሔር በዓለም ላይ ከአብ ኃይልና ፍርድ በተሰጠው በኢየሱስ ክርስቶስ በጽድቅ የሚፈርድበት ቀን ቀጥሯል።[1] በዚያ ቀን ያመፁት መላእክት ብቻ ሳይሆኑ[3]፣ በዓለም ላይ የኖሩ ሰዎች ሁሉ ስለ አሳባቸው፥ ስለ ቃላቸው፥ ስለ ሥራቸው መልስ ለመስጠት፤ በሕይወታቸው ለሠሩት መልካምም ቢሆን መጥፎ፤ እንደ ሥራቸው ብድራትን ለመቀበል በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ይቀርባሉ።[4]

1. የሐዋ. 17፡31
2. ዮሐ. 5፡22፥27
3. ይሁ. 6 2ኛ ጴጥ. 2፡4
4. 2ኛ ቆሮ. 5፡10፤ መክ. 12፡14፤ ሮሜ 2፡16፤ 14፡10፥12፤ ማቴ. 12፡36፥37

2. ይህን ቀን ሊቀጥር የእግዚአብሔር ዓላማ የምሕረቱን ክብር ለዘላለም ሕይወት በተመረጡት ለመግለጽ፤ የፍርዱን ክብር መጥፎዎችና ዓመፀኞች ስለሆኑ ባልተመረጡት ለመግለጽ ነው። በዚያን ጊዜ ጻድቃን ወደ ዘለዓለም ሕይወት ሄደው ሙሉ ደስታንና እረፍትን ከጌታ ፊት ሊቀበሉ፣ ነገር ግን እግዚአብሔርን የማያውቁት ክፉዎችና የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ያልታዘዙት በዘለዓለም ጥፋት ከጌታ ፊትና ከኃይሉ ክብር ርቀው ወደ ዘለዓለም ሥቃይ ይጣላሉ።5

5. ማቴ. 25፡31–46፤ 25፡21፤ ሮሜ 2፡5፥6፤ 9፡22፥23፤ የሐዋ. 3፡19፤ 2ኛ ተሰ. 1፡7–10

3. ሰዎችን ሁሉ ከኃጢአት ለመከላከልና ጻድቃን በመከራቸው እንዲጽናኑ ለማድረግ በእርግጥ የፍርድ ቀን እንደሚኖር ክርስቶስ እንደሚያረጋግጥልን ሁሉ6፤ እንዲሁም ደግሞ ሥጋዊ መመኪያቸውን ሁሉ ትተው ጌታ በየተኛው ሰዓት እንደሚመጣ አያውቁምና ሁልጊዜ እንዲጠብቁ፣ እንዲሁም «ጌታ ኢየሱስ ቶሎ ና» ለማለት ሁልጊዜ የተዘጋጁ እንዲሆኑ፣ ያ ቀን መቼ እንደሚሆን ከሰዎች ተሰውሯል።7

6. 2ኛ ጴጥ. 3፡11፥14፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡10፥11፤ 2ኛ ተሰሎ. 1፡5–7፤ ሉቃ. 21፡28፤ ሮሜ 8፡23–25
7. ማቴ. 24፡36፥41–44፤ ማር. 13፡35–37፤ ሉቃ. 12፡35፥36፤ ራእ. 22፡20።

አጭሩ ካታኪዝም

በጥያቄና በመልስ የተዘጋጀ
መንፈሳዊ ትምህርት

ጥያቄ 1

የሰው ዋና ዓላማ ምንድነው?

መልስ

የሰው ዋና ዓላማ እግዚአብሔርን ማክብርና በእርሱ ለዘላለም መደሰት ነው።

መዝ. 73፡24-26፤ ሮሜ 11፡36፤ 1ኛ ቆሮ. 10፡3

ጥያቄ 2

እግዚአብሔርን እንዴት ባለ አኳኋን እያከበርነውና በእርሱም እየተደሰትን እንድንኖር የገለጠልን አሱ የሰጠን መሪ ሥርዓት ምንድነው?

መልስ

እግዚአብሔርን እንዴት ባለ አኳኋን እያከበርነውና በእርሱም እየተደሰትን እንድንኖር የገለጠልን እርሱ የሰጠን መሪ ሥርዓት በብሉይና በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት የሚገኘው የእርሱ ቃል ብቻ ነው።

ሉቃ. 16፡31፤ 24፡24፥40፤ ዮሐ. 15፡11፤ ገላ. 1፡-9፤ 2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ 2ኛ ጴጥ. 3፡2፥15-16

ጥያቄ 3

መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረው ዋና ነገር ምንድነው?

መልስ

መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረው ዋና ነገር ሰው ስለ እግዚአብሔር ምን ማመን እንዳለበትና እግዚአብሔር ከሰው የሚፈልገው አገልግሎት ምን እንደሆነ ነው።

ዮሐ. 5፡39፤ 20፡31፤ ሮሜ 15፡4፤ 1ኛ ቆሮ. 10፡11፤ 1ኛ ዮሐ. 1፡3-4።

ጥያቄ 4

የእግዚአብሔር ባሕርይ እንዴት ያለ ነው?

መልስ

እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ በነዋሪነቱ፥ በጥበቡ፥ በኃይሉ፥ በቅድስናው፥ በቅንነቱ፥ በበጎነቱ፥ በእውነቱ ወሰን የሌለው ዘላለማዊና የማይለውጥ ነው።

ዘፍ. 17፡1፤ ዘጸ. 3፡14፤ 34፡6-7፤ መዝ. 90፡2፤ 145፡3፤ ዮሐ. 4፡24፤ ሮሜ 11፡33፤ ያዕ. 1፡17፤ ራእ. 4፡8

ጥያቄ 5

ከአንዱ እግዚአብሔር በቀር ሌሎች ሕያዋንና እውነተኞች አማልክት አሉን?

መልስ

ከአንዱ እግዚአብሔር በቀር ሌሎች ሕያዋንና እውነተኞች አማልክት የሉም።

ዘዳ. 6፡4፤ ኤር. 10፡10፤ ዮሐ. 17፡3፤ 1ኛ ቆሮ. 8፡4

ጥያቄ 6

በመለኮት ስንት አካላት አሉ?

መልስ

በመለኮት ሦስት አካለት አሉ፤ እነሱም አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ናቸው። እነዚህም ሦስቱ አንድ አምላክ ናቸው። አንድ ሕላዌ አላቸው፤ በኃይልና በክብርም እኩል ናቸው።

ማቴ. 3፡16-17፤ 28፡19፤ ዮሐ. 1፡1+5+18፤ የሐዋ. 5፡3-4፤ 2ኛ ቆሮ. 13፡14፤ ዕብ. 1፡3

ጥያቄ 7

እግዚአብሔር ሁሉን ነገር የወሰነው እንዴት ነው?

መልስ

እግዚአብሔር ሁሉን ነገር የወሰነው በዘላለማዊ አሳቡ ነው። በዚህም አሳቡ እንደ ፈቃዱ ምክር ለራሱ ክብር የሚሆኑትን ነገሮች ሁሉ አስቀድሞ ወስኗል።

የሐዋ. 2፡23፤ ሮሜ 11፡36፤ ኤፌ. 1፡11

ጥያቄ 8

እግዚአብሔር የወሰናቸውን ነገሮች እንዴት ይፈጽማል?

መልስ

እግዚአብሔር የወሰናቸውን ነገሮች የሚፈጽመው በመፍጠር ሥራውና በመግቦተ እግዚአብሔር ሥራው ነው።

ኢሳ. 40፡26፤ ዳን. 4፡35፤ ራእ. 4፡11

ጥያቄ 9

የፍጥረት አፈጣጠር እንዴት ነው?

መልስ

የፍጥረት አፈጣጠር እግዚአብሔር በኃይሉ ቃል ከምንም ነገር ሁሉን እጅግ መልካም አድርጎ በስድስት ቀን የፈጸመው አሠራር ነው።

ዘፍጥ. 1፡1+31፤ መዝ. 33፡9፤ ዕብ. 11፡3

ጥያቄ 10
እግዚአብሔር ሰውን እንዴት አድርጎ ፈጠረ?
መልስ
እግዚአብሔር ሰውን ወንድና ሴት አድርጎ በእውነት፥ በጽድቅና በቅድስና እንደራሱ መልክ ፈጠራቸው፤ በፍጥረቱም ላይ ገዥነትን ሰጣቸው።
ዘፍ. 1፡27-28፤ ኤፌ. 4፡24፤ ቆላ. 3፡10

ጥያቄ 11
እግዚአብሔር የመጋቢነት ሥራውን እንዴት ያካሂዳል?
መልስ
እግዚአብሔር የመጋቢነት ሥራውን የሚያካሂደው በሙሉ ቅድስናው፥ በሙሉ ጥበቡና በሙሉ ኃይሉ፤ ፍጥረቱንና ተግባራቸውን በመንከባከብና በማስተዳደር ነው።
ነህ. 9፡6፤ መዝ. 104፡24፤ 145፡17፤ ማቴ. 10፡30፤ ዕብ. 1፡3

ጥያቄ 12
ሰው በተፈጠረበት ሁኔታ እግዚአብሔር ምን አዘጋጀለት?
መልስ
እግዚአብሔር ሰውን ከፈጠረ በኋላ መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና በማለት፤ ሰው ፈጽሞ ቢታዘዝ የሚጸናለትን የሕይወት ተስፋ ሰጠው።
ዘፍ. 2፡17፤ ገላ. 3፡12

ጥያቄ 13
የመጀመሪያ ወላጆቻችን በተፈጠሩበት ሁኔታ ጸንተው ኖረዋልን?
መልስ
የመጀመሪያ ወላጆቻችን በግል የነፃ ምርጫቸው በመወሰን በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን ስለ ሠሩ ከተፈጠሩበት ሁኔታ ወደቁ።
ዘፍ. 3፡6፤ ሮሜ 5፡12

ጥያቄ 14
ኃጢአት ምንድነው?
መልስ
ኃጢአት የእግዚአብሔርን ሕግ አለመታዘዝ ወይም የእግዚአብሔርን ሕግ መተላለፍ ነው።
ሮሜ 4፡15፤ 1ኛ ዮሐ. 3፡4፤ ያእቆብ 2፡10፤ 4፡17

ጥያቄ 15
የመጀመሪያ ወላጆቻችን ከተፈጠሩበት ሁኔታ የወደቁበት ኃጢአት ምንድነው?
መልስ
የመጀመሪያ ወላጆቻችን ከተፈጠሩበት ሁኔታ የወደቁበት ኃጢአት ከተከለከለው ዛፍ መብላታቸው ነው።
ዘፍ 3፡12-13

ጥያቄ 16
አዳም ከሠራው ከመጀመሪያው መተላለፍ የተነሣ ሰው ሁሉ ወድቆአልን?
መልስ
ከአዳም ጋር ያደረገው ቃል ኪዳን ለሚቀጥለው ትውልድም ጭምር እንጂ ለእርሱ በቻ ተወስኖ የቀረ አልነበረም። ስለሆነም ሰው ሁሉ የአዳም ዘር ሆኖ እርሱ በሠራው በመጀምሪያው መተላለፍ በእርሱ ኃጢአትን ሠርቶ ከእርሱ ጋር ወደቀ።
ዘፍ. 1፡28፤ የሐዋ. 17፡26፤ ሮሜ 5፡12፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡21-22

ጥያቄ 17
ከዚህ ውድቀት የተነሣ ሰው እንዴት ያለ ሁኔታ ደረሰበት?
መልስ
ከዚህ ውድቀት የተነሣ ሰው በኃጢአትና በመከራ ወደቀ።
ሮሜ 5፡12-13

ጥያቄ 18
ሰው የወደቀበት ሁኔታ በኃጢአት የተሞላ ያደረጉ ምንና ምን ናቸው?
መልስ
ሰው የወደቀበትን ሁኔታ በኃጢአት የተሞላ እንዲሆን ያደረጉ በመጀመሪያ አዳም ከሠራው ኃጢአት የተወረሰ በደል፥ ቀድሞ የነበረውን ጽድቅ ማጣትና የሙሉ ባሕርይ መበላሸት ናቸው። ከዚህም ከተወረሰው የኃጢአት ባሕርይ የመተላለፍ ተግባሮች ሁሉ ይመነጫሉ።
ማቴ. 15፡19፤ ሮሜ 5፡18-19፤ 8፡7-8፤ ኤፌ. 2፡1

ጥያቄ 19
ሰው የወደቀበት መከራ ምንድነው?

መልስ
ከውድቀቱ የተነሣ ሰው ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን ኅብረት አጥቶ ከቁጣውና ከእርግማኑ በታች ሆነ፤ ስለዚህም ለዚህ ዓለም ችግር፥ ለሞት፥ ለዘላለም የገሃነም ሥቃይ ተገዥ ሆነ።
ዘፍ. 3፡8+24፤ ማር. 9፡47-48፤ ሮሜ 7፡23፤ ኤፌ. 2፡3

ጥያቄ 20
ሰው ሁሉ በኃጢአትና በችግር ውኔታ እንዲጠፋ እግዚአብሔር ትቶታልን?
መልስ
ከዘላለም ጀምሮ እግዚአብሔር በበጎ ፈቃዱ ብቻ የዘላለምን ሕይወት እንዲወርሱ ብዙዎችን መርጦ በአንድ አዳኝ ከኃጢአትና ከመከራ ነፃ አውጥቶ ወደ ደኅንነት ሊያመጣቸው የሕይወት ቃል ኪዳን ገብቶላቸዋል።
ዮሐ. 17፡6፤ ኤፌ. 1፡4፤ ቲቶ 1፡2-3፤ 3፡7

ጥያቄ 21
እግዚአብሔር የመረጣቸውን የሚያድን ማነው?
መልስ
እግዚአብሔር የመረጣቸውን የሚያድን ጌታ ኢየሱስ ብቻ ነው። እሱም ዘላለማዊ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ሳለ ፍጹም ሰው ሆነ። በባሕርዩ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው ሆኖ አምላክነቱና ሰውነቱ ሳይደባለቁ በአንድ አካል ኖረ፤ ለዘላለምም እንዲሁ ሆኖ ይኖራል።
ዮሐ. 1፡14፤ ሮሜ 9፡5፤ ቆላ. 2፡9፤ 1ኛ ጢሞ. 2፡5፤ ዕብ. 13፡8

ጥያቄ 22
ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ሳለ ሰው የሆነው እንዴት ነው?
መልስ
ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በድንግል ማርያም ማኅፀን ተፀንሶ ያለ ኃጢአት ከእሷ ተወለደ፤ እውነተኛ ሥጋን ወሰደ፤ አእምሮ ያላትንም ነፍስ በመያዝ ፍጹም ሰው ሆነ።
ማቴ. 26፡38፤ ሉቃ. 1፡31+35፤ 2፡52፤ ዕብ. 2፡14፤ 4፡15

ጥያቄ 23
ክርስቶስ አዳኛችን ስለሆነ የሚፈጽማቸው ሥራዎች ምን ምን ናቸው?

መልስ

ክርስቶስ አዳኛችን ስለሆነ በምድር በውርደት በነበረበትም ጊዜ ሆነ አሁን በክብሩ ሳለ የነቢይነትን፥ የከህነትንና የንጉሥነትን ሥራዎች ይፈጽማል።

መዝ. 2፡6፤ ዮሐ. 1፡49፤ የሐዋ. 3፡22፤ ዕብ. 3፡5-6

ጥያቄ 24

ክርስቶስ የነቢይነትን ሥራ እንዴት ይፈጽማል?

መልስ

ክርስቶስ በቃሉና በመንፈሱ ለደኅንነታችን የሆነውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለኛ በመግለጥ የነቢይነትን ሥራ ይፈጽማል።

ዮሐ. 1፡18፤ 14፡26፤ 16፡13፤ ዕብ. 1፡1-12

ጥይቄ 25

ክርስቶስ የከህነትን ሥራ እንዴት ይፈጽማል?

መልስ

ክርስቶስ የአምላካዊ ጽድቅን ሊያረካና ከእግዚአብሔር ጋር ሊያስታርቀን አንድ ጊዜ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ በማቅረቡ ዘወትርም ስለ እኛ በማማለድ የከህነት ሥራውን ይፈጽማል።

ሮሜ 3፡26፤ 8፡34፤ 10፡4፤ ዕብ. 2፡17፤ 7፡24-25፤ 9፡28

ጥያቄ 26

ክርስቶስ የንጉሥነትን ሥራውን እንዴት ይፈጽማል?

መልስ

ክርስቶስ እኛን የእርሱ ታዛዦች በማድረግ እያስተዳደረን እየተከላከለልንም የእርሱንና የእኛን ጠላቶች ሁሉ በመከላከልና በማሸነፍ የንጉሥነት ሥራውን ይፈጽማል።

መዝ. 110፡3፤ የሐዋ. 2፡36፤ 18፡9-10

ጥያቄ 27

ክርስቶስ ራሱን ያዋረደው በምን በምን ነገር ነው?

መልስ

ክርስቶስ ራሱን ያዋረደው በመወለዱ፥ ዝቅተኝነትን በመቀበሉ፥ ከሕግ በታች በመሆኑ፥ የዚህን ዓለም ችግር በመቀበሉ፥ የእግዚአብሔርንም ቁጣና የተረገመውን የመስቀል ሞት በመቀበሉ፥ በመቀበሩና ለተወሰነ ጊዜ ከሞት ሥልጣን በታች በመሆኑ ነው።

ኢሳ. 53፡3፤ ማቴ. 27፡46፤ ሉቃ. 2፡7፤ 22፡44፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡3-4፤ ገላ. 3፡13፤ 4፡4፤ ፊል. 2፡7-8፤ ዕብ. 12፡2

ጥያቄ 28
ክርስቶስ ከፍ ከፍ ያለው በምንና በምን ነገር ነው?
መልስ
ክርስቶስ ከፍ ከፍ ያለው በሦስተኛው ቀን ከሙታን በመነሣቱ፥ ወደ ሰማይ በማረጉ፥ በእግዚአብሔር አብ ቀኝ በመቀመጡና በመጨረሻው ቀን በዓለም ላይ ሊፈርድ በመምጣቱ ነው።
የሐዋ. 1፡11፤ 16፡31፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡4፤ ኤፌ. 1፡20

ጥያቄ 29
ክርስቶስ በዋጀው ቤዛነት ተካፋዮች የሆንነው እንዴት ነው?
መልስ
ክርስቶስ በዋጀው ቤዛነት ተካፋዮች የሆንነው ቤዛነቱን በውስጣችን አትሞ በሚሠራው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ነው።
ዮሐ። 1፡12፤ 3፡3-6፤ ቲቶ 3፡5-6

ጥያቄ 30
መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስ የዋጀውን ቤዛነት በውስጣችን አትሞ የሚሠራው እንዴት ነው?
መልስ
መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስ የዋጀውን ቤዛነት በውስጣችን አትሞ የሚሠራው እምነትን በውስጣችን በመፍጠር፥ በዚህም እምነት ወደ ደኅንነት በሚመራው ጥሪአችን ከክርስቶስ ጋር አንድ በማድረግ ነው።
ኤፌ. 1፡13-14፤ 4፡15-16፤ ገላ. 2፡20

ጥያቄ 31
ወደ ደኅንነት የሚመራው ጥሪ ምንድነው?
መልስ
ወደ ደኅንነት የሚመራው ጥሪ የእግዚአብሔር መንፈስ ሥራ ነው። እሱም በዚህ ሥራ ኃጢአታችንንና መከራችንን እያስገነዘበን፣ ክርስቶስንም እንድናውቅ አእምሮአችንን እያበራ፣ ፈቃዳችንን አድሶ፥ ወንጌልን ያለ ዋጋ ያቀረበልንን ኢየሱስ ክርስቶስን እንድንቀበል ያደርገናል፥ ያስችለናልም።
ሕዝ. 36፡26-27፤ ዮሐ. 6፡44-45፤ የሐዋ. 2፡37፤ 26፡18፤ ፊል. 2፡13፤ 2ኛ ተሰ. 2፡13

ጥያቄ 32

ወደ ደኅንነት በሚመራው ጥሪ የተጠሩት በዚህች ሕይወት ምንና ምን በረከቶችን ያገኛሉ?

መልስ

ወደ ደኅንነት በሚመራው ጥሪ የተጠሩት በዚህች ሕይወት መጽደቅን፥ የእግዚአብሔር ልጆች መሆንንና መቀደስን፥ ከእነዚህም ጋር የተያያዙትን ወይም ከእነዚህ የሚፈልቁትን ብዙ በረከቶች ያገኛሉ።

ሮሜ 8፡30፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡30፤ ኤፌ. 1፡5

ጥያቄ 33

ማጽደቅ ምንድነው?

መልስ

ማጽደቅ እግዚአብሔር እንዲያው በጸጋው የሚያደርገው ተግባር ነው። በዚህም ተግባር በእምነት ብቻ ልነቀበለው የሚቻል የክርስቶስ ጽድቅ ስለተቆጠረልን፤ እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ሁሉ ይቅር ይለናል፤ በፊቱም እንደ ጻድቃን ቆጥሮ ይቀበለናል።

ሮሜ 3፡24፤ 4፡6፤ 5፡18፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡21፤ ገላ. 2፡16፤ ኤፌ. 1፡7፤ ፊል. 3፡9

ጥያቄ 34

የእግዚአብሔር ልጆች መሆን ማለት ምንድነው?

መልስ

የእግዚአብሔር ልጆች መሆን ማለት እግዚአብሔር እንዲያው በጸጋው የሚያደርገው ተግባር ነው። በዚህም ተግባር እንደ ልጆቹ ቆጥሮ ይቀበለናል፤ ለልጆቹም የተገባውን ሁሉ መብታችን አድርጎ ይሰጠናል።

ዮሐ. 1፡12፤ ሮሜ 8፡17፤ 1ኛ ዮሐ. 3፡1

ጥያቄ 35

ቅድስና ምንድነው?

መልስ

ቅድስና እግዚአብሔር እንዲያው በጸጋው የሚያደርገው ሥራ ነው። በዚህም ሥራ እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ ሕይወታችንን እያደሰና በየጊዜውም ከኃጢአት እየለየን ለጽድቅ መኖርን ያስችለናል።

ሮሜ 6፡6፥11፤ 8፡4፤ ኤፌ. 4፡24፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡2

ጥያቄ 36
በዚህች ሕይወት ከመጽደቅ፥ የእግዚአብሔር ልጆች ከመሆንና ከመቀደስ ጋር የተያያዙት ወይም ከእነዚህ የሚፈልቁት በረከቶች ምንና ምን ናቸው?

መልስ
በዚህች ሕይወት ከመጽደቅ፥ የእግዚአብሔር ልጆች ከመሆንና ከመቀደስ ጋር የተያያዙት ወይም ከእነዚህ የሚፈልቁት በረከቶች የእግዚአብሔርን ፍቅር የሚያረጋግጥ እውቀት፥ የሕሊና ሰላም፥ በመንፈስ ቅዱስ የሆነ ደስታ፥ በጸጋ ማደግ፥ እንዲሁም በዚህ ጸጋ እስከ መጨረሻው መጽናት ናቸው።
ዮሐ. 1፡16፤ ሮሜ 5፡1–2፡5፤ 14፡17፤ ፊል. 1፡6፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡5

ጥያቄ 37
ምእመናን ሲሞቱ ከክርስቶስ የሚያገኟቸው በረከቶች ምንና ምን ናቸው?

መልስ
ምእመናን ሲሞቱ ነፍሳቸው ፍጹማን ይሆናሉ፤ ወዲያውም ወደ ክብር ያልፋሉ። ሥጋቸው ከክርስቶስ ጋር ያለው አንድነት ሳይቋረጥ እስከ ትንሣኤ ድረስ በመቃብር ውስጥ ያርፋል።
ሉቃ. 23፡43፤ ዮሐ. 5፡28፤ የሐዋ. 7፡55፥59፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡8፤ ፊል. 1፡23፤ 1ኛ ተሰ. 4፡14፤ ዕብ. 12፡23፤ ራእ. 14፡13፤ 19፡18

ጥያቄ 38
በትንሣኤ ቀን ምእመናን ከክርስቶስ የሚያገኙዋቸው በረከቶች ምንና ምን ናቸው?

መልስ
በትንሣኤ ቀን ምእመናን በክብር በመነሣታቸው በፍርድ ቀን ከፍርድ ነፃ ወጥተው ጻድቃን መሆናቸው በግልጥ ይታወቃል፤ በእግዚአብሔርም እየተደሰቱ ለዘላለም ፍጹማንና ብፁዓን ይሆናሉ።
መዝ. 16፡11፤ ማቴ. 10፡32፤ 25፡31፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡43

ጥያቄ 39
እግዚአብሔር ከሰው የሚፈልገው አገልግሎት ምንድነው?

መልስ
እግዚአብሔር ከሰው የሚፈልገው አገልጎሎት ለተገለጠው ፈቃዱ መታዘዝን ነው።
ዘዳ. 29፡29፤ 1ኛ ሳሙ. 15፡22፤ ሚክ. 6፡8፤ ሉቃ. 10፡28

ጥያቄ 40

ሰው እንዲታዘዘው እግዚአብሔር በመጀመሪያ የገለጠው ሥርዓት ምንድነው?

መልስ

ሰው እንዲታዘዘው እግዚአብሔር በመጀመሪያ የገለጠው የሥነ ምግባር ሕግ ነው።

ሮሜ 2፡14-15፤ 10፡5

ጥያቄ 41

የሥነ ምግባር ሕግ ባጭሩ የሚገኘው የት ነው?

መልስ

የሥነ ምግባር ሕግ ባጭሩ የሚገኘው በአሥርቱ ትእዛዛት ነው።

ዘዳ. 10፡4፤ ማቴ. 19፡17

ጥያቄ 42

የአሥርቱ ትእዛዛት አጠቃላይ አሳብ ምንድነው?

መልስ

የአሥርቱ ትእዛዛት አጠቃላይ አሳብ ጌታ አምላካችንን በፍጹም ልባችን፥ በፍጹም ነፍሳችን፥ በፍጹም አሳባችን፥ በፍጹምም ኃይላችን እንድንወደውና ባልንጀራችንን እንደራሳችን አድርገን እንድናፈቅር ነው።

ማቴ. 22፡37-40

ጥያቄ 43

የአሥርቱ ትእዛዛት መቅድም ምን የሚል ነው?

መልስ

የአሥርቱ ትእዛዛት መቅድም «ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ያወጣሁህ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ» የሚል ነው።

ዘጸ. 20፡2

ጥያቄ 44

የአሥርቱ ትእዛዛት መቅድም ምን ያስተምረናል?

መልስ

የአሥርቱ ትእዛዛት መቅድም እግዚአብሔር ጌታና አምላካችን አዳኛችንም ስለሆነ ትእዛዛቱን ሁሉ መጠበቅ እንደሚገባን ያስተምረናል።

ዘዳ. 11፡1፥ 1ኛ ጴጥ. 1፡17፥19

ጥያቄ 45

አንደኛው ትእዛዝ ምን ይላል?

መልስ
አንደኛው ትእዛዝ «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ» የሚለው ነው።

ጥያቄ 46
በአንደኛው ትእዛዝ እግዚአብሔር የሚፈልገው ምንድነው?
መልስ
በአንደኛው ትእዛዝ እግዚአብሔር እውነተኛ አምላክ ብቻና አምላካችን መሆኑን እንድናውቅና እንድንመሰክር እሱንም በሚገባ እያመለክን እንድናከብረው ይፈልጋል።
ዘዳ. 26፡17፤ 1ኛ ዜና 28፡9፤ መዝ. 29፡2፤ 95፡6-7፤ ማቴ. 4፡10

ጥያቄ 47
በአንደኛው ትእዛዝ የተከለከለው ምንድነው?
መልስ
በአንደኛው ትእዛዝ አምላካችን የሆነውን እውነተኛውን አምላክ ከመካድ፥ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ሳናመልከውና ሳናከብረው ከመቅረት፥ ለእርሱም ብቻ የሚገባውን አምልኮና ክብር ለሌላ ከመስጠት ይከልከላል።
መዝ. 14፡1፤ 21፡11፤ ሮሜ 1፡20-21፥25

ጥያቄ 48
በአንደኛው ትእዛዝ በዕብራይስጡ «በፊቴ» የሚለው ምን ያስተምረናል?
መልስ
በአንደኛው ትእዛዝ «በፊቴ» የሚለው ሌላ አምላክ ብናመልክ ሁሉን የሚያይ እግዚአብሔር ተመልክቶ እጅግ እንደሚቆጣ ያስተምረናል።
ዘዳ. 30፡17-18፤ 1ኛ ዜና 28፡9፤ መዝ. 44፡20-21፤ 139፡1-3

ጥያቄ 49
ሁለተኛው ትእዛዝ ምን ይላል?
መልስ
ሁለተኛው ትእዛዝ «በላይ በሰማይ ካለው በታችም በምድር ካለው በምድርም በታች በውሃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ፥ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ። አትስገድላቸው፤ አታምልካቸውም። በሚጠሉኝ እስከ ሦስተኛና እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ፤ ለሚወዱኝ ትእዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ ሺህ

ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና» የሚለው ነው።
ዘጽ. 20፡4-6

ጥያቄ 50
በሁለተኛው ትእዛዝ የሚፈልገው ምንድነው?
መልስ
በሁለተኛው ትእዛዝ እግዚአብሔር በቃሉ ያዘዘው አምልኮና ሥርዓት ሁሉ ንጹሕና ፍጹም ሆኖ እየተከበረ እንዲጠበቅ ይፈልጋል።
ዘዳ. 12፡32፤ 32፡46፤ ማቴ. 28፡20

ጥያቄ 51
በሁለተኛው ትእዛዝ የተከለከለው ምንድነው?
መልስ
በሁለተኛው ትእዛዝ እግዚአብሔር በምስል ወይም በቃሉ ካልታዘዘው በማንኛውም መንገድ እንዳይመለክ ይከለክላል።
ዘዳ. 4፡15-19፤ 12፡3፤ ሮሜ 1፡22-23፤ ቆላ. 2፡18

ጥያቄ 52
በሁለተኛው ትእዛዝ የተሰጡ ምክንያቶች ምንድናቸው?
መልስ
እግዚአብሔር በእኛ ላይ ሙሉ ሥልጣን እንዳለው፥ እኛ የእርሱ ሀብት መሆናችንንና ስለ ራሱ አምልኮ ቅንዓት እንዳለው በሁለተኛው ትእዛዝ የተሰጡ ምክንያቶች ናቸው።
ዘጸ. 34፡14፤ መዝ. 45፡11፤ 100፡3፤ 1ኛ ቆሮ. 10፡22

ጥያቄ 53
ሦስተኛው ትእዛዝ ምን ይላል?
መልስ
ሦስተኛው ትእዛዝ «የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፤ እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነጻውምና» የሚለው ነው።
ዘጸ. 20፡7

ጥያቄ 54
በሦስተኛው ትእዛዝ እግዚአብሔር የሚፈልገው ምንድነው?

መልስ
በሦስተኛው ትእዛዝ የእግዚአብሔር ስሞች፥ ማዕረጎቹ፥ ግብሮቹ፥ ሥርዓቶቹ፥ ቃሉና ሥራዎቹ በቅድስና እንዲከበሩ ይፈልጋል።
ዘዳ. 28፡58፤ ኢዮ. 36፡24፤ መዝ. 29፡2፤ 104፡24፤ 138፡2፤ መክ. 5፡1፤ ማቴ. 6፡9፤ ራእ. 15፡3-4

ጥያቄ 55
በሦስተኛው ትእዛዝ የተከለከው ምንድነው?
መልስ
በሦስተኛው ትእዛዝ እግዚአብሔር ራሱን የሚገልጥበት ማንኛውም ነገር በፍጹም ርኩስ ሆኖ እንዳይቆጠር ወይም እንዳይሰደብ ይከለክላል።
ዘሌ. 19፡12፤ ማቴ. 5፡34-35

ጥያቄ 56
ለሦስተኛው ትእዛዝ የተሰጠ ምክንያት ምንድነው?
መልስ
ለሦስተኛው ትእዛዝ የተሰጠው ምክንያት ይህን ትእዛዝ የሚያፈርሱ ምንም እንኳ ሰው ከሚሰጠው ቅጣት ቢያመልጡም፤ እግዚአብሔር ከሚሰጠው ቅን ፍርድ ለማምለጥ እንደማይችሉ ነው።
ዘዳ. 28፡58-59

ጥያቄ 57
አራተኛው ትእዛዝ ምን ይላል?
መልስ
አራተኛው ትእዛዝ «የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ። ስድስት ቀን ሥራ ተግባርህንም ሁሉ አድርግ፤ ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር ለአምላክህ ሰንበት ነው። አንተ፥ ወንድ ልጅህም፥ ሴትህም፥ ገረድህም፥ ከብትህም፥ በደጆችህ ውስጥ ያለ እንግዳ፤ በእሱ ምንም ሥራ አትሥሩ። እግዚአብሔር በስድስት ቀን ሰማይንና ምድርን ባሕርንም ያለባቸውንም ሁሉ ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን አርፎአልና፤ ስለዚህ እግዚአብሔር የሰንበትን ቀን ባርኮታል፥ ቀድሶታልም» የሚለው ነው።
ዘጸ. 20፡8-11

ጥያቄ 58
በአራተኛው ትእዛዝ የሚፈልገው ምንድነው?

መልስ

እግዚአብሔር በአራተኛው ትእዛዝ የሚፈልገው በቃሉ የወሰናቸው ጊዜያት፣ በተለይም ከሰባቱ ቀናት አንዱ ለራሱ ቅዱስ ሰንበት ሆኖ፣ በሙሉ ለእርሱ በቅድስና እንዲጠበቅ ይፈልጋል።

ዘሌ. 19፡30፤ ዘዳ. 5፡12

ጥያቄ 59

በየሳምንቱ ሰንበት እንዲሆን እግዚአብሔር ከሰባቱ ቀናት የወሰነው የትኛውን ነው?

መልስ

እግዚአብሔር ዓለምን ከፈጠረ ጊዜ ጀምሮ እስከ ክርስቶስ ትንሣኤ ድረስ የሳምንቱ ሰባተኛ ቀን ሰንበት እንዲሆን፣ ከክርስቶስ ትንሣኤ ወዲህ የሳምንቱ መጀመሪያው ቀን የክርስቲያን ሰንበት ሆኖ እስከ ዓለም መጨረሻ ድረስ እንዲሆን ወስኗል።

ዘፍ. 2፡3፤ ዘጸ. 16፡23፤ የሐዋ. 20፡7፤ 1ኛ ቆሮ. 16፡1–2፤ ራእ. 1፡10

ጥያቄ 60

የሰንበት ቀን እንዴት ይቀደሳል?

መልስ

የሰንበት ቀን በሌሎች ቀናት ከተፈቀዱ ዓለማዊ ሥራና መዝናኛ በመለየት፥ በጠቅላላም በዚያ ቀን ቅዱስ ዕረፍት በማድረግ፥ ከአስፈላጊና ከርኅራኄ ሥራ በስተቀር በግልና በማኅበር ጸሎትና እግዚአብሔርን በማምለክ ሙሉው ቀን ይቀደሳል።

ዘሌዋ. 23፡3፤ ኤሳይ. 58፡13–14፤ ማቴ. 12፡11–12፤ ማር. 2፡27

ጥያቄ 61

በአራተኛው ትእዛዝ የተከለከለው ምንድነው?

መልስ

አራተኛው ትእዛዝ የሚፈለገውን መንፈሳዊ ሥርዓት አለመፈጸምን፥ አለመጠንቀቅን፥ በመቦዘን ኃጢአት ማድረግን፥ ስለዓለማዊ ሥራዎቻችን ወይም መዝናኛዎቻችን ያለ መጠን በማሰብና በመነጋገር ወይም በመሥራት ቀኑ ርኩስ እንዳይሆን ይከለክላል።

ሕዝ. 23፡38፤ ኤር. 17፡21፤ ሉቃ. 23፡56

ጥያቄ 62

ለአራተኛው ትእዛዝ የተሰጡት ምክንያቶች ምንድናቸው?

መልስ

ለአራተኛው ትእዛዝ የተሰጡት ምክንያቶች እግዚአብሔር ሥራዎቻችንን እንድንሠራባቸው ከሳምንት ስድስት ቀናትን መፍቀዱ፥ ሰባተኛውን ቀን ለራሱ መለየቱ፥ ለእኛ ምሳሌ ይሆን ዘንድ ራሱ በሰንበት ቀን ማረፉና ቀኑን መባረኩ ናቸው።

ዘፍ. 2፡3፤ ዘጸ. 31፡15–17፤ ዘሌ. 23፡3

ጥያቄ 63

አምስተኛው ትእዛዝ ምንድነው?

መልስ

አምስተኛው ትእዛዝ «አባትህንና እናትህን አክብር፤ እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር እድሜህ እንዲረዝም» የሚለው ነው።

ዘጸ. 20፡12

ጥያቄ 64

በአምስተኛው ትእዛዝ እግዚአብሔር የሚፈልገው ምንድነው?

መልስ

አምስተኛው ትእዛዝ ለማንኛውም ሰው እንደ ማዕረጉ፤ እንደ ከፍታውና እንደዝቅታው ወይም እንደ እኩልነቱ፤ በተመደበለት ስፍራና ግንኙነት የሚገባውን ክብር እንዲጠብቅና ተግባርን እንዲያደርግ ይፈልጋል።

ዘሌ. 19፡32፤ ሮሜ 12፡1፤ 13፡1፤ ኤፌ. 6፡1፥5፥9፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡17

ጥያቄ 65

በአምስተኛው ትእዛዝ የተከለከለው ምንድነው?

መልስ

አምስተኛው ትእዛዝ ለማንኛውም ሰው እንደ ማዕረጉ በተመደበለት ስፍራና ግንኙነት የሚገባውን ክብርና ተግባር እንዳይነፈገው ወይም አግባብ የሌለው ተቃውሞ እንዳይደርስበት ይከለክላል።

ሮሜ 12፡7–8

ጥያቄ 66

ለአምስተኛው ትእዛዝ የተሰጠው ምክንያት ምንድነው?

መልስ

ለአምስተኛው ትእዛዝ የተሰጠው ምክንያት ይህን ትእዛዝ ለሚጠብቁ ሁሉ የረዥም ዕድሜና የብልጽግና ተስፋ ቃል ናቸው። ይህ የተስፋ ቃል የተሰጠበት መሠረት ለእግዚአብሔር ክብርና ለራሳቸው ጥቅም እንዲያገለግል ነው።

ኤፌ. 6፡2–3

ጥያቄ 67

ስድስተኛው ትእዛዝ የትኛው ነው?

መልስ

ስድስተኛው ትእዛዝ «አትግደል» የሚለው ነው።

ዘጸ. 20፡13

ጥያቄ 68

በሰድሰተኛው ትእዛዝ የተከለከለው ምንድነው?

መልስ

ስድስተኛው ትእዛዝ ሕግ በሚፈቅደው መንገድ ሁሉ የራሳችንና የሌሎችን ሕይወት እንድንጠብቅ ይፈለጋል።

መዝ. 82፡3–4፤ ኤፌ. 5፡29–30

ጥያቄ 69

በስድሰተኛው ትእዛዝ የተከለከለው ምንድነው?

መልስ

በስድሰተኛው ትእዛዝ የራሳችንን ሆነ የባልንጀራችንን ሕይወት፣ ቅንነት በሌለበት መንገድ እንዳናጠፋ ወይም እንዳንጎዳ ይከለክላል።

ዘፍ. 9፡6፤ ዘዳ. 24፡6፤ ምሳ. 24፡11–12፤ የሐዋ. 16፡28፤ 1ኛ ዮሐ. 3፡15

ጥያቄ 70

ሰባተኛው ትእዛዝ የትኛው ነው?

መልስ

ሰባተኛው ትእዛዝ «አታመንዝር» የሚለው ነው።

ዘጸ. 20፡14

ጥያቄ 71

በሰባተኛው ትእዛዝ እግዚአብሔር የሚፈልገው ምንድነው?

መልስ

በሰባተኛው ትእዛዝ የራሳችንንና የባልንጀራችንን ንጽሕና በሐሳብ፣ በንግግር፣ በአካሄድ እንድንጠብቅ ይፈልጋል።

ኤፌ. 4፡29፤ 5፡11–12፤ 1ኛ ተሰ. 4፡2፤ 2ኛ ጢሞ. 2፡22፤ 1ኛ ጴጥ. 3፡2

ጥያቄ 72

በሰባተኛው ትእዛዝ የተከለከለው ምንድነው?

መልስ
ሰባተኛው ትእዛዝ ርኩስ የሆነ ሐሳብን፥ ቃልንና ተግባርን ሁሉ ይከለክላል።
ማቴ. 5፡28፤ ኤፌ. 5፡3፥4

ጥያቄ 73
ስምንተኛው ትእዛዝ የትኛው ነው?
መልስ
ስምንተኛው ትእዛዝ «አትስረቅ» የሚለው ነው።
ዘጸ. 20፡15

ጥያቄ 74
በስምንተኛው ትእዛዝ እግዚአብሔር የሚፈለገው ምንድነው?
መልስ
ስምንተኛው ትእዛዝ ሕግ በሚፈቅደው መንገድ ሁሉ የራሳችንም ሆነ የሌሎች ሀብትና ኑሮ እንዲሻሻልና እንዲለማ ይፈልጋል።
ዘሌ. 25፡35፤ ዘዳ. 15፡1 ምሳ. 27፡23

ጥያቄ 75
በሰምንተኛው ትእዛዝ የተከለከለው ምንድነው?
መልስ
ስምንተኛው ትእዛዝ የራሳችን ሆነ የባልንጀራችን ሀብትና ኑሮ ቅንነት በሌለበት መንገድ እንዳይበላሽ ወይም እንዲሰናከል የሚያደርግ ነገር እንዳይሠራ ይከለክላል።
ምሳ. 28፡19፤ ኤፌ. 4፡28፤ 1ኛ ጢሞ. 5፡8፤ ያዕ. 5፡4

ጥያቄ 76
ዘጠነኛው ትእዛዝ የትኛው ነው?
መልስ
ዘጠነኛው ትእዛዝ «በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር» የሚለው ነው።
ዘጸ. 20፡16

ጥያቄ 77
ዘጠነኛው ትእዛዝ እግዚአብሔር የሚፈለገው ምንድነው?
መልስ
ዘጠነኛው ትእዛዝ በተለይ በምንመሰክረበት ጊዜ በሰው መካከል እውነት እንዲነገር፤ እንዲሁም የራሳችንና የባልንጀራችን መልካም ስም እንዲጠበቅና ከፍ ከፍ እንዲል ይፈልጋል።

ምሳ. 14፡5+25፤ የሐዋ. 25፡10፤ ኤፌ. 4፡25፤ 1ኛ ጴጥ. 3፡16፤ 3ኛ ዮሐ. 12

ጥያቄ 78

በዘጠነኛው ትእዛዝ የተከለከለው ምንድነው?

መልስ

ዘጠነኛው ትእዛዝ እውነትን የሚቃወም ወይም የራሳችንንና የባልንጀራችንን መልካም ስም የሚነዳ ነገር ሁሉ እንዳይደረግ ይከለክላል።

ዘሌ. 19፡16፤ መዝ. 12፡3፤ 15፡3፤ 2ኛ ቆሮ. 8፡20-21፤ ቆላ. 3፡9

ጥያቄ 79

አሥረኛው ትእዛዝ የትኛው ነው?

መልስ

አሥረኛው ትእዛዝ «የባልንጀራህን ቤት አትመኝ፥ የባልንጀራህን ሚስት፥ ሎሌውንም ገረዱንም በሬውንም አህያውንም ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ ማናቸውንም አትመኝ» የሚለው ነው።

ዘጸ. 20፡17

ጥያቄ 80

በአሥረኛው ትእዛዝ የሚፈለገው ምንድነው?

መልስ

አሥረኛው ትእዛዝ ራሳችን የምንኖርበት ኑሮ ይበቃናል እንድንል፤ እንዲሁም ባልንጀራችንና የእርሱ የሆነው ነገር ሁሉ ቅንነትና ልግስና በሞላበት መንፈስ እንዲታይ ይፈልጋል።

ዘሌ. 19፡18፤ ኢዮ. 31፡29፤ 1ኛ ቆሮ. 13፡4-6፤ 1ኛ ጢሞ. 6፡6፤ ዕብ. 13፡5

ጥያቄ 81

በአሥረኛው ትእዛዝ የተከለከለው ምንድነው?

መልስ

አሥረኛው ትእዛዝ ራሳችን የምንኖርበት ኑሮ አይበቃንም እንዳንል፥ የባልንጀራችንን መልካም ዕድል እንዳንመኝና እንዳናዝን እንዲሁም የባልንጀራችን በሆነው በማናቸውም ነገር ቀንተን የማይገባ መሻትና ምኞት እንዳያድርብን ይከለክላል።

1ኛ ቆሮ. 10፡10፤ ገላ. 5፡26፤ ቆላ. 3፡5

ጥያቄ 82
የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ፈጽሞ ለመጠበቅ የሚችል ሰው አለን?
መልስ
ከአዳም ውድቀት ወዲህ ከክርስቶስ በቀር በዚች ሕይወት የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ፈጽሞ ለመጠበቅ የሚችል ሰው የለም። እያንዳንዱ ሰው በሐሳቡ፥ በቃሉና በሥራው በየዕለቱ ሊተላለፋቸው ይገኛል።
1ኛ ነገ. 8፡46፤ ሮሜ 3፡9-10፤ 1ኛ ዮሐ. 1፡8-2፡6፤ ያዕ. 3፡2

ጥያቄ 83
ሕግን መተላለፍ ሁሉ በአስጸያፊነቱ እኩል ነውን?
መልስ
አንዳንድ ኃጢአቶች ከራሳቸው መጥፎነትና ከመደጋገም ከመፈጸማቸው የተነሣ፥ ከሌሎች ኃጢአቶች ይልቅ በእግዚአብሔር ፊት የከፉ ናቸው።
መዝ. 19፡13፤ ማቴ. 11፡24፤ ሉቃ. 12፡10፥47-48፤ ዮሐ. 19፡11፤ ዕብ. 10፡29

ጥያቄ 84
ኃጢአት ምን ይገባዋል?
መልስ
በዚህች ሕይወትም ሆነ በሚመጣው፤ ለማንኛውም ኃጢአት የእግዚአብሔር ቁጣና እርግማን ይገባዋል።
ማቴ. 25፡41፤ ገላትያ 3፡10፤ ኤፌ. 5፡6፤ ያዕ. 2፡10

ጥያቄ 85
እግዚአብሔር ለኃጢአታችን ከሚገባ ከእርሱ ቁጣና እርግማን እንድናመልጥ ከኛ ምን ይፈልጋል?
መልስ
እግዚአብሔር ለኃጢአታችን ከሚገባ ከእርሱ ቁጣና እርግማን እንድናመልጥ በኢየሱስ ክርስቶስ እንድናምን፥ ለሕይወት የሚሆን ንስሐ እንድንገባና ክርስቶስ ለእኛ ቤዛነቱን የሚያስተላልፍባቸውን ውጫዊ የጸጋ መሣሪያዎች በትጋት እንድንፈጽማቸው ይፈልጋል።
የሐዋ. 20፡21፤ 1ኛ ጢሞ። 4፡16፤ ዕብ. 2፡3፤ 2ኛ ጴጥ። 1፡10

ጥያቄ 86
በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ምንድነው?

መልስ

በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ማለት በወንጌል እንደ ቀረበልን ለድኅንነታች እርሱን መቀበልና በእርሱ ብቻ ማረፍ ነው። ይህም እምነት በክርስቶስ የምናርፍበትና ወደ ደኅንነት የሚመራን የጸጋ ስጦታ ነው።

ዮሐ. 1፡12፤ የሐዋ. 16፡31፤ ፊል. 3፡9፤ ዕብ. 10፡39፤ ራእ. 22፡17

ጥያቄ 87

ለሕይወት የሚሆን ንስሐ ምንድነው?

መልስ

ለሕይወት የሚሆን ንስሐ ኃጢአተኛ የኃጢአቱ ክፋት ተሰምቶት፥ በኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጠውን የእግዚአብሔርን ምሕረት የሚገነዘብበት፤ ኃጢአቱንም በመጥላት በልቡ የሚጸጸትበት፤ ሙሉ ፍላጎቱንና ጥረቱን ለአዲስ መታዘዝ አውሎ፣ ከኃጢአቱ ወደ እግዚአብሔር የሚመለስበትና ወደ ደኅንነት የሚመራበት ጸጋ ነው።

ኤር. 31፡18-19፤ ሉቃ. 1፡77-79፤ የሐዋ. 2፡37፤ ሮሜ 6፡18፤ 2ኛ ቆሮ. 7፡10

ጥያቄ 88

ክርስቶስ የቤዛነት በረከቶችን ለእኛ የሚያስተላልፍባቸው ውጫዊ መንገዶች ምንና ምን ናቸው?

መልስ

ክርስቶስ የቤዛነት በረከቶቹን ለእኛ የሚያስተላልፍባቸው ውጫዊና የተለመዱ መንገዶች ሥርዓቶቹ ናቸው። በተለይም ቃሉ፥ ምሥጢራቱና ጸሎት ናቸው። እነዚህ መንገዶች የተመረጡትን ወደ ደኅንነት ለማድረስ ከንውን ያላቸው መሣሪያዎች ናቸው።

ማቴ. 28፡18-20፤ የሐዋ. 2፡41-42

ጥያቄ 89

የእግዚአብሔር ቃል ደኅንነትን በማምጣት ከንውንን እንዴት ያገኛል?

መልስ

ኃጢአተኞች ኃጢአተኝነታቸውን ተረድተው ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ፥ በእምነት እንዲድኑ፥ በቅድስናና በመጽናናት እያደጉ እንዲሄዱ መንፈስ ቅዱስ ከሚነበበው በተለይም ከሚሰበከው ቃል ጋር እየተባበረ በአድማጮቹ ልብ ውስጥ በመሥራት ለቃሉ መከናወንን ይሰጣል።

ነህ. 8፡8፤ መዝ. 19፡7፤ የሐዋ. 20፡23፤ ሮሜ 15፡4፤ 2ኛ ጢሞ. 3፡15፤ ያዕ. 1፡21

ጥያቄ 90
የእግዚአብሔር ቃል ለደኅንነት የተከናወነ እንዲሆን የቃሉ አነባበብና የሰው አደማመጥ እንዴት ሊሆን ይገባል?
መልስ
የእግዚአብሔር ቃል ለደኅንነት የተከናወነ እንዲሆን አስቀድሞ በመዘጋጀት፥ በትጋት፥ በጸሎት በእምነት፥ በፍቅር በመቀበል፥ በልብ ውስጥ በማኖር፥ እንዲሁም በሕይወታችን በሥራ ላይ በማዋል ቃሉን ልናዳምጥ ይገባል።
ዘዳ. 7፡6-7፤ መዝ. 119፡11፤ ሮሜ 1፡16፤ 2ኛ ተሰ. 2፡10፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡1-2፤ ያዕ. 1፡25

ጥያቄ 91
ምሥጢራት ለደኅንነት የተከናወኑ የሚሆኑበት መንገድ እንዴት ነው?
መልስ
ምሥጢራት ለደኅንነት የተከናወኑ የሚሆኑበት መንገድ በራሳቸው ኃይል ስላላቸው ወይም ከአቅራቢዎቻቸው በጎነት የተነሣ ሳይሆን፤ ከርስቶስ ስለ ባረካቸውና አምነው በሚቀበሏቸው ውስጥ የእርሱ መንፈስ ስለሚሠራ ብቻ ነው።
የሐዋ. 8፡13+23፤ ሮሜ 2፡28-29፤ 1ኛ ቆሮ. 12፡13፤ 1ኛ ጴጥ. 3፡21

ጥያቄ 92
ምሥጢር ምንድነው?
መልስ
ምሥጢር ከርስቶስ ያዘዘው ቅዱስ ሥርዓት ነው። በዚህ ሥርዓት በሚታዩና በሚጨበጡ ምልክቶች በኩል ከርስቶስ ራሱና የአዲስ ኪዳን በረከቶች በምሳሌ ሆነው ለምእመናን ይታያሉ፥ ለምእመናን ይታተማሉ፥ ለምእመናን ይሰጣሉ።
ማቴ. 28፡19፤ 26፡26-28፤ ሮሜ 4፡11

ጥያቄ 93
አዲስ ኪዳን ምሥጢራት የትኞቹ ናቸው?
መልስ
የአዲስ ኪዳን ምሥጢራት ጥምቀትና የጌታ እራት ናቸው።
የሐዋ. 10፡47-48፤ 1ኛ ቆሮ. 11፡23-26

ጥያቄ 94

ጥምቀት ምንድነው?

መልስ

ጥምቀት በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም በውሃ በመታጠብ የሚፈጸም ምሥጢር ሲሆን፤ በክርስቶስ መግባታችንና የሕይወት ቃል ኪዳን በረከቶች ተካፋዮች መሆናችንን፤ እንዲሁም የጌታ ለመሆን ቃል ኪዳን መግባታችንን ያመለክታል፥ ያትማል።

ማቴ. 28፡19፤ ሮሜ 6፡3-5፤ ገላ. 3፡27

ጥያቄ 95

መጠመቅ የሚገባቸው እነማን ናቸው?

መልስ

ከሚታየው ቤተ ክርስቲያን ውጭ የሆኑ በክርስቶስ ማመናቸውንና ለእርሱ መታዘዛቸውን እስኪመሰክሩ ድረስ መጠመቅ አይገባቸውም። የሚታየው ቤተ ክርስቲያን አባሎች ሕጻናት ግን መጠመቅ ይገባቸዋል።

ዘፍ. 17፡7፥10፤ የሐዋ. 2፡38-39፤ 8፡36-37

ጥያቄ 96

የጌታ እራት ምንድነው?

መልስ

የጌታ እራት ክርስቶስ እንዳዘዘው ኅብስትና ጽዋ በመስጠትና በመቀበል ሞቱ የሚታይበት ምሥጢር ነው። ለመቀበል የተገባቸው መንፈሳዊ ምግብ እንዲሆንላቸውና በጸጋ እንዲያድጉ ኅብስቱንና ጽዋውን በሥጋዊ አኳኋን ሳይሆን፤ በእምነት መቀበል አለባቸው። በዚህም መንገድ የክርስቶስን ሥጋና ደም በረከቶችንም በመንፈሳዊ መንገድ ይካፈላሉ።

የሐዋ. 3፡21፤ 1ኛ ቆሮ. 10፡16፤ 11፡23-26

ጥያቄ 97

የጌታን እራት በሚገባ እንዲቀበሉ ከምእመናን ምን ይፈለግባቸዋል?

መልስ

የጌታን እራት በሚገባ መካፈል የሚሹ ሳይገባቸው ቀርበው ለራሳቸውም ፍርድ እንዳይበሉና እንዳይጠጡ የጌታን ሥጋ ለይተው ለማስተዋል እውቀት እንዳላቸው፥ ከእርሱ ለመመገብ እምነት እንዳላቸው፥ በንስሐ፥ በፍቅርና በአዲስ መታዘዝ

ጸንተው እንደሚኖሩ ራሳቸውን መፈተን የሚችሉ መሆን አለባቸው።
ሮም 6፡17-18፤ 1ኛ ቆሮ. 5፡7-8፤ 11፡27፥31-32

ጥያቄ 98
ጸሎት ምንድነው?
መልስ
ጸሎት ኃጢአታችንን እየተናዘዝንና ስለ ምሕረቱ እግዚአብሔርን እያመሰገንን፣ ከፈቃዱ ጋር የሚስማማ ፍላጎታችንን በክርስቶስ ስም ወደ እግዚአብሔር አብ ማቅረብ ነው።
መዝ. 10፡17፤ 145፡19፤ ዮሐ. 1፡9፤ 5፡14፤ 16፡23፤ ፊልጵ. 4፡6

ጥያቄ 99
ስለ ጸሎት የሚመራን እግዚአብሔር የሰጠን ሥርዓት ምንድነው?
መልስ
ስለ ጸሎት የሚመራን ሞላው የእግዚአብሔር ቃል የሚጠቅም ነው። ነገር ግን ልዩ መሪ ሥርዓት የሚሆነው ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ያስተማረው መሪ ጸሎት ነው። ይህ መሪ ጸሎት የጌታ ጸሎት የተባለው ነው።
መዝ. 119፡170፤ ማቴ. 6፡9-13፤ 2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ 1ኛ ዮሐ. 5፡14

ጥያቄ 100
የጌታ ጸሎት መቅድም ምን ያስተምረናል?
መልስ
«በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ» የሚለው የጌታ ጸሎት መቅድም እግዚአብሔር ሊረዳን የተዘጋጀና የሚችልም መሆኑን ተገንዝበን ልጆች ወደ አባታቸው እንደሚቀርቡ ሁሉ በቅዱስ አክብሮትና ድፍረት ወደ እርሱ እንድንቀርብ ከሌሎችም ጋር ሆነን ስለ ሌሎች መጸለይ እንደሚገባን ያስተምረናል።
ሉቃ. 11፡13፤ ሮሜ 8፡15፤ ኤፌ. 6፡18፤ 1ኛ ጢሞ. 2፡1-2

ጥያቄ 101
በመጀመሪያው ልመና ስለ ምን እንጸልያለን?
መልስ
«ስምህ ይቀደስ» በሚለው በመጀመሪያው ልመና እግዚአብሔር ራሱን በሚያስታውቅባቸው ነገሮች ሁሉ እርሱን ለማክበር እኛንና ሌሎችን እንዲያስችልና ሁሉንም ነገር ለራሱ ክብር እንዲያደራጅ እንጸልያለን።

መዝ. 67፡1-3፤ ሮሜ 11፡36፤ ራእ. 4፡11

ጥያቄ 102
በሁለተኛው ልመና ስለ ምን እንጸልያለን?
መልስ
«መንግሥትህ ትምጣ» በሚለው በሁለተኛው ልመና የሰይጣን መንግሥት እንድትጠፋ፥ የእግዚአብሔር የጸጋ መንግሥት እንድትስፋፋ፥ እኛና ሌሎችም ወደ እርስዋ ገብተን በእርስዋ ውስጥ እንድንጠበቅና የክብር መንግሥት እንድትፋጠን እንጸልያለን።
መዝ. 68፡1፤ ማቴ. 9፡6-38፤ ሮም 10፡1፤ 1ኛ ተሰ. 3፡11፤ ራእ. 22፡20

ጥያቄ 103
በሦስተኛው ልመና ስለ ምን እንጸልያለን?
መልስ
«ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን» በሚለው በሦስተኛው ልመና መላእክት በሰማይ እንደሚያደርጉት ሁሉ በማናቸውም ነገር የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንድናውቅ፥ እንድንታዘዝና ራሳችንን እንድናስገዛ፥ እርሱ በጸጋው እንዲያስችለንና ፈቃደኞች እንዲያደርገን እንጸልያለን።
መዝ. 103፡20-21፤ 119፡34-36፤ ማቴ. 26፡39፤ የሐዋ. 21፡14፤ ፊል. 1፡9-11

ጥያቄ 104
በአራተኛው ልመና ስለ ምን እንጸልያለን?
መልስ
«የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን» በሚለው በአራተኛው ልመና ከእግዚአብሔር ነጻ ስጦታ በዚህች ሕይወት መልካም ከሆኑት ነገሮች በቂ ድርሻ እንድንቀበልና ከዚያም ጋር በበረከቱ እንድንደሰት እንጸልያለን።
ምሳ. 10፡22፤ 30፡8-9፤ 1ኛ ጢሞ. 6፡7-8

ጥያቄ 105
በአምስተኛው ልመና ስለ ምን እንጸልያለን?
መልስ
«እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን» በሚለው በአምስተኛው ልመና እግዚአብሔር ለክርስቶስ ሲል ኃጢአታችንን ሁሉ በነፃ ይቅር እንዲለን እንጸልያለን።

እኛም ሌሎችን ከልባችን ይቅር ለማለት ጸጋው ስለሚያስችለን ይህን እንድንለምን የበለጠ ድፍረት ይኖረናል።
መዝ. 51፡1-2፤ ማቴ. 18፡35፤ ማር. 11፡25

ጥያቄ 106
በስድስተኛው ልመና ስለ ምን እንጸልያለን?
መልስ
«ከክፉም አድነን እንጂ ወደ ፈተና አታግባን» በሚለው በስድስተኛው ልመና ኃጢአት ለመሥራት ከሚያነሣሣን ፈተና እንዲያወጣን እንጸልያለን።
መዝ. 19፡13፤ ማቴ. 26፡41፤ ዮሐ. 17፡15፤ 1ኛ ቆሮ. 10፡13

ጥያቄ 107
የጌታ ጸሎት መጨረሻ ምን ያስተምረናል?
መልስ
«መንግሥት ያንተ ናትና ኃይልም ክብርም ለዘለዓለሙ፤ አሜን» የሚለው የጌታ ጸሎት መጨረሻ ስንጸልይ ድፍረታችንን ከእግዚአብሔር ብቻ እንድንቀበል፤ ደግሞም መንግሥት ኃይልና ክብርም የእርሱ መሆናቸውን እየገለጥን፤ እንድናመሰግነው ያስተምረናል። እንዲሁም እግዚአብሔር ጸሎታችንን እንዲሰማ፤ ፍላጎታችንና እምነታችን የተረጋገጠ መሆኑን በመመስከር «አሜን» እንላለን።
1ኛ ዜና 29፡11-13፤ ዳን. 9፡18-19፤ 1ኛ ቆሮ. 14፡16፤ ፊል. 4፡6፤ ራእ. 22፡20-21